# ዐፄ ቴዎድሮስ

እና

# የኢትዮጵያ አንድነት

በ

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
፲፱፻፹፩

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
KURAZ PUBLISHING AGENCY

ስልክ / TEL. 11 27 19

ፖ. ሣ. ቁ. / P. O. BOX 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የሽፋኑ ሥዕል—ሉቃስ አማረ

አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

# ማ ው ጫ

| ተ. ቁ. | አ ር እ ስ ት | ገ ጽ |
|---|---|---|
| 1 | ማስተዋወቂያ | 13 |
| 2 | መቅድም | 21 |
| 3 | ማመልከቻ | 27 |
| 4 | ምስጋና | 31 |
| 5 | <u>ክፍል አንድ</u> | |
| | የዐፄ ቴዎድሮስ የወጣትነትና የሽፍትነት ዘመን | |
| | <u>ምዕራፍ 1</u> | |
| | የደምቢያና የወሎ መሳፍንት ፍልሚያ በጐንደር መንግሥት ውስጥ | 35 |
| | <u>ምዕራፍ 2</u> | |
| | በካሣ ልደትና ዕድገት አካባቢ የነበሩት መሳፍንትና ያገዛዝ ፍልሚያ ፥ ልጅ ካሣ ባሽከርነት ያገለገሉዋቸው መኳንንትና መሳፍንት | 49 |
| | <u>ምዕራፍ 3</u> | |
| | ከአሽከርነት ወደ ሽፍትነት | 63 |
| | <u>ምዕራፍ 4</u> | |
| | ከሽፍትነት ወደ ጋብቻ ፥ ከአማችነት ወደ ሹመት | 69 |

ምዕራፍ 5

ኮሶና ታላቁ የብልት ሥጋ—የልጅ ካሣ ቅያሜና የመጨረሻው ሽፍትነት - - - - - - - 75

ምዕራፍ 6

በመሳፍንቱ መካከል የውጭ አገር የወዳጅነት ሽሚያ - - - - - - - - - - - - - 81

ምዕራፍ 7

የማርቆስ መንበርና ዘረኛዋ የፍትሐ ነገሥት አንቀጽ—የአቡነ ሰላማ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት - - - - - - - - - - - - - 89

ምዕራፍ 8

የራስ ዐሊና የደጃች ውቤ ጦርነት - - - - 97

ምዕራፍ 9

የግብጽ ጦር አጥቂነት ፣ የደጃዝማች ክንፉ ጉብዝና ፣ የነራስ ዐሊ አቤቱታ ለሉዊ ፊሊፕ ፣ የወይዘሮ መነንና ያጼ ዮሐንስ ጋብቻ - - - - 105

ምዕራፍ 10

የደጃዝማች ካሣ አጥቂነት ፣ የደጃዝማች ወንድይራድና የእቴጌ መነን ውድቀት - - - - - 115

6 ክፍል ሁለት

የዘመነ መሳፍንት ማክተም

ምዕራፍ 11

ጠላትን በመናቅ የሚመጣ የመሸነፍ ፍዳ ፣ ደጃች ካሣ ደጃች ጐሹን ጉራምባ ላይ ፣ ራስ ዐሊን አይሻል ላይ ድል እንዳደረጓቸው - - - 123

ምዕራፍ 12

የደጃዝማች ብሩ ጐሹ ሀብት ፣ የደጃች ውቤ መሸነፍ ፣ ደጃች ካሣ ሥርዓተ ንግሥ ተደርጎላቸው ቴዎድሮስ ተብለው እንደ ነገሡ - - 133

ምዕራፍ 13

የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያደረገችው ተጽዕኖ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስና ጳጳሱ አቡነ ሰላማ በኢትዮጵያ ባሉት የካቶሊክ ሚሲዮን መሪዎች ላይ ያደረጉት ተቃውሞ ፣ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጸጐች ውድቀት ፣ የካራዎች ማንሠራራት - - - - - - - - - - - - 149

ምዕራፍ 14

ከንግሥ በኋላ የወሎ ዘመቻ - - - - - - - 157

ምዕራፍ 15

የሸዋ ዘመቻ ፣ የንጉሥ ኃይለ መለኮት ሞትና የምኒልክ በምርኮ ወደ ጐንደር መምጣት ፣ የወይዘሮ በዛብሽና የወይዘሮ ትደነቂያለሽ ልዩነት - - - - - - - - - - - 163

ምዕራፍ 16

የእቴጌ ተዋበች ዐሊ ዕረፍት - - - - - - - 183

ምዕራፍ 17

የሣልሳይ ዮሐንስ ዕድል ፣ ለናፖሊዮን ሣልሳይ የጻፉት ደብዳቤ - - - - - - - - - - - 187

ምዕራፍ 18

ዐፄ ቴዎድሮስ የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነ
ትን ሕግ እንዳቆሙ ፣ ሸዋ በአቤቶ ሰይፉ መሪ
ነት እንደ ሸፈተባቸው - - - - - - - 191

ምዕራፍ 19

የግብጽና የኢትዮጵያ ግንኙነት ባፄ ቴዎድሮስ
ዘመን ፣ የአቡነ ቄርሎስ ጉብኝት በኢትዮጵያ - - 199

ምዕራፍ 20

ነዋሪ የሥልጣን ሽሚያ ፣ የዋግ ሹም ገብረ
መድኅን ስቅላት ፣ የፕሎውዴን አማሟት ፣
በጋረድና በንጉሡ መካከል የተደረገው ጦር
ነትና የሊቀመኳስ ዮሐንስ መሠዋት ፣
የምርኮኛ መከራና ፍዳ ፣ - - - - - - - 211

ምዕራፍ 21

የፈረንሣይ መንግሥት ጣልቃ ገብነት ፣ የደጃ
ዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤል አነሣሥና አወ
ዳደቅ ፣ የእቴጌ ጥሩ ወርቅ ጋብቻ - - - - - 223

ምዕራፍ 22

ያፄ ቴዎድሮስ የመጨረሻው ዘመን ችግር - - 243

ምዕራፍ 23

የመሳፍንቱና የመኳንንቱ የተለያየ አቅዋም - - 249

ምዕራፍ 24

ከቅብዓተ ንግሥ የወረደ የፈላጭ ቆራጭነት
መብት ፣ የባላገርና የነጋዴ የችግር ደረጃ - - - 255

ምዕራፍ 25

ያፄ ቴዎድሮስ መልክ ፣ ቅርፅና ጠባይ ፣ ሰፊ
ምኞትና ውስን ዐቅም - - - - - - - - 263

ምዕራፍ 26

ያፄ ቴዎድሮስ የውጭ ጉዳይ ግንኙነታቸውና
አገራቸውን ለማሠልጠን ያላቸው ጽኑ ፍላጐት - - 275

7 ክፍል ሦስት

ምዕራፍ 27

የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ጠብና ፍጻሜው ፣
ወደ አፍሪካ የሚላከው የመልክተኛ ዐይነ
ትና የቆንስል ካሜሮን ተሹሞ መምጣት - - 287

ምዕራፍ 28

የኢትዮጵያና የፈረንሣይ ግንኙነት ፣ ጉዮም ለዣ
ንና አጉስት ባርዴል - - - - - - - - - 295

ምዕራፍ 29

ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የጠቡ አጀማመር ፣
የቆንሲል ካሜሮን መታሰር ፣ የሆርሙዝ
ራሳም ተልኮ መምጣትና አብሮ መታሰር - - 301

ምዕራፍ 30

የማርቲን ፍላድ ወደ ሎንዶን መላክ ፣ ስለ እስረ
ኞቹ ጉዳይ በእንግሊዝ ባለሥልጣኖች መካ
ከል የተደረገው ውይይትና የመጨረሻው
ወታደራዊ ውሳኔ - - - - - - - - - 321

ምዕራፍ 31

የጄኔራል ናፒዬር ጦር አዝማችነትና የእንግሊዝ ጦር ሰናፌ መድረስ - - - - - - - - - 333

ምዕራፍ 32

ባዬ ቴዎድሮስ በኩል ያለው ዝግጅትና ትልቁ መድፍ - - - - - - - - - - - - - 361

ምዕራፍ 33

በጥርጣሬ የአቤቶ ዳርጌና የበዐልጋዳ አርአያ እስራት ፤ የእሮጌ ጦርነት ፤ የፊታውራሪ ገብርዬ ሞት - - - - - - - - - - - - - 373

ምዕራፍ 34

የዕርቅ ጭምጭምታ ፤ ቴዎድሮስና ናፒዬር የተለዋወጡት መልእክት - - - - - - - - - 393

ምዕራፍ 35

ሁለተኛው ያፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤ ለጄኔራል ናፒዬር ፤ የእስረኞቹ መለቀቅ - - - - - - 399

ምዕራፍ 36

የዕርቁ ተስፋ መፍረስ ፤ የፉላና የሰላምጌ ጦርነት ፤ ያፄ ቴዎድሮስ ፍጻሜ - - - - - - - 405

ምዕራፍ 37

ባፄ ቴዎድሮስ ሰውነትና ባሕርይ ላይ አጭር አስተያየት ፤ ስለ ዝማንነታቸው የተደረሰላቸው ግጥም - - - - - - - - - - - - - 431

ምዕራፍ 38

የመቅደላ ውድቀት ፤ ያፄ ቴዎድሮስ ሥርዓተ ቀብር ፤ የእቴጌ ጥሩ ወርቅ ሞት ፤ የእንግሊዝ ጦር ወደ አገሩ መመለስ - - - - - - - - 441

ምዕራፍ 39

የናፒዬር አሸናፊነት በሎንዶን ስለ መሰማቱና የተደረገለት አቀባበል - - - - - - - - - 469

ምዕራፍ 40

እንግሊዝ ከኢትዮጵያ ለቆ የወጣበት ምክንያት - 475

8 አባሪ አንድ

ካፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤዎች ጥቂቶቹ - - - - - 481

9 አባሪ ሁለት

ባፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የነበሩ የመኳንንትና የሹማምንት ፤ የጸሐፊዎችና የተርጓሚዎች ዝርዝር - - - - - - - - - - - 503

# ማ ስ ተ ዋ ወ ቂ ያ

ዐፄ ቴዎድሮስ የተነሡበት የታሪክ ወቅት ለቅርቡ ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ ቁልፍ የሆነ መነሻነት አለው ። በአንድ በኩል ፣ በአፍሪካና በእስያ ሕዝቦች ላይ ኀያል ተጽዕኖ ለማድረግ በዘመናዊ ኢንዱስትሪና ድርጅት ታጥቆ የተነሣውን ፣ የምዕራብ አውሮፓን የቅኝ አገዛዝ ኃይል በብቸኝነት መክቶና ተቋቁሞ የኢትዮጵያን ነጻነት ለማቆዩት የተቻለበት ረዥም ፣ መሪርና አዡሪ ታሪካችን መመዝገብ የጀመረው ቀደም ባሉት ዘመናትም ቢሆን ፣ በተለይ ጕልቶ የወጣው በቴዎድሮስ ዘመን ነው ። የቴዎድሮስ የአንድነትና የነጻነት ተጋድሎ ፣ የመቅደላው መሥዋዕትነት ፣ በአጠቃላይ የጀግንነት አርአያነት በነጻነት ተጋዳይነት ታሪካችን ውስጥ ዘላለማዊና አንጸባራቂ ሥፍራ ይዞ የሚኖር ፣ የተከታታይ ትውልድ ጥልቅ አክብሮት ሊለየው የማይገባ እጅግ አኩሪ ቅርስ ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ፣ አገሪቱ በረዥም ዘመን ፊውዳላዊ የታሪክ ሒደት ውስጥ ከወደቀችበት ኋላቀርነትና ፣ በተለይም ከቴዎድሮስ በፊት በነበረው የአንድ መቶ ዓመት ዕድሜ ከደረሰባት አስከፊ ሁከትና መከፋፈል እንድትወጣ ፣ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ተመሥርቶ አስተዳደር እንዲስተካከል ፣ ቀደምት ዓላማ ይዘው የተነሡት ቴዎድሮስ ናቸው ።

የዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን ሁለት ባሕርያትን ያጣመረ ነው ። አንደኛው ገጽታው ፣ ከአንድ የታሪክ ዘመን ወደ ሌላ የታሪክ ዘመን ሽግግር የተደረገበት ድልድይ መሆኑ ነው ። ከቴዎድሮስ በፊት በነበሩት ሁለት መቶ ዓመታት ፣ ነገሥታቱ በቅርብ ይቆጣጠሯቸው በነበሩት የመሐል አገር ፣ የሰሜን ግዛቶችና አውራጃዎች ውስጥ ልዩ ሁኔታ ተከስቷል ። ይኸውም የዘውዱ ሥልጣን መዳከምና በየአውራጃው የነበሩት መሳፍንት በየፊናቸው አምባገነን እየሆኑ ፣ የፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣናቸው እየጐላ መምጣቱና

ለነገሥታቱም አንገብርም ፣ አንታዘዝም እያሉ አሻፈረኝ ማለ
ታቸው ነው ።

በተለይም ጐንደር ፣ የነገሥታቱ ቋሚ መኖሪያና ከተማ ሆና
በ17ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ መቆርቆሯ ፣ ለዚህ ሒደት
ዐይነተኛ ምክንያትና መነሻ ሆኗል ።

ነገሥታቱ ቀደም ሲል አገር ያስተዳድሩ የነበረው ፣ የጦር
ሠፈራቸውን ከአውራጃ ወደ አውራጃ በማዘዋወርና ፣ በየጊዜው
ሹም ሽር እያደረጉ ለዘውዱ ታማኝ የሆኑ መሳፍንትን በማስቀ
መጥና ሥልጣናቸውን በማሳየት ነበር ። ጐንደር ከተቆረቆረች
በኋላ ግን ፣ ተቀማጭነታቸው በአንድ ቦታ በመወሰኑ በአንዳንድ
አካባቢ ሥልጣናቸው እስከ መረሳት ደርሶ ፣ በእነሱ ፋንታ መሳ
ፍንቱ ይበልጥ ሥልጣንና ኃይል እያገኙ መጡ ።

በጐንደር ቤተ መንግሥት የሚታየው የተድላና የደስታ ኑሮ ፣
ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ድልወት እያመዘነ በመሔዱ ፣ የዙፋኑን
ሥዩምና የመሳፍንቱን ማንአለብኝ ባይነት ይበልጥ እንዲባባ
ስና እንዲፋጠን አድርጐታል ። በመጨረሻም ፣ ከየአውራጃው
የተነሡት መሳፍንት ፣ አንዱ ሌሎቹን አሸንፎ የበላይ ለመሆን
በሚያደርገው የርስ በርስ ጦርነትና ፉክክር ዘመኑ የጥፋትና
የእልቂት ሆነ ። የመሳፍንቱ ዓላማ ፣ አንዱ በሌሎቹ ላይ ኃያል
ነትን አግኝቶ ፣ በጐንደር ነገሥታት ዘውድ-ሥር ሌላውን ለመ
ቈጣጠርና ዋና እንደራሴ ሆኖ ለመግዛት ነበር ። ከ1761 እስከ
ሥቶ ፣ ቴዎድሮስ እስከ ነገሡ ድረስ የቆየውና ፣ በታሪክም
«ዘመነ መሳፍንት» ተብሎ የሚታወቀው ጊዜ ይህ ነው ።

የቴዎድሮስ ጊዜ ፣ ከአንድ የታሪክ ዘመን ወደሌላ የታሪክ
ዘመን ሽግግር የተደረገበት ድልድይ ነው የምንለውም ፣ እርሳ
ቸው ይህን ሁከትና ውዝግብ ለማቆምና ጠንካራ ማዕከላዊ መን
ግሥት ተመሥርቶ የአገሪቱን አንድነት መልሶ የመገንባቱን
ተግባር ቀደምት ዓላማቸው አድርገው በመነሣታቸው ነው ።

ዐፄ ቴዎድሮስ ፣ ይህን ዓላማቸውን ዕውን ለማድረግ ሲሉ
የተለሟቸው የአስተዳደር ዘዴዎች ፣ ከሌሎቹ ከጊዜው የቀደሙ
ስለ ነበሩ ፣ አገሪቱ የነበረችበት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታ ፣



እንዲሁም ሰፍኖ የነበረው የፖለቲካ ባህል ሊቀበላቸው አልቻ
ለም ። በየአውራጃው የነበሩትን ገዥዎች የመንግሥት ተቀጣ
ሪና ደመወዝተኛ ለማድረግ ሞክረዋል ። የመሳፍንቱ ወታደሮች
በባላገሩ ላይ የሚያደርሱትን ዘረፋና ቅሚያ ለማቆም ሲሉ ቋሚ
ጦር ተመልምሎ እንዲሠለጥንና በደመወዝ እንዲተዳደር ጽኑ
ሐሳባቸው ነበር ። ከዚህም በተረፈ ፣ የመሬትን ሥሪት ለመለ
ወጥ ፣ የቤተ ክህነትን የፖለቲካ ተጽዕኖ ለማስወገድና ሰፊ የኢኮ
ኖሚ ይዞታውን ለማስለቀቅ ፣ በአጠቃላይ ፣ ዘመናዊ የአስተዳ
ደርና የኢኮኖሚ ሥልጣኔ አገር ውስጥ እንዲገባላቸው ያለፋታ
ደክመዋል ።

እዚህ ላይ ቁምነገሩ ፣ ቴዎድሮስ በሕይወት ዘመናቸው የወ
ጠኑትን ሁሉ ሊፈጽሙ ቻሉ ወይስ አልቻሉም? የሚለው ጥያቄ
አይደለም ። የዘመኑ ታሪክ እንደሚመሰክረው አብዛኛው ዕቅ
ዳቸው አልተሳካላቸውም ። የመሳፍንቱና የቤተ ክህነት ጥላቻና
ተቃውሞ ፣ የዘረጉትን የአስተዳደር ሥርዓት እያደናቀፈ አስቀ
ርቶባቸዋል ። እሳቸውም ምኞታቸው በራቀ መጠን ፣ ቁጣቸውና
እልኻቸው እየገነፈለ ፣ በግለሰቦችም ሆነ በአውራጃዎች ላይ
የሚያሳርፉት ቅጣት የከፋ ሊሆን ችሏል ።

ይሁን እንጂ ፣ እስከ ርሳቸው ዘመን ድረስ ያለ ምንም ገደብ
በሕዝቡ ላይ ሲወርድ የነበረውን ጥፋትና እልቂት ለማቆምና ፣
ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ለመትከል ቆርጠው መነሣታ
ቸው ፣ ለዘመነ መሳፍንት ፍጻሜ ምክንያት መሆናቸውን ታሪክ
ይመሰክራል ። ከርሳቸው በኋላ የመጡት ነገሥታት ፣ ጠንካራ
የፌውዳል ማዕከላዊ መንግሥት ለማቆምና ፣ ተበታትነው የነበ
ሩትን የአገሪቱን ክፍሎች በአንድ አስተዳደር ሥር ለማሰባሰብ
የቻሉት ፣ ርሳቸው በከፈቱት ጐዳና ተጉዘው ነው ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚከሰተውና ፣ ለቴዎድሮስ የታሪክ
ዘመን ሌላውንና ሁለተኛውን ገጽታ የሚያጐናጽፈው ባሕርይ ፣
የዛሬይቱ ኢትዮጵያ መሠረት የተጣለው ፣ በዚሁ በርሳቸው ዘመን
መሆኑ ነው ።

እስከ 16ኛው ምዕት ዓመት ድረስ የነበረው የማዕከላዊው
ዘመን ረዥም ታሪካችን ፣ በመሐልና በሰሜን አውራጃዎች

ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ፣ መላውን የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ቆዳና
ከዚያም ባሻገር የነበሩ ክፍሎችን በአንድ የታሪክ ሒደት ያስተ
ሳሰረና ያወራረሰ ነው ። ለዚህ ዘመን ታሪክ ፣ ወሳኝነት ከነበራ
ቸው ክስተቶች መካከል አንዱ ፣ በክርስትናና በእስልምና ሃይማ
ኖት ሽፋን የተካሔደው የሥልጣን ትግልና የርስ በርስ ጦርነት
ነው ። ነገሥታቱ በምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ አውራጃዎች
ላይ ሲዘምቱ ፣ ሕዝቡን ክርስትና ሲያጠምቁና መስጊዶችን
ሲያቃጥሉ ፣ በአንጻሩ ደግሞ ፣ በተለይ በ16ኛው ምዕት ዓመት
በአህመድ ግራኝ መሪነት እነዚህ አውራጃዎች ኃይል አግኝተው ፣
በልብነ ድንግል ላይ ካመፁ በኋላ ፣ መሐሉንና ሰሜኑን አገር
እየወጉ ሕዝቡ እስልምናን እንዲቀበል ሲያስገድዱና ቤተ ክርስ
ቲያኖችን ሲያቃጥሉ የምናየው የርስ በርስ የጦርነት ታሪክ ፣
የሃይማኖት ጦርነት እየሆነ ሲቀርብ ኖሯል ። ሆኖም ፣ ሃይማኖት
ሽፋን እንጂ መሠረታዊ የውጊያ መነሻ ሆኖ አያውቅም ። ይህ
ቢሆን ኖሮ ክርስቲያን ከክርስቲያን ፣ እስላምም ከእስላም ባል
ተዋጋ ነበር ። ሁልጊዜም አንዱ ሌላውን ለማስገበር ፣ ለመሬት
ወይም የንግድ መሥመርን ተቆጣጥሮ የኢኮኖሚ ኃይል ለማግ
ኘትና የፖለቲካ የበላይነትን ለመያዝ ነው ። በኢትዮጵያ የማ
ዕከላዊ ዘመን (ከ13ኛው ምዕት ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ እስከ
16ኛው አጋማሽ) ታሪክ ከዐምደ ጽዮን እስከ ልብነ ድንግል ተደ
ጋግሞ የምናየው ይህንኑ ነው ።

ሌላው ለኢትዮጵያ ታሪክ ፣ ለሕዝቧ ዕድገትና ባሕርይ ወሳ
ኝነት ያለው የሕዝብ ፍልሰት ነው ። ከዚህም አንዱና ዋንኛው ፣
ከ16ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ የኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ልዩ ዘር
ፎች ፣ በመላው የአገሪቱ ክፍሎች መስፋፋትና ፣ ይህም ያስከተ
ለው መሠረታዊ ሒደት ነው ።

ፍልሰቱ የጀመረበት ወቅት ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የነገሥ
ታቱም ሆነ የአውራጃዎች ሥልጣን የተዳከመበት ወቅት ነበር ።
በተለይ ከላይ በተመለከትነው ሁኔታ ፣ በአህመድ ግራኝ መሪነት
በተቀጣጠለው ጦርነት ፣ የመሐልና የሰሜኑም ሆነ ፣ የምሥራቅና
የደቡብ ምሥራቁ የሀገሪቱ ኃይል ፣ ከፉኛ የተዳከመበት ነበር ።

በዚህ መሐል ፣ በጐሣና በገዳ ተደራጅቶ የተነሣው የኦሮሞ
ብሔረሰብ ፍልሰት ፣ በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ የአገሪቱን



ምድር በስፋት ለመሸፈን ችሏል ። ይህን ሁኔታ ተከትሎ የመጣው
መሠረታዊ ሒደት ፣ ለኢትዮጵያ ታሪክና ሕዝቧም ዛሬ ላለው
ማኅበራዊ ዕውነታ አንዱ ወሳኝ ገጽታ ሆኗል ። የብሔረሰቡ ልዩ
ልዩ ዘርፎች እንደየሔዱበት አካባቢ ሁኔታ ፣ የተለያየ ሒደት
እንዲከሰት አድርገዋል ። እስልምና ተስፋፍቶ በነበረበት አው
ራጃ እስልምናን ፣ ክርስትና ባለበት ክርስትናን የተቀበሉ አሉ ።
በቁጥርም ሆነ በድርጅት አይለው ፣ ቀድሞ የነበረውን ሕዝብ እን
ዲዋጥ በማድረግ ፣ የበላይነትን የያዙባቸው አካባቢዎችም በተለ
ያዩ ክፍሎች ይገኛሉ ።

በቴዎድሮስ ዘመን የነበረውን ሁኔታ ፣ ቀድሞ ከነበረው ጋር
ስናነጻጽር በጉልህ የሚታየን አንድ ነጥብ አለ ። ይኸውም ፣ ከኢት
ዮጵያ የዛሬ ድንበሮች ውጭ ጭምር ፣ ቀድሞ በአንድ የታሪክ
ሒደት ተሳስረው የነበሩት ክፍሎች ፣ ከ17ኛው እስከ19ኛው ምዕት
ዓመት በየፊናቸው ተከፋፍለውና ተለያይተው መገኘታቸው ነው ።
ይህም ሊሆን የበቃው ከላይ እንደ ተመለከትነው ፣ በርስ በርስ
ጦርነት በደረሰው መዳከምና ፣ ቀድሞ በአንድ ታሪክ የተሳሰረውን
ክልል መልሶ ለማያያዝ የሚችል ኃይል ሊፈጠር ባለመቻሉ ነው ።

ቴዎድሮስ የተነሡበት የዘመን መሳፍንት መድረክ ፣ ከሰ
ሜኑና ከመሐሉ አገር የኢትዮጵያ ክልል ያለፈ አልነበረም ።
የርሳቸው ሥልጣን ከፍተኛውን ደረጃ በያዘበት ወቅት እንኳን ፣
ክልላቸው በሰሜን ከቦጐስ (ዛሬ ከረን) በደቡብ ደግሞ ከሸዋ
አልዘለለም ።

ይሁን እንጂ ፣ ቴዎድሮስ ዘመነ መሳፍንት እንዲያከትም
ከማድረጋቸውም በላይ ፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ መሠረትም የተጣ
ለው በዚሁ በርሳቸው ዘመን ነው ስንል ፣ ያለ ምክንያት አይደ
ለም ። ቀድሞ በአንድ የታሪክ ክልል ውስጥ የነበረውን ክፍል
ሁሉ ፣ ከረዥም ጊዜ በኋላ በ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ
እንደገና ለማያያዝ ዓላማ ይዘው የተነሡት እርሳቸው በመሆና
ቸው ነው ። በተለይም ቅኝ ገዥ ኃይሎች በአፍሪካና በእስያ ሕዝ
ቦች ላይ የገዥነት ዓላማ ይዘው በተነሡበት ዘመን ፣ ይህን አደጋ
በቅድሚያ መገንዘባቸውና ከውስጥ የነበረውን መከፋፈልና
ድክመት አስወግደው ፣ አገሪቱን መልሶ የአንድ ታሪክ ባለቤት
ለማድረግ መነሣታቸው ለዚህ ክብር ያበቃቸዋል ።

እንደ ተመለከትነው ፣ በእርግጥ በሕይወታቸው ዘመን እርሳቸው ይህን ዓላማ ዕውን ለማድረግ አልተቻላቸውም ። የመቅደላን ዓርማ በማንሣት ፣ ከቅኝ ገዥዎች ጋር እየተፋለሙ አኩሪ የተጋድሎና የድል ታሪክ ለመጻፍ የታደሉት ከርሳቸው በኋላ የነገሡት ዮሐንስና ምኒልክ ናቸው ። በዚህም ተጋድሎና ድል የኢትዮጵያ ነጻነት በብቸኝነት ታፍሮ እንዲኖርና ፣ በሰሜኑ ክፍል ለአጭር ጊዜ ከተፈጠረው ሁኔታ በስተቀር ፣ የቅኝ ገዥዎች ተጽዕኖም ከዛሬው የኢትዮጵያ ድንበር ውጭ ተገቶ እንዲቆም ተደርጓል ።

የዐፄ ቴዎድሮስን ዘመን ታሪክ በሚገባ ለመገንዘብ ፣ አንዳንድ ጊዜ ወደኋላ ካለው ታሪክ ጋር ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ተከትሎት ከተፈጸመ ሁኔታ ጋር እየተመላለሱ ማስተያየትንና ማያያዝን ይጠይቃል ። ድርጊቶች ይፈጸሙ ከነበረበት ክልል ውጭ የነበሩ ሁኔታዎችንም ማዛመድ ተገቢ ነው ።

«ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት» የሚል ሰፊ ርዕስ ይዞ በቀረበው በአቶ ተክለ ጻድቅ መኵሪያ መጽሐፍ ውስጥ ፣ የዘመነ መሳፍንት ፍልሚያና የቴዎድሮስ ሥልጣን ከደረሰባቸው የሰሜንና የመሐል አገር አውራጃዎች በተጨማሪ ፣ በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የነበረውንም ሁኔታ ከታሪክ አንጻር ማዛመዱ ተገቢ ነው ። ይህንን ሳያገናዝብ መጽሐፉን የሚያነብ ሰው ፣ «ኢትዮጵያ የምንለው ይህን ብቻ ነው?» ብሎ ግራ ሊጋባ ይችላል ።

የዚያን ዘመን መሳፍንትና ነገሥታት ፣ በዘመናቸው አነጋገር ፣ "ጋላ" ፣ "ትግሬ" ፣ "አማራ" ፣ "ወሎ" ፣ "ሸዋ" ፣ "እስላም" ፣ "ክርስቲያን" ሲሉ ፣ ምን ታሪክና ባህል ይዘው እንደ ሆነ የዘመኑን ባሕርይ ካላጤኑ ፤ የዛሬው ትውልድ አንባቢ ሊደናገር ይችላል ። ጋብቻም በፊውዳል ኢትዮጵያ እስከ ዘመናችን ድረስ ዐይነተኛ የፖለቲካ መሣሪያ ሆኖ ቆይቷል ። በዘመነ መሳፍንት ማን ማንን እንዳገባ ፣ ማን ከማን እንደ ተወለደና እንደ ተዋለደ ፣ አቶ ተክለ ጻድቅ መኵሪያ አሣምረው በዝርዝር ጽፈዋል ። በአጠቃላይ የጋብቻን ፣ የሃይማኖትንና የትውልድ ሐረግን ጉዳይ ከፖለቲካ ትርጉሙ ፣ አንዱ ሌላውን ለመቈጣጠርና የበላይነት ለመቀዳጀት ከነበረው ዓላማ አንጻር መረዳቱ ጠቃሚ ነው ።



መሳፍንቱ ለየራሳቸው የሥልጣን ዓላማ ሲሉ ፣ አንዱ በሌላው ላይ ቅስቀሳ ያካሒዱ እንጂ በትውልድ ፣ በጋብቻ ፣ በሃይማኖትና እንዲሁም በቋንቋ የተሳሰሩ ናቸው ። የዚህን መተሳሰር ለማየት ያህል ፣ ለዘመነ መሳፍንት መምጣት ምክንያት የሆኑት ፣ የትግሬው ሚካኤል ስሑል ያገቡት ፣ የጐንደሬዋን የእቴጌ ምንትዋብን ልጅ ነው ። የየጁው ትንሹ ራስ ዐሊም የስሜኑንና የትግሬውን የደጃች ውቤን ልጅ ሂሩትን አግብተዋል ። በኋላም ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ የየጁውን የራስ ዐሊን ልጅ ምንትዋብን አግብተዋል ። የዝምድናው ዝርዝር መላውን የመሳፍንት ቤተሰብ የሚያገናኝ ነው ። እዚህ ላይ ቁልፍ ነገር ሥልጣን መሆኑ መዘንጋት የለበትም ።

በዚህ የማስተዋወቂያ ጽሑፍ ውስጥ ፣ የቴዎድሮስን ዘመን ታሪክ ዋና ዋና ገጽታዎች ለመጠቆም ጥረት የተደረገው ፣ አንባቢው የአቶ ተክለ ጻድቅ መኵሪያን ዝርዝር ታሪክ ሲከታተል ፣ ነገሮችን የማገናዘቢያ አድማስ እንዲኖረው ታስቦ ነው ። ለአንባቢው በሚከተሉት ገጾች ውስጥ ፣ ምናልባትም ተከታታይ ደራሲዎች ሊጽፉ በማይችሉበት ጣዕምና ለዛ የተቀናበረ ጣፋጭ የታሪክ ድግስ ቀርቦለታል ።

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

የካቲት 1981

# መ ቅ ድ ም

ዐፄ ቴዎድሮስ ፣ በተለመደው ሥርዓተ ንግሥ ከነጋሢ ፣ ወደ
ነጋሢ ዘውድና ዙፋን በሰላም በሚተላለፍበት ዘመን ከነጋሢ
ተወልደው በዙፋን የወጡ ሳይሆን ፣ በመጨረሻዎቹ በጐንደር
ነገሥታት ድክመት የነገሥታቱን ሥልጣን በጉልበታቸው በወ
ረሱት በመሳፍንቱ የማያቋርጥ የርስ በርስ ጦርነት ምክንያት
በአገሪቱ ላይ በደረሰው ከፍተኛ መከፋፈልና የርስ በርስ ጦርነት
በተፋፋመበት ጊዜ ፣ በዚሁ ጐን የቱርኮች ፣ የግብጾችና የሌሎች
ወረራ በሚያሠጋበት ወቅት ፣ ሳይታሰቡ ካንዲት ወረዳ ከቋራ
ተነሥተው ፣ ለመከፋፈሉ ደንበኛ ምክንያት የሆኑትን መሳፍንት
በሚያስደንቅ አኳኋን በየተራ ደምስሰው ነው ። ዐፄ ቴዎድሮስ
አንደኛ ያገር አንድነትን ፣ ሁለተኛ የማዕከላዊ መንግሥትን አቅ
ዋም እንደገና የመሠረት ደንጊያ ያጸኑ ጦርጣራ ንጉሥ ናቸው ።

ለዚህ ከፍተኛ ብሑራዊ ተልዕኮ አብነት የሆኗቸው ፣ ያለ
ግኸ ከራሳቸው በፍጥረታቸው ያገኙዋቸው መሣሪያዎች ፣ ይኸ
ውም ማለት የከፍተኛ ዓላማ ምኞት ፣ ድፍረት ፣ ቁርጠኝነት ፣
ሞትን መናቅ ፣ ድልወትን መራቅ ናቸው ፡ በድልወትና በልስላሴ
ተደላድለውና ተንሠራፍተው ፣ ትጥቃቸውን ከርሳቸው በተሻለ
አኳኋን አደራጅተው ፣ በብዙ ሠራዊት ተከበው የቆዩት የቤጌ
ምድር ፣ የጎጃም ፣ የስሜንና የትግራይ ፣ የላስታ ፣ የወሎና የሸዋ
መሳፍንት ሁሉ ፣ በሰው እጅ በማይሠሩ ከባሕርይ በሚገኙ ፣ በነ
ዚህ መሣሪያዎች እና ቁጥሩና ትጥቁ ባነሰው በኝህ ደፋር ጀግና
በሚመራው ወታደር በየተራ እየተመቱ ወደቁ ። እላይ ኩተጠቀ
ሱት የባሕርይ መሣሪያዎቻቸው በቀር ፣ ለቴዎድሮስ ልዕልና
በጣም የረዳቸው ሌላው በጐን የተገኘው ምክንያት ፣ በመዠመ
ሪያው ያነሣሣቸው ወቅት በጠላቶቻቸው ዘንድ መናቃቸው
ነው ። ከቸልታ ጋር ፣ ከድካም ጐን ብዙ ጊዜ ጠላቱን የናቀ ጉል
በታም ነኝ ባይ ፣ በንቀት የተነሣ ኀደኛ ሳይጨምር በራሱ ተማ
ምኖ የሚዋጋ ባልጠበቀው መንገድ በናቀው ጠላቱ ፊት ሲዋረድ
ይኖራል ።

መሪዎች ትምህርቱን አተኩረው መቅሰምና መማር ያዳግ
ታቸዋል እንጂ ፣ ይህ እንግዳ ነገር ሳይሆን በዓለም ታሪክ ውስጥ
ሲደጋገም የኖረ ነው ። ቁመተ ዝርጋዳው ፣ ጥሩር የለበሰው ፣ የራስ
ቁር በራሱ የደፋው ፣ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ የመሰለ ረዥም
ጦር የጨበጠው ጐልያድ ፣ ከዱላና ከወንጭፍ በቀር ምንም በሌ
ለው ፣ በትንሹ የበግ እረኛ ፣ በዳዊት የወንጭፍ በትር ተመትቶ
ማልሳይ (336 — 330) አንድ ሚሊዮን ጅምላ ወታደር አስከትሎ
40,000 ጦር ባስከተለው ፣ የጦርነት ዘዴ በተማረው ፣ በወጣቱ
የግሪክ ንጉሥ በታላቁ እስክንድር ተሸንፏል ።

የጦርነት ዘዴ ብቻውን ይጠቅማል እንዳይባል ፣ የጦርነትን
ባህል ሲያጠኑ የኖሩት ፣ ዓለምን ያንቀጠቀጡት ፣ ቁጥራቸው የበ
ሰሜን ነገሥታት ሲያስግዱ የኖሩት ሮማውያን ፣ በተድላ በደ
ሰሜን ነገሥታት ሲያስግዱ የኖሩት ሮማውያን ፣ በተድላ በደ
ስታ ፣ ከባቢሎን ወዲህ ወሰን በሌለው የኑሮ አዱኛ በተንቀባረ
ሩበት ሰዓት ፣ ሳያስቡት የወረራ ውርደት የደረሰባቸው ፣ ቀደም
ባለው ጊዜ ባርባር (አረመኔ) እያሉ በንቀት በሚሰድቧ
ቸው ፣ ምንም ሥልጣኔና የጦር ዕቅድ ባልነበራቸው ፣ ከሰሜን
ተዥጐድጉደው በፈለቁ የጀርማኒክና የካውካዝ ነገዶች መንጋ
ነው ። ባገራችንም ፣ ዐፄ ልብነ ድንግል በግራኝ አህመድ ፊት የመ
ሸነፍ ውርደት የደረሰባቸው ፣ በዚሁ የንቀት ትምክህት መሆኑ
በሥፍራው ተተርኳል ። በዐድዋም ‘ኃያል ነን ፣ ሥልጡን ነን’
እያሉ የተመኩት ጣሊያኖች ፣ ‘አልሠለጠኑም ፣ የተከፋፈሉ
ናቸው ፤ የኛንም ያህል ኃይል የላቸውም’ እያሉ በናቁዋቸው ፣
ኢትዮጵያውያን ፊት ያዋረዳቸው ይኸው ንቀት ነው ። በዚህ
ዐይነት በዓለም የሕይወት መዝገብ ውስጥ የተከበረው በተናቀው ፣
የደላው ባልደላው ፣ በኃይሉ የተዝናናው በታታሪው የተሸነፈ
በት ታሪክ በሰፊው ተመዝግቦ ይገኛል ። ነገር ግን ፣ ለትምህርት
ከተመዘገበው ታሪካዊ ጽሑፍ የሚማሩት ቁጥራቸው በጣም ያነሰ
ነው ። በዚህ ፋንታ ፣ መሪ ሁሉ በራሱ ኃይልና ዕውቀት በመተ
ማመን በውድቀት አዘቅት ይሰጥማል ።

ዐፄ ቴዎድሮስም በሽፍትነታቸው ሰዓት ፣ አንድ ጊዜ
«ካሣ የቋራው ሽፍታ» ሌላ ጊዜ ፣ «ዕብዱ ካሣ» እንደዚሁም
«ያ ቀለኛ ፣ የፍየል እረኛ» እየተባሉ በገዥዎቹ በነእቴጌ መነን



ዘንድ በንቀት ሲዘበትባቸው ነበር ። ዋናው መስፍንም ራስ
ዐሊ በመጨረሻ እንደዚያ ተዋርደው መሸሻቸው ላይቀር ፣ በመ
ዠመሪያው ወቅት ፣ «ምንም ቢሆን ለካሣ ጦር አልጭንለትም»
ሲሉ መቆየታቸውን ፣ የዘመኑ ታሪክ ጸሐፊ የመዘገቡትን ወደ
መጽሐፉ አካል ስንገባ እናገኘዋለን ። ይኸውም ማለት ፣ በተላከ
ጦር እደመሰስዋለሁ እንጂ ፣ ራሴ ጦር መርቼ አልሔድለትም
ማለት ነው ።

በዚህ ዐይነት ፣ በኩራትና በትምክህት አንዱ የሌላውን
መሸነፍ በሰማ ቁጥር ፣ «እንዴት! አይደረግም!» እያለ በመደነቅ ፣
የካሣ ጦርጦራው ወታደር ከደጃፉ ደርሶ በመታው ጊዜ ተሸንፎ
የውድቀት ጽዋዉን መራራ ወይን እየተንገፈገፈ በየተራ በተለያዩ
ጊዜያት ከመጠጣት በቀር ፣ ካሣ የንጉሠ ነገሥትነቱን ዘውድ
በደረስጌ ማርያም እስከ ተቀዳጁ ድረስ ፣ ሁለት መሳፍንት እን
ኳን ፣ ቀን ወስነው በኅብረት ተስማምተው ፣ ወታደራቸውን
አስተባብረው ጦርነት ገጥመዋቸው አያውቁም ። ስለዚህ ፣ በዚህ
የንቀት አቅዋም እርሳቸው ሲጠቀሙ ፣ ጠላቶቻቸው መሳፍንቱ
ተጐዱ ። ሁሉም የኅብረትና የአወጋግ ስሕተታቸውን የተረዱት ፣
ለማረም በማይችሉበት ፣ ከተሸነፉ በኋላ በምርኮና በእስራት
ባሉበት ፣ በሐዘን ፣ በትካዜ ፣ በኃፍረት በተጨበጡበት ሰዓት
ነው ። ካሣ ከመዠመሪያው ተፈርተው ቢሆን ኖሮ ሊደመሰሱ
በቻሉ ነበር ። ራሱ ተሸናፊው ያለፈን ጊዜ መልሶ እንደገና ጨብጦ
አሻሽሎ ለመጠቀም ለማንም ፍጡር አይቻልም ። ወደፊትም
የማይቻል ተሸናፊዎችን ሲያስተክዝ ፣ አሸናፊዎችን ሲያስደስት
የኖረ አብነተ ቢስ የሆነ ፣ የሰው ልጅ የኩራቱ የደካማ ጐንና የት
ምክህቱ ውጤት ነው ። በዚህ ምክንያት ብልህ ሰው ‘ከማንም
አልበልጥም ፣ ከማንም አላንስም ይሆናል’ ብሎ ከልቡ የሚያምንና
ጠላቱን ሳይንቅ ፣ ራሱን ሳያኩራራ የሁሉንም አብነት ከመዠመ
ሪያው ላይ በትጋትና በንቃት የሚያዘጋጅ ነው ።

ይኸውም ሆኖ ፣ ከራስ ከአካል ድካምና ከአዕምሮ ሕጸጽ
ጋር ዓለምና የዓለም ያኗኗር ውዝግብ ራሱ ፣ በሰው ልጅ አዕምሮ
የማይጨበጥ ፣ በእጅ የማይዳሰስ ፣ ውስብስብ ሐረግ የበዛበት ፣
የአሳብና የድርጊት ጉራንጉር ፣ የእንቅፋት ደን የመላበት ስለሆነ ፣
ማንም ጉልበቱ የጸና ፣ አዕምሮው የበሰለ አልሸነፍም ባይ ፣ ለዘለ
ቄታው የክንውን አንጡራ ባለቤት ሆኖ ፣ ከምኞቱ ከክብሩ

ሳይዛነፍ ፣ በድል አድራጊነት ተሸልሞ እየወጣ ዕድሜውን የሚ
ፈጅ በጣም ብርቅ ነው ። የማናቸውም የዕድል ጽዋ በየተራ ካንዱ
ወደሌላው ሊተላለፍ የሚችለው ፣ የፍጡር ሕግ በሆነ ባንዱ ስሕተ
ትና ስሕተቱ በሚያስከትለው ውድቀት ነው ። በራስ ዐሊ የንቀት
ስሕተት ማሸነፍን ያገኙት ቴዎድሮስ ፣ በተራቸው የፈረንጆችን
ኃይል በመናቅ ስሕተት ራሳቸው ተሸንፈዋል ። ፈረንጆችም በተ
ራቸው እርስ በርሳቸው ሲተላለሉ ፣ ወይም በሌላው ሲታለሉ ኖረ
ዋል ። በዚህ ምክንያት ነው ፣ በዓለም የገነኑ የቄሣሮች አገዛዝ
እየተለዋወጠ መጥቶ በመጨረሻ አለንበት ደንገዝገዝ ካለው
ዓለም ጋር የተገናኘነው ።

ባሁኑ ዘመን ያለነው ፣ ያለፈውን ታሪክ ስናነብ ዐፄ ቴዎድ
ሮስ ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ፣ ስለ ማዕከላዊው መንግሥት ግን
ባታ እንደ መነሣታቸው መጠን ፣ የርሳቸውን መሸነፍ ፣ ያገር
ከፋፋዮችን መሳፍንት አሸናፊነት እንደማንመኝ የታወቀ ነው ።
ቴዎድሮስ ተሸንፈው መሳፍንቱ አሸንፈው ቢሆን ኖሮ ፣ ምንም
እንኳን በልዩ ልዩ ሰበብ አገሪቱን አልምተን በሀብቷ መጠቀምን
ባናውቅበት ፣ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ባሁኑ ወርድና ቁመቷ ከነ
ሀብቷ አናገኛትም ነበር ። በዚህ ፈንታ ፣ ሁሉም በየቤቱ 'ማን
ከማን ያንሳል ፣ አሻፈረኝ' እያለ እርስ በርሱ ሲዋጋ ለቅኝ ገዥ
ዎች ጥርጊያ ጐዳና ይከፍት ነበር ። ከቴዎድሮስ በኋላ የተከታተ
ሉት ዮሐንስም ፣ ምኒልክም ፣ ራሳቸው በሥልጣን ተደላድለው ፣
በሌሎቹ አውራጃዎች ላይ መጠናከርን ያገኙት ፣ በቅድሚያ የዳን
ዴዎችን መሳፍንት ቅስም ቴዎድሮስ ሰባብረው ፣ የመከፋፈሉን
መርዝ ከነቀሉላቸው በኋላ በመሆኑ ነው ። ቴዎድሮስ የጠረጉት
ያንድነት ጐዳና ለተከታዮቻቸው ቀለል ያለ የመንደርደሪያ መስክ
ሆኗል ማለት ነው ።

እላይ እንዳልነው ፣ መሳፍንቱ ቀድሞ በኅብረት እርሳቸውን
ለመቃወም ባሳዩት የንቀት ስሕተት ፣ እርሳቸውም የውጭውን
ኃይል በመናቅ የቅጣት እጃቸውን ካገራቸው ሰው ላይ አሳልፈው
ከውጭ አገር ሚሲዮናውያንና ከቆንሲል ላይ በማሳረፍ ፣ እነር
ሱን ሳስር ፣ የነርሱ የመንግሥት ኃይል ሊያጠቃኝ ይችላል የሚ
ለው አሳብ በብዙ ረገድ ብልሀነት ይታይበት ከነበረው አዕምሮ
አቸው እንደ ምን እንደ ተሰወረ ለአንባቢ ግር ይላል ። የጉልበታ
ቸው መጠን በትክክል የገባቸው ፣ ከእሮጌ ጦርነትና ከነገብርዬ



ውድቀት በኋላ ፣ እጃቸውን እንዲሰጡ ናፒዬር ያፈጠጠ ጊዜ
መሆኑን ወደፊት በዚሁ ምዕራፍ የሰፈሩት ሠነዶች በግልጽ
ያመለክታሉ ።

የሆነ ሆኖ ፣ ይኸን ከመሰለው ፈተና ለመውጣት በበላይ
አስተዳዳሪ ላይ የሚደርሰውን ውዝግብ በትዕግሥት ተሸክመው
ለማሸነፍ ፣ የአካባቢውና የወቅቱ ሁኔታ ሳይፈቅድላቸው ቀርቶ
ለከፍተኛ ችግር ቢዳረጉም ፣ ያስቀመጡት የብሔራዊ አንድነት
የመሠረት ደንጊያ የማዕዘን ራስ ሆኖ ፣ ባለፈው እንዳልነው ለተከ
ታዮቻቸው ለነዐፄ ዮሐንስ ፣ ለነዐፄ ምኒልክ ያስተዳደር ዘመን
ጥርጊያ ጐዳና በመክፈት አገልግሏል ።

በብዙ ሰው ላይ ፣ በውጭ አገር ሰዎችና በዘመዶቻቸው በነጋ
ረድ ላይ ቆራጥ አቋም እንደ ወሰዱ ሁሉ ፣ በመጨረሻይቱ ሰዓት
በምርኮኛ ላይ የሚደርሰውን ውርደት ላለመቀበል ሲሉ ፣ በራሳቸ
ውም ሕይወት ላይ የማያወላውል ውሳኔ ሰጥተዋል ። በዚህም
አድራጐታቸው ፣ ለሕዝባቸው የዠግንነትና የኩራት ቅርስ ሲያወ
ርሱ ፣ በተለይ በጠላቶቻቸው በእንግሊዞችና በጠቅላላው በውጭ
አገር ሰዎች ዘንድ መገረምን አሳድረው ፣ የወደፊት ታሪካቸውን
ተደናቂ እንዲሆን አድርገውታል ።

ዐፄ ቴዎድሮስ በዘመነ መንግሥታቸው በታላቅ የቤተ መን
ግሥት ሕንፃ ፣ ባማረ አዳራሽ ተቀምጠው ፣ ዘውድ ደፍተው ፣
በትረ መንግሥት ጨብጠው ፣ በዙፋን ላይ ተንሠራፍተው ፣ በወ
ርቅ አልጋና በሚደላ ፍራሽ ላይ ተጋድመው ፣ የዚህን ዓለም ንጉ
ሣዊ አዱኛ ማጣጣም ሳያምራቸው ፣ ለራሳቸው ባርኔጣ ፣ ለእግራ
ቸው ጫማ ሳይፈልጉ ፣ ያለ ምንም ዕረፍትና መዝናናት በድንኳን
እየኖሩ ፣ በከብት ጀርባና በእግራቸው ከአውራጃ ወደ አውራጃ
በመዘዋወር ፣ ዳገት ቁልቁለቱን ሸለቆና ወንዛ ወንዙን በማቋ
ረጥ ፣ ቆንጥር ለቆንጥር በክረምትና በበጋ በመንከራተት እየታ
ገሉ ፣ አዲሱን የመሬት ሥሪትና የማዕከላዊ መንግሥትን አቋም
ለማሳመን ፣ ከመሳፍንትና ከካህናት ጋር በመከራከር ፣ የውጭ
አገር ባለሙያዎች ያገራቸውን ሰው እንዲያሠለጥኑላቸው በመ
ጨቃጨቅ ፣ ጉልበታቸውንም አዕምሮአቸውንም ፣ በመጨረሻ ሕይ
ወታቸውንም ፣ ሙሉ በሙሉ ለሚወዷት አገራቸው ለኢትዮጵያ

የሥልጣኔና የአንድነት ሕይወት ሠውተዋል ። የኢትዮጵያን አንድነትና ውሕደት የሚወድ ያሁኑም ፣ የወደፊቱም ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይኸን ውለታ ተገንዝቦ ፣ የኛህን ንጉሥ ስማቸውን በአክብሮትና በአድናቆት ሊዘከረው ይገባል ።

መስከረም 1 ቀን 1981

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ



## ማ መ ል ከ ቻ

በዘመኑ የተሟላ ይመስለኝ የነበረው ፣ በወጣትነት ጊዜዬ በ1934 — 1935 ዓ. ም. ያዘጋጀሁት ፣ «ካዔ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ» የሚባለው የኢትዮጵያ ታሪክ ፣ ዕድሜ ከንባብ ጋር በጨማመርሁ መጠን ፣ ያለመሟላቱ እየገባኝ ሔደ ። ከሰው ልጅ የደካማነት ጠባዩ አንዱ ፣ በተለይ በቴክኒክና በጽሕፈት የነጻነት መብት ወደኋላ ቀር በሆነው አገር ውስጥ ሲሆን ፣ ባንድ ጊዜ እንኳ ባይቻል በተቀራረበ አጫጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ሥራ ለማከናወን አለመቻሉ ነው ።

ስለዚህ ፣ በዚሁ የመዠመሪያ መጽሐፌ ላይ ብቻ እያጧላሁ ለመሥራት እንዳላተኩር ፣ ካዔ ቴዎድሮስ በፊት ያለውን የረዥም ዘመን የኢትዮጵያን ታሪክ በመጠነኛ ደረጃም ቢሆን ማከታተሉና ማሟላቱ ፣ ለአንባቢ ጠቅላላ ያገሩን ታሪክ ማሳወቅ የበለጠ የሚጠቅም መስሎ ታየኝ ። ይኸንንም እንደ ተቻለ አገባድጄ ፣ በአራት ቅጽ እንዳሳተምሁ ፣ ወደ መዠመሪያው መጽሐፌ አሳቤን መልሼ እንዳላሟላ ፣ አዲሱ የሱማልያ መንግሥት ነጻ መንግሥትነቱን ካቋቋመ በኋላ ፣ በኢትዮጵያ ላይ የሚያቀርበው የግዛት ጥያቄው ፣ ዛቻውና ድንፋታው ፣ የወሰን ላይ ግጭቱም እየተፋፋመ ስለሔደ ፣ ከሁሉ በፊት ከአራት መቶ ዓመት በፊት ከዚሁ ከሱማሌና ከሐረር አካባቢ ተነሥቶ በኢትዮጵያ ላይ ብዙ ጥፋት ያደረሰውን ፣ የግራኝ አህመድ ወረራን አስቀድሞ በመጽሐፍ መልክ ማቅረቡ ፣ ያሁኑን መንግሥትና ሕዝብ ሊያስጠነቅቅ ይችላል በሚል ግምት ፣ ከ1952 እስከ 1961 ዓ. ም. እስራኤልና ዩጎስላቪያ በነበርሁባቸው ጊዜዎች ውስጥ ፣ ከደንበኛው ሥራዬና ከዕረፍቴ የተረፈኝን ጊዜዬን ለዚሁ ሥራ መሠዋት ፈቀድሁ ።

የጽሕፈቱን ሥራ ጨርሼ ከቤልግሬድ በ1961 ዓ. ም. ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለስሁ ፣ የመጽሐፉ እትማት (አንባቢ በግይስተው) በየምክንያቱ ዘግይቶ ፣ በ1965 ዓ. ም. በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ተዠምሮ ፣ የየካቲት ንቅናቄ በዠመረበት ዓመት

በ1966 ዓ. ም. ተጠርዞ ወጣ ። እንደ ወጣ ግን ፣ እንደ ጠበቅሁትና እንደ ተመኘሁት በቶሎ የመበተንን ዕድል ሳያገኝ ፣ ከለውጡ በኋላ በልዩ ልዩ ሰበብ እመጋዘን እንደ ተቀመጠ ፣ በዚህ መካከል እኔም በ1967 ዓ. ም. ወደ ጡረታ የመገለል ዕድል ገጠመኝ ። አሳቤንም ሁሉ ፣ ከዚህ በፊት ወዳሳተምሁት መለስሁ ። በተለይ ለኢትዮጵያ መከፋፈል ምክንያት የሆነው የዘመነ መሳፍንት አገዛዝ ወድቆ ፣ አዲስ የማዕከላዊ መንግሥት መቆም ከጀመረበት ካፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ያለውን ፣ ከዚህ በፊት ባጭሩ የጻፍሁትን እያሟላሁ ለመሥራት በቂ ጊዜ ለማግኘት ቻልሁ ።

ይኸንንም ፣ ከዚህ በፊት በግል ባጠራቀምሁዋቸው ሠነዶች እየተጠቀምሁ ፣ በቤቴ በምሠራበት ጊዜና በእጅ የጻፍሁትንም በመኪና የሚመታልኝ እያጣሁ በተቸገርሁበት ወቅት ፣ ሳላስበው ፣ ያን ጊዜ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዋና ጸሐፊ ወደ ነበሩት ወደ ጓድ ፍቅረ ሥላሴ ወግደረስ ጽሕፈት ቤት ተጠርቼ ፣ እንደኛ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት መጋዘን ተከማችቶ እንደዚሁ በመቀመጥ ሥራ ፈትቶ የነበረው ፣ የግራኝ አህመድ የወረራ መጽሐፍ ፣ በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት በኩል ሕዝብ ሊያነበው እንዲችል በቀላል ዋጋ እንዲሸጥ መወሰኑን ፤ ቀጥሎም በዚያው ሰዓት ለማዘጋጀው መጽሐፍ የጐደሉ ሠነዶች ቢኖሩ ፣ እነርሱን ለመሰብሰብ ወደ ውጭ አገር ብሔድ መንግሥት ለዚሁ ጠቃሚና ታሪካዊ ዝግጅት ፣ በጥናት መልክ ከቀረበ ፣ ወጭውን እንደሚችል ነገሩኝ ። መንግሥት የሚያደርግልኝን የደጋፊነት አሳብ በምስጋና ተቀብዬ ፣ የኢትዮጵያ ሠነዶች በይበልጥ ወደሚገኙባቸው ወደ ሮማ ፣ ፓሪስ ፣ ሎንዶን ሔጄ ፣ ጊዜው ከማጠሩ የተነሣ ድካም ቢጨምርም ፣ በተመደበው የአራት ወራት ጊዜ ውስጥ የቻልሁትን ያህል ለታሪኩ ጽሑፍ ጠቃሚነት ያላቸውን ሠነዶች ሰብስቤ ተመለስሁ ።

እንደ ተመለስሁም ፣ ቀድሞ የሠራሁትን በማፍረስ እንደገና እያሟላሁ በመጻፍ ፣ እነሆ አሁን «ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት» በሚል አርዕስት ተዘጋጅቶ ለአንባቢ የቀረበው ይኸ መጽሐፍ ሲሆን ፣ በውስጡ ያፄ ቴዎድሮስ አነሣሣቸው ፣ ማዕከላዊ መንግሥት ለመገንባት የደረሰባቸው የውጣ ውረድ ድካም ፣ በመጨረሻም ከእንግሊዞች ጋር ያደረጉት ጦርነትና የዘመናቸው ፍጻሜ ይገኝበታል ።



## ያሁኑ መጽሐፍ የተጻፈበት ሥልት

እንደ ማናቸውም የታሪክ መጽሐፍ ፣ ለዚህ ከመቶ ዓመት በላይ ላለፈውና በሕይወተ ሥጋ ላልነበርንበት ያፄ ቴዎድሮስ ታሪክ መሠረት የሆኑት ፣ በመጽሐፉ መጨረሻ የተዘረዘሩት አብዛኞቹ ያይን ምስክር ከሆኑት ካገር ተወላጆችና ከውጭ አገር ዜጎች በወቅቱ የተዘጋጁት መጻሕፍት ናቸው ። እነርሱንም ፣ በደፈናውና በቀላሉ ዝርዝራቸውን ብቻ ከማስቀመጥ ዐልፌን ፣ በየምዕራፍ ከፋፍለን ካሰፈርነው ጽሑፍ ጋር በቀላሉ አንባቢ አገናኝቶ ፣ የተባለውንና የተደረገውን ሁሉ ሊያመዛዝንባቸው እንደሚችል ፣ በየገጹ ግርጌ የምዕራፋቸውና የገጻቸው ቁጥር ለምስክርነት ተመልክቷል ።

ከዚህም ጋር የታሪክ ድርጊቶችን ፣ ጊዜዎችን ፣ የጉዞ መሥመሮችን ፣ የጦርነት ቦታዎችን ፣ በውጭ አገር ጽሑፎች ውስጥ ያጋጠሙንን ታሪካውያን ሥዕሎችን ሰብስበን ከታሪኩ ጽሑፍ ከማዛመድ ጋር ፣ የሁለቱን ዜጎች ደራስያን አባባል በቀጥታ ካሰፈርን በኋላ ፣ ጥሬ አሳቡን ለማለዘብና በዛሬው ዘመን አባባላችን ፣ ለዛሬው ዘመን አንባቢ አብራርቶ ለማቅረብ ሞክረናል ።

ከማናቸውም ጠባብ ብሔረተኝነት ፍጹም ነጻ የሆኑትን ጸሐፊና አንባቢ ሳያጣላ ፣ በቁም ነገር አዛምዶ ለዘለቄታ በስምምነት አብሮ ለማኖር የሚያስችለው ያጻጻፍ ዘዴ ከዚህ መሥመር ውጭ ሊሆን አይችልም ።

# ም ስ ጋ ና

1. በአውሮፓ በተለይ በሮማ ፣ በኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር "Archivio Storico de' Soppressi Ministero dell' Africa Italiana" የሚባለውንና የቫቲካንን ቤተ መጻሕፍት

2. በፈረንሣይ አገር፣ Ministère des Affaires Etrangères Menoir et documents Afrique የሚባለውን ፤

3. በእንግሊዝ አገር ፣ ኪው ጋርድን በሚገኘው India Office እና በ Public Record Office

   ለሠነድ ፍለጋ በተሠማራሁበት ጊዜ፣ስለ ሹማምንቱ ቅን አመራርና አቀባበል፣ስለ ሠራተኞቹ የማያቋርጥ አገልግሎት ምሲጋናዬን ከማቅረብ ጋር ፣ አንዳንዶቹ አብያተ መጻሕፍት እንኳን ሠነድ ያለበትን ጽሑፍ፣ ሠነዱ የሔደበትን አንቬሎፕ እስከ ማስቀመጥ መድረሳቸው የሚደነቅና የሚመሰገን ነው ።

   በዚሁ ጊዜ በሮማ፣ፕሮፌሰር ላንፍራንኮ ሪቺ፣በሎንዶን ፣ ዶክተር ሪቻርድ ፓንክረስት ከሹማምንቱ ጋር በማስተዋወቅ ረገድ ያደረጉልኝ እርዳታ ሊዘነጋኝ አይችልም ።

4. ወዳገር ከተመለስሁ በኋላ፣ይህንን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ፣ የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር በተለይም ፣ በሚኒስትሩ በጓድ ግርማ ይልማ ፈቃድ የጸፍሁትን ምዕራፍ እያነበበ፣የቃላት ቀውስ የፊደል ግድፈት እንዳይኖር እየተጠባበቀ ፣ በማረም የረዳኝን አቶ ጥዑመ ልሳን ኃይሉን ፣ በሚኒስቴሩ ውስጥ በፎቶግራፍ ክፍል እነ አቶ ላቀው ፋንታዬ ለመጽሐፉ የሚያገለግሉትን ሥዕሎችና ፎቶግራፎች እያነሡ በመስጠት ፣ ከብሔራዊ

ቤተ መጻሕፍት አዳራሽና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለጥቅስ የፈለግሁዋቸውን መጻሕፍት በማቅረብ የረዱኝን ፣ ከኢትዮጵያ የካርታ ድርጅት አስቀድሞ በደረቅ እርሳስ ባመለከትሁት መንገድ ካርታዎቹን በደንብ እየሠራ ያቀረበልኝን አቶ ዳንኤል ሲይፉን ፣ በመጨረሻም በእጅ የጻፍሁትን በመኪና በመምታት የረዳችኝን ወይዘሪት እታፈራሁ ከንፈን ከልብ አመሰግናለሁ ።

ተ. ጸ. መ.



# ክፍል አንድ

## የዐፄ ቴዎድሮስ የወጣትነትና የሽፍትነት ዘመን

# ምዕራፍ አንድ

## የደምቢያና የወሎ መሳፍንት ፍልሚያ በጐንደር መንግሥት ውስጥ

የኢትዮጵያን መከፋፈል ለማስቀረትና ሀገሪቱን አንድ ለማድረግ፣ከፍተኛ ጥረት ያደረጉትን የዐፄ ቴዎድሮስን አነሣሥና አወዳደቅ ከመመልከታችን በፊት፣ የርሳቸው ወገኖች የሆኑትን፣ የቋረኞችን ሁኔታ አስቀድሞ መመልከቱ የታሪኩን አመጣጥ ለመገንዘብ ይጠቅማል ። ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው በፊት ፣ ማንም እንደሚያውቀው ፣ መጠሪያ ስማቸው ካሣ ነበር ። ከሌላ ጋር በሞግሼነት እንዳያደናግር ፣ በትውልድ ወረዳቸው በቋራ ፣ 'ቋረኛው' ካሣ እየተባሉ ይጠሩ ነበር ። ቋራ የሚገኘው ፣ በቤጌምድር አውራጃ በደምቢያ ውስጥ ነው ።የዚህ ክፍል ተወላጆች 'ቋረኞች' እየተባሉ በጐንደር መንግሥት ከዐፄ በካፋ ሞት ወዲህ ብዙ ሚና ተጫውተዋል ። አጭር ታሪኩ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

በካፋ በ1686 ዓ. ም. ተወልደው ፣ በ1713 ዓ. ም. ስመ መንግሥታቸው 'መሢህ ሰገድ' ተብሎ ከነገሡ በኋላ ፣ በ1715 ዓ. ም. ከቋራ ባላባቶች ከደጃች መንበርና ከወይዘሮ እንኮዩ የሚወለዱትን ፣ ቁንጅናቸውን እነጂምስ ብሩስ ያደነቁትን ወይዘሮ ምንትዋብን አገቡ ። ከዚሁ ጋብቻ ፣ ስመ መንግሥታቸው 'ብርሃን ሰገድ' የተባለው ዳግማዊ ኢያሱ ፣ በ1715 በሰኔ 12 ቀን ተወለዱ ። በካፋና ምንትዋብ 8 ዓመት ያህል አብረው እንደ ተቀመጡ ፣ በመስከረም 11 ቀን 1723 ዓ. ም. ባልዮው ዐፄ በካፋ ስለ ሞቱ፣የስምንቱ ዓመት ወጣት ኢያሱ ነገሡ።ምንም ለስሙ ኢያሱ ቢነግሡ ፣ እናትዮዋ እቴጌ ምንትዋብ በመልክ ውበት ብቻ ሳይሆን በማስተዳደር ዕውቀትም፣ችሎታም አሟልተው የያዙ በመሆናቸው በልጃቸው ጐን ሆነው ፣ ንግሥት ተብለው የጐንደርን መንግሥት ይመሩ ዠመር ።([1])

---

1 Annales.....(Regume Iyasu II et Ignatius Guidi pp, 20—39

ከእቴጌነታቸው በላይ በንግሥትነት በነገሡበት ቀን ምንትዋብ የወርቅ አክሊል ደፍተው ፣ የወርቅ ጫማ ተጫምተው ፣ በደንብ ተጊያጊጠው ፣ ጎማ በተባለው በቅሏቸው ላይ ሆነው በአደባባይ ሲያልፉ ፣ በዘመኑ ያማርኛ አገጣጥም ፣

«አሁን ወጻች ዝምበር ፣ ተሸሽጋ ነበር ።
አሁን ወጻች ጨረቃ ፣ የምትለን ፍርድ ይብቃ
ደስ ይበልህ ዘመድ ፣ ከነገሡች በዘውድ
ደስ ይበልህ ባለጌ (*) ፣ ከነገሡች ይተጌ
ደስ ይበልህ ጐንደር ፣ ቀድሞ ከፍቶህ ነበር»

እያለ ወንዱም ሴቱም ሲዘፍን ፣ ካህናቱም በበኩላቸው ፣

«መንክር ገርግ ፣ መንክር ገርግ
ወልደ ልዑል ጸለላ መንክር ገርግ»

እያሉ በወረብ አሸብሸበዋል ። (1)

ኢያሱ በዕድሜ ከፍ ብለው ሥልጣን በጨበጡበትም ጊዜ ፣ እናትና ልጁ በሥልጣን ሽሚያ ሰምና እሳት ሳይሆኑ ፣ ሰምና ወርቅ ሆነው ፣ በፍቅር በስምምነት ፣ በኅብረት አብረው ሲገዙ ቆዩ ። በሴትዮዋ ምክንያት ፣ ገና ቀደም ብለው በበካፋ ዘመን የሴትዮዋ ዘመድ አዝማዶች ከቋራ እየመጡ በየሥልጣኑ ገብተው ተሠገሡጉ ። የኢያታቸው የወይዘሮ ዮልያና ወንድም ፣ ደጃዝማች ኒቆላዎስ የራስነት ማዕረግ ተጨምሮ የስሜን ገዥ ሆነው ከቆዩ በኋላ ፣ ቢትወደድነት ጨምረው እንደራሴ ሆኑ ። (2) ወንድሞው ራስ ወልደ ልዑል ፣ ካህናቱ በወረቡ ላይ «ወልደ ልዑል ጸለላ» እያሉ ስሙን የጠቀሱት ፣ ለእኅትዮዋ መንግሥት ጣራም ግድግዳም ሆኖ ፣ ከሹመት ወደ ሹመት ሲዘዋወር ቆይቶ ፣ በመጨረሻ ከራስ ኒቆላዎስ ሞት በኋላ ፣ ራስ ተብሎ የእንደራሴነቱን ሥፍራ የያዘ ነው ። (3) እነ ራስ ኢልያስ ፣ እነ ማሞ ተንሜ ሸፍተው ፣

---

* ባለጌ ማለት ባላገር ማለት ነው ፣ ይተጌ ማለትም በዛሬ አነጋገር እቴጌ ማለት ነው ።

1 Annales ...... pp. 40—41

2 Idem ...... pp. 46, 48

3 Idem ...... pp. 75, 81



ሕዝቅያስ የሚባል የነጋሢነት ዘር ያለውን ከወህኒ አምባ አውጥተው ፣ በኢያሱ ፋንታ ለማንገሥ ቤተ መንግሥቱን ከበው ውጊያው በከበደበት ሰዓት ፣ ለመሸሽ ያቆበቆበውን ወታደር ፣ «ባለሁ ቁም ጐልማሳ! እኔ የወንዶች ወንድ መሆኔን ከተማው ያውቃል» ብሎ በፉከራው ያረጋጋ ፣ ራሱም «ለምድር ቃል ይሁን ፣ እንቺ ካልሸሸሽ እኔ እንዳልሸሽ» ብሎ ፣ በመፎከር ለውጊያ ከቆመባት መሬት ጋር ቃል ኪዳን የተጋባ ፣ ታላቅ የገድግና ወንድም ነው ። (1) ከዚህ ድል በኋላ ፣ የኢያሱና የንግሥት ምንትዋብ መንግሥት ጸና ። ወልደ ልዑልም ከዚህ በኋላ ነው—ቢትወደድ ሲባል ቆይቶ ራስ ተብሎ የመንግሥቱ እንደራሴ የሆነው ። የማዕዙ ዜና መዋዕል ይኸን ሰው አንድ ጊዜ 'መልአከ ምክር' ፣ ሌላ ጊዜ 'መልአከ ሠራዊት' ይለዋል ። (2)

ከራስ ወልደ ልዑል በቀር ፣ የንግሥት ምንትዋብ ዘመድ አዝማድ የራስ ኒቆላዎስ ወንድም አዛዥ ደኔ ፣ የአዛዥ ደኔ ልጅ ደጃች ማሞ ፣ የኢያታቸው የወይዘሮ ዮልያና እኅት የወይዘሮ ሱብሌና የአቤቶ መርቆርዮስ ልጆች ደጃች አውሳብዮስ ፣ ደጃች አዮ ፣ ደጃች እሸቴ(3) ፣ የንግሥት ምንትዋብ እኅስት የወይዘሮ ማሚት ልጆች ፣ ደጃች አደሩና አዛዥ ልዑለ ቃል ፣ አሳላፊ ቀጸላ ሌሎችም በጐንደር ቤተ መንግሥት በየሥልጣኑ በብዛት ማስተዳደር ስለያዙ ፣ መንግሥቱ ራሱ 'የቋረኞች መንግሥት' እየተባለ ይጠራ ዠመር ። ነገር ግን ፣ ምንም እንኳን አብዛኛውን ያስተዳደር ቦታ ቢይዙም ፣ በአገው ምድርና በዳሞት ደጃች ወሬኛ ፣ በአማራ አገር ራስ ወዳጆ ፣ በቤጌምድር ደጃች የማርያም ባሪያ ፣ በትግሬ ደጃች ስሑል ሚካኤል ፣ በጐጃም ደጃች ዮሴዴቅ ጣልቃ እየገቡ ፣ ቢጋርዮሽ በየክፍለ አገራቸው እየተሾሙ ማስተዳደራቸው አልቀረም ።

---

1 Annales ...... pp. 66

2 መልአከ ሠራዊት ራስ ወልደ ልዑል ፣ ዓቢየ ምክር ወጽኑዕ ኃይል እስመ አልቦ ዘይመስሉ (158—159)

3 ደጃች እሸቴ የወ/ሮ ኢያሱ አድያም ሰገድ ልጅ ፣ ወይዘሮ ወለተ ሩፋኤልን አግብተው ደጃች ኃይሉን ይወልዳሉ ። ኃይሉ ማኅደረ ማርያም በግዞት የነበሩ ጊዜ የኢትዮጵያ ታሪክ እንዳይጠፋ ፣ ከየገዳማቱ አሰባስበው በማጻፍ ፣ ወደ ጊዜያችን ያደረሱ የመጀመሪያው ምሁር ናቸው ። የኢትዮጵያ ታሪክ ዓፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል, ገጽ 13 — 15

ከዐፄ ፋሲልና ከታላቁ ኢያሱ ወዲህ ፣ አሁንም በንግሥት ምንትዋብና በልጃቸው በኢያሱ ብርሃን ሰገድ ዘመነ መንግሥት (1723 — 1747) ዓ. ም. የጐንደር ከተማ ፣ ባዳዲስ ሕንፃና በአትክልት እያሸበረቀ በቤተ መንግሥቱም ለግብር ሠንጋው ፣ ሙክቱ እየታረደ ፣ ከጠላና ከጠጅ ዐልፎ ወይን ጠጅ እንደ ውሃ የተጠጣበት ፣ ተድላ ደስታ የታየበት ጊዜ ስለ ነበረ ዘመኑ ራሱ ፣ 'የቋረኞች የአዱኛ ዘመን' ተባለ ።

ንግሥት ምንትዋብም ፣ በወጣትነታቸው ጊዜ ባለቤታቸው ዐፄ በካፋ ስለሞቱ ፣ ባገራችን የቤት ንግሥት ባል እንዳታገባ ሁኔታው ስለማያመች ፣ ኢያሱ የሚባለውን ፣ የዐፄ በካፋን የእኅት ልጅ አስቀምጠው ፣ ከዚሁ ሰውዬ አስቴር ፣ አልጣሽ ፣ ወለተ እሥራኤል የሚባሉ ሦስት ቆነጃጅት ወልደው ፣ አስቴር በፊት ለቤጌምድሩ ባላባት ለደጃች አዮ ልጅ ፣ ለደጃች የማርያም ባሪያ በኋላም ለደጃች ሚካኤል ስሑል ፣ አልጣሽ ለልጅዬው ለበዥሮንድ ተክለ ሃይማኖት ፣ ወለተ እሥራኤል ለጐጃሙ ባላባት ለደጃች ዮሴዴቅ ተድረው ፣ የየአውራጃውንም ባላባቶች በጋብቻ መያዝ ፈልገው ነበር ። ደጃች ዮሴዴቅ ከወለተ እስራኤል ታላቅ ራስ ኃይሉን ስለ ወለዱ ፣ በሙሉ የጐጃም መሳፍንትና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የታላቅ ራስ ኃይሉ ተወላጆች ናቸው ።

ልክ በእንግሊዝ አገር ፣ ንግሥት ቪክቶሪያ በ1840 መስፍኑን አልቤርን አግብተው ባላቸው በ1861 ሞቶ ብቻቸውን በነበሩበት ሰዓት ፣ ጆን ብራውን የሚባለውን የልፍኝ አሽከራቸውን 'እንደ ባል ይዘዋል' እየተባሉ በሚታሙበት ሰዓት ፣ አንዳንዱም ለማናደድ እያለ እመት ብራውን «እያለ» ያሾፍ እንደነበረ (1)፣ በኢትዮጵያም ፣ ሕዝቡ የንግሥቲቱንና የኢያሱን ውስጠ ግንኙነት እየሰማ ፣ «ከባላቸው ዘመድ ማገጡ ፣ ወለዱ» እያለ እያማ ፣ ኢያሱንም «ምልምል ኢያሱ» እያለ ማፌዝ ስለ አበዛባቸው ፣ ይኸን ያስቀሩ መስሏቸው ፣ በንግሥቲቱ ፈቃድ የግራዝማችነት ማዕረግ ለኢያሱ ተሰጥቶት ነበር ። ማገቡ በዚሁ በግራዝማችነት ሲጠራው ፣ ሌላው በውጭ ያለው ቤገምድሬ

1- Historia No. 350 Janifier, les petits secrets de Victoria C.A Hibert pp. 63—66.



ግን ፣ አዲሱን የማዕረጉን ስም ወደ ጐን እየተወ ፣ «ምልምል ኢያሱ» በማለት ጸና ። ይሁን እንጂ ፣ ንግሥት ምንትዋብ ከወገኖቻቸው ከቋረኞች ጋር በዚህ ዐይነት ተድላ ደስታ ሲኖሩ ፣ በመጨረሻ ተድላ ደስታ እየሸሸ የዚያኑ ያህል ሐዘን በሐዘን ላይ እየተከታተለ ደረሰባቸው ። የንግሥቲቱ ወዳጅ «ምልምል ኢያሱ» በ1735 ዓ. ም. ሞተ ። (1) ወደ ባሕር ገፍተው በመጣል የገደሉት ንጉሥ ኢያሱ ናቸው ተብሎ ተወራ ። በ1747 ዓ. ም. ንጉሥ ኢያሱ ሞቱ ። መርዝ ከመብል ጋር አብልታ ንጉሡን የገደለቻቸው የሟቹ የምልምል ኢያሱ እኅት ነች ተባለ ።

የሆነ ሆኖ ፣ እቴጌ ምንትዋብ በስውር የምልምል ኢያሱ ሞት ቢቆጫቸውም በይፋ ግን ፣ ታላቅ ሐዘን ተሰምቷቸው አምርረው ያለቀሱት ስለ ልጃቸው መሆኑን ፤ በሥርዓተ ቀብሩም ላይ በዘመኑ የለቅሶ ግጥም ፣

«አያ በሰቀላህ ውሃ መላ ፣ በሰቀላህ ውሃ መላ
የተራበ ዘመድ እንዳይበላ ፣ በሰቀላህ ውሃ መላ
ወይ እርሱ ሳለ ቀሊል ኢያሱ ለጋሡ
አንተ የወፍላ ንጉሡ»

እየተባለ መለቀሱን ዜና መዕዋሉ ያመለክታል ።(*)

ከዚሁ ተከታትሎ ፣ እናታቸው ወይዘሮ እንኮዬ በ1750 ፣ ወንድማቸው ራስ ወልደ ልዑል መጋቢት 20 ቀን በ1759 ዓ. ም. በጣም የሚያፈቅሩዋቸው ያክስታቸው ልጆች ፣ ደጃች እሸቴና ደጃች አውሳብዮስ በ1760 ዓ. ም. ፣ በዳሞት ከኦሮሞዎች ጋር ሲዋጉ ሁለቱም ባንድ ቀን ጦርነት ሞቱ ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በንግሥት ምንትዋብና በቋረኞች ላይ መከራና ሐሣር እየተከታተለ መጣ ። የዚህም ምክንያት እንደዚህ ነው ።

1 Annales.........pp. 168—169

* በሰቀላህ ውሃ መላ ማለት ፣ በዛሬ አነጋገር በአዳራሽህ ግብር ገብቶ ሕዝቡ እንዳይበላበት ሰዉ እየተላቀሰ የእንባ ውሃ መላበት ማለት ነው ። ቀሊል የተባለውም በየዜና መዋዕላቸው ነገሥታት ቀሊል ከሙ ንስር ፣ ጽኑዕ ከሙ አንበሳ ይባላሉ ። ወፍላን አልታሽ ያንግችው ላስቶችና ዋጅራቶች የሸፈቱ ጊዜ ኢያሱ በፍጥነት ሔደው ተዋግተው የነበረውን ለማውሳት ነው ።

ዐፄ ኢያሱ በሕይወታቸው ሳሉ ፣ በሚስትነት ያገቡዋቸው ውቢት የሚባሉትን የወሎ የኦሮሞ ባላባት ልጅ ነበር ። በሞቱበት ጊዜ በዙፋን የተከተሏቸው ከውቢት (ወለተ ቤርሳቤህ) የተወለዱት ልጃቸው ኢዮአስ ናቸው ። ስለዚህ ልክ እንደ ዚያው በንግሥት ምንትዋብና በልጃቸው በዐፄ ኢያሱ ጊዜ እንደ ሆነው ፣ ኢዮአስ የአያታቸውን የንግሥት ምንትዋብን ወገኖች ቋረኞችን ችላ እያሉ ፣ የእናታቸውን የውቢትን ወገኖች ከወሎ እያስመጡ ማቀራረብና ባለሟል ማድረግ ዠመሩ ። የእናታቸውን የውቢትን ወንድሞች ፣ ሉቦንና ብርሌን አምጥተው ፣ ሉቦን እንደ እንደራሴ ባጠገባቸው አስቀምጠው ፣ ለብርሌ የደጃዝማችነት ማዕረግ ጨምረው እስከዚህ ጊዜ ድረስ ከቋረኞች እጅ ወጥቶ የማያውቀውን የቤገምድርን ግዛት ሰጡት ።

በዚህ ጊዜ በወሎዎቹና በቋረኞቹ መካከል የሹመትና የሥልጣን ፍልሚያ ተነሣ ። ፍልሚያው በግድ ወደ ጥላቻ ፣ ጥላቻው ወደ ጦርነት በየወቅቱ እየዞረ ፣ በንጉሡ ባዬ ኢዮአስ መመቾት ፣ ወሎዎች አጥቂዎች ፣ ቋረኞቹ ተጠቂዎች ሆኑ ። ንግሥት ምንትዋብም ፣ በልጃቸው ጊዜ እንደ ገዙ በልጅ ልጃቸውም ዘመን በሥልጣን ለመቀጠል ሞክረው ሳለ ፣ ኢዮአስ ለእናታቸው ፊት እየሰጡ ለአያታቸው ፣ 'እንግዲህ በቃሽ ! አሁን ተራው የናቴ ነው' በሚል ስሜት ፊት ነሷቸው ፤ በዚህም ላይ ዕድሜያቸው ከስድሳ ዐልፎ ወደ እርጅና ስለ አዘነበለ ፣ የነገሩን አዝማሚያ አይተው ፣ ሁሉንም ትተው ወዳሠሩት ቤተ ክርስቲያን ወደ ቁስቋም ሔደው ፣ በጾም በጸሎት ተቀመጡ ።[1]

በወሎዎች ሥልጣን አያያዝ ተቀይሞ የሸፈተው ፣ የታወቀው የቤገምድሩ ባላባትና የንግሥት ምንትዋብ አማች የነበረው ፣ የስመ ጥሩው የደጃች አዮ ልጅ ደጃዝማች የማርያም ባሪያ ፣ በቤገምድር ሸፍቶ አዲስ ከተሾመው ከብርሌ ጋር ተዋግቶ ገደለው ። በሌላ ቀን ንጉሡና ሉቦ ዘምተውበት ከተማረከ በኋላ ፣ የማርያም ባርያ በጭካኔ በጦር ተጨቅጭቆ ተገደለ ።

በዚህ መካከል ፣ በቋረኞቹና በወሎዎች ጠብ መካከል ገብተው ሥልጣን ለመጨበጥ የተጠቀሙት ፣ ደጃች ስሑል ሚካኤል ናቸው ። እርሳቸውም በዐፄ ኢያሱ ጊዜ በትግሬ ሸፍተው ሳለ ፣ በኋላ

1 ታሪክ ነገሥት ፣ ፓሪስ በቁጥር 143 የተቀመጠው ፣ ገጽ 287



በጦር ኃይል ተገድደው ጐንደር ከመጡ ወዲህ ፣ እያደር ከንጉሣዊ ቤተሰብ ተዛምደው የንግሥቲቱን ልጅ አስቴርን አግብተው የኢያሱም ባለሟል ሆኑ ። ካገራቸው ከትግሬ መጥተው ጐንደር በገቡ ቁጥር ለንግሥቲቱና ለንጉሡ በሚያቀርቡት ገጸ በረከት ፣ ለየመኳንንቱ በሚያድሉት ልዩ ልዩ ስጦታ ስማቸው በጐንደር ታወቀ ። ዋና የግዛት ባላንጣቸውን ፣ የእንደርታውንና የእንዳመሆኔን ገዥ ፣ ደጃዝማች ወልዴን በጦርነት ስለ ገደሉ ፣ ትግሬን በሙሉ ጠቅለው መያዝ ቻሉ ። በመጨረሻም ፣ ራስ ወልደ ልዑል በ1759 ዓ. ም. ከሞቱ ወዲህ ፣ በ1760 ዓ. ም. በዐፄ ኢዮአስ ጊዜ ፣ ራስ ተብለው የእንደራሴነቱን ሥፍራ ከሉቦ እየተፋለሙ ያዙ ። በዘዴና በውስጠ ተንኮል ፣ በቅድሚያ ከኦሮሞዎቹ ጋር የኅብረት መልክ አሳይተው ፣ አማሮቹን ከአስጠቁና ራስ ተብለው ሥልጣን ጠቅልለው ከጨበጡ በኋላ ፣ ቀጥለው በኦሮሞቹ ላይ ተነሥተው በይፋ ተጣልተው በዳሞት ከሉቦና ከነፋሲል ጋር ይዋጉ ዠመር ።

ንጉሡ ኢዮአስም ፣ በአማሮቹና በኦሮሞዎቹ ጠብ ጊዜ ተጨንቀው 'ያበርድልኛል' ብለው በመጀመሪያ ላይ ለርሳቸው ሥልጣን ካስጨበጡ በኋላ ፣ በመጨረሻ ለእናታቸው ወገኖች ለነሉቦ ላድላ ብለው ሚካኤልን ለመጣል ምንም ውስጥ ለውስጥ ቢጣጣሩ አልሆነላቸውም ። ኦሮሞዎቹ እነ ፋሲል ፣ እነ ሉቦ በዳሞት በሸፈቱበት ጊዜ ፣ ሚካኤል ስሑል 'ሒደን በመንግሥትዎ ላይ የሸፈቱትን እንውጋ' ቢሏቸው 'እምቢ' ብለው ቀሩ ። ከዚህ በኋላ ፣ ራሳቸው ሚካኤል ሔደው በሚዋጉበት ጊዜ ፣ ኦሮሞዎቹ ተሸንፈው ግማሾቹ ሲሞቱ ወይንም ሲሸሹ ከተማረኩት ላይ በምርምር የኢዮአስ ከሸፍቶቹ ጋር ውስጥ ለውስጥ ማበራቸው ተገለጠ ። ንጉሡን ባደባባይ ከሶ መቅጣት አግባብ ስለ አል ሆነ ፣ የንጉሡ ጠላት የነበሩትን የደጃች ነጩን ልጆች ወደ ቤተ መንግሥት ልከው በእልፍኛቸው እንዳሉ ንጉሡን ኢዮአስን በሻሽ አሳንቀው በግንቦት 8 ቀን በ1761 ዓ. ም. አስገደሏቸው ። በኢዮአስ ፋንታ ፣ ለግዛት የሚመጥኑቸውን ፣ የሰባ ዓመቱን ሽማግሌና እጀ ቆራጣውን ዮሐንስን ፣ ከወህኒ አምባ አውርደው አነገሡ ። የጐንደር ካህናት «ቀታሌ ንጉሥ — ንጉሥ ገዳይ» እያለ ቢያማም ፣ ያማራውና የኦሮሞው መኳንንትም ፣ ሥልጣናችንን በትግሬ 'ተቀማን' እያለ ውስጥ ውስጡን ቢያጕመተምትም ፣

ራስ ሚካኤል ስሑል (*) በጐንደር ተቀምጠው፣ ወደ ዓድዋም እየተመላለሱ በኃይላቸው ሁሉንም እየተጫኑ ከ1760 ዓ. ም. ጀምሮ በሙሉ ሥልጣን ሲያስተዳድሩ ቆይተው፣ በ1763 እና በ1764 ዓ. ም. በላስታና በአማራ ገዥዎች፣ በነደጃዝማች ወንድወሰን ተሸንፈው ተይዘው፣ በድብኮ አንድ ዓመት በግዞት እንዳሉ፣ ደጃች ወንድወሰን 'አገራቸው ይግቡ' ብለው ፈቅደውላቸው በዓድዋ 7 ዓመት ከቆዩ በኋላ፣ አርጅተው በ1772 ዓ. ም. ሞቱ። ቀደም ሲል የትግሬንና ኋላም የጐንደርን መንግሥት ያስተዳደሩበት ጊዜ ሲደመር፣ ወደ ዐርባ ዓመት ይሆናል።

በዚህ መካከል፣ የቋረኞች መመኪያ የሆኑት ንግሥት ምንትዋብ፣ ስሑል ሚካኤል አማቻቸውን ለዚህ ማዕረግም ያበቋቸው አንደኛዋ እርሳቸው ስለሆኑ፣ በስሑል ሚካኤልም፣ በነደጃች ወንድወሰንም፣ በነራስ ዐሥራትም ጊዜ፣ ምንም ከሥልጣን ውጭ ቢሆኑ፣ ሁሉም እሉበት ድረስ እየሔደ እጅ እየነሣ እክብሯቸው ሲኖር፣ ከራስ ስሑል ሚካኤል ሞት ቀደም ብለው በ1767 ዓ. ም. ዐርፈው፣ በዘመናቸው አስጊጠው ባሠሩት ቤተ ክርስቲያን በቁስቋም ተቀበሩ።[1]


የርሳቸው ወገኖች ቋረኞች፣ ምንም የቀድሞ ገናንነታቸውና በየከፍተኛው ሥልጣን ተሳታፊነታቸው ቢቀር፣ ቀድሞ ከሞት የተረፉት በስሑል ሚካኤልም፣ በነወንድወሰንም፣ በነራስ ዐሊም ዘመን ሁሉ በልዩ ልዩ ሥራ እየተባበሩ ሠርተዋል። ከነዚህም ውስጥ ደጃች ኃይሉ እሸቴ፣ የእቴጌ ምንትዋብ እክስት፣ የወይዘሮ ሰብሌ የልጅ ልጅ የደጃች እሸቴ ልጅ፣ የራስ ስሑል ሚካኤልን ልጅ አግብተው፣ ብዙ ጊዜ ከሹመት ወደ ሹመት እየተዘዋወሩ፣ አንድ ጊዜም በራስ ሚካኤል ስሑል ባላጋራዎች እየተሻሩ፣ ወደ ጐጃምም እየተሰደዱ እስከ ብዙ ዘመን ቆይተዋል።[2] የሞቱበትን ጊዜ የሚናገር ማስረጃ ለጊዜው አላገኘንም።

---

* ስሑል ማለት 'የተሳለ፣ ስል፣ ሹል' ማለት ነው። የራስ ሚካኤል የቅጽል ስም ሲሆን ከስማቸው ቀድሞም፣ ተከትሎም ይነገራል (ይጻፋል።

1 ታሪክ ነገሥት፣ ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት፣ ቍ. 143 ገጽ 287። እቴጌይቱ የሞቱበትን ግንቦት 26 ቀን 1765 ዓ. ም. የሚያደርገው አለ።

2 Idem...pp. 250—285.




ራስ ስሑል ሚካኤል
(ከጄምስ ብሩስ መጽሐፍ)



ከደጃዝማች የማርያም ባሪያ ሞት በኋላ ራስ ስሑል ሚካኤል ያገቧቸው
ወ/ሮ አስቴር ኢያሱ (ምልምል)
(ከጀምስ ብሩስ መጽሐፍ)



ጄምስ ብሩስ የራስ ስሑል ሚካኤልን እጅ ሲስም
(ከስቱር ዱ ሞንድ መጽሐፍ)

# ምዕራፍ ሁለት

*በካሣ ልደትና ዕድገት አካባቢ የነበሩት መሳፍንት ያገዛዝ ፍልሚያ — ልጅ ካሣ ባሽከርነት ያገለገሉዋቸው መኳንንትና መሳፍንት*

ዝርዝር ታሪክ ሰፌ ሐተታ ቢጐድለውም ፣ የዐፄ ቴዎድሮስን ታሪክ በደረቁና በመጠኑ ጽፈው ያወረሱን ሦስት የኢትዮጵያ ምሁራን ናቸው ። እነዚህም ፤

አንደኛው አለቃ ዘነብ የሚባሉት የይፋት (ሸዋ) ተወላጅ ሲሆኑ ፣ እርሳቸውም በመዠመሪያው ወቅት የንጉሠ ነገሥቱ የጸሐፊዎች አለቃ (ጸሐፌ ትእዛዝ) በመሆን ሲያገለግሉ ቆይተው ፣ በኋላ ጸሐፌ ትእዛዝ እንግዳ ሲተኩ ፣ እርሳቸው የመዝገብ ቤት ሹም ሆነዋል ።[1] ያፄ ቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት ፣ ከእንግሊዝ ጦር ጋር በ1860 ዓ. ም. እስከ ግብጽ ድረስ ከሔዱ በኋላ ፣ ከዚያ ተመልሰው ምጥዋ ከነሙንዚንገር ጋር በሰነበቱበት ጊዜ ይሁን ፣ ወይም ወደ አገራቸው ወደ ይፋት ከተመለሱ በኋላ ይሁን ፣ በትክክል አይታወቅም ። የሆነ ሆኖ ፣ የርሳቸውን ታሪካዊ ጽሑፍ ኢኖ ሊትማን የሚባሉት የጀርመን ሊቅ በ1902 ዓ. ም. (እ.ኤው. ቁ.) በማሳተም አራብተውታል ።

ሁለተኛው ፣ አለቃ ወልደ ማርያም ዘምሑይ (ሸዋ) የጻፉት ነው ። እርሳቸውም በመቅደላ ከግዞተኞቹና ከነአባ ሰላማ ጋር እንደ ነበሩ ሲናገሩ ፣ እንደ ዘነብ ቀደም ብለው የቴዎድሮስ አሽከር ይሁኑ ፣ አይሁኑ አናውቅም ። ታሪኩንም የጻፉት ቴዎድሮስ በሞቱ በዐሥራ ሦስተኛው ዓመት ፣ በ1873 ዓ. ም. መሆኑን ራሳቸው በጽሑፉ መጨረሻ ገልጠውታል ።[2] የርሳቸውንም የእጅ ጽሑፍ ብዙ ዘመን በአዲስ አበባ ያፄ ምኒልክ አማካሪ

---

1 Narratife of The Mission
H. Rassam - Vol. II - pp. 152-349

2 ሞንዶን ቪዳዬ ያሳተሙት ያለቃ ወልደ ማርያም ጽሑፍ ገጽ 79

ሆነው የተቀመጡት ሙሴ ሞንዶን ቪዳዬ ወደ ፈረንሣይኛ ተርጕመው በማሳተም ፣ አራብተው ጽሑፉን ከአውሮፓ ሊቃውንት ጋር አስተዋውቀውታል ።

ሦስተኛው ፣ ስማቸው የማይታወቀው ፣ ነገር ግን በአጻጻፋቸው ውስጥ የትግራይ ወይም የትግሬ ተወላጅና ፣ በዚህም ላይ የኢጣሊያን ቋንቋ የሚያውቁ መሆኑ የሚያስታውቀው ጸሐፊ ናቸው ። ይኸንኑ ጽሑፍ እንደ አውሮጳ አቆጣጠር በ1959 ዓ. ም. በሮማ ሉዊጂ ፉዚላ አሳትመውታል ።

የሦስቱም ጸሐፊዎች አተራረክና በቴዎድሮስ ታሪካዊ አፈጻጸም ላይ ጊዜው ይለያያል ። አለቃ ዘነብ ፣ ከወደ መዠመሪያው ያለውን የካሣን የልደታቸውን ፣ የዕድገታቸውን ፣ የሽፍትነታቸውን ፣ የሹመታቸውንና የንጉሠ ነገሥትነታቸውን ዘመን እንደ ተቻለ በዘመኑ አነጋገር አስፋፍተው ከጻፉ በኋላ ፣ የመጨረሻውን ዘመን አስቀርተውታል ። ጽፈውት ፣ ሌላ ሰው ጕርዶ አስቀርቶት ወይስ ጠፍቶ ይሆን ያሰኛል ። አለቃ ወልደ ማርያም ፣ የመዠመሪያውን የቴዎድሮስን የልጅነትና የወጣትነት ዘመን በመቀነጣጠብ አሳጥረው ፣ የመካከለኛውንና እስከ ፍጻሜ ሕይወታቸው ድረስ ያለውን ግን ትንሽ ሰፋ አድርገው ጽፈዋል ። ሦስተኛው ፉዚላ ያሳተሙት ፣ ከመዠመሪያውና ከመካከለኛው የበለጠ ፣ በነዚያ በሁለቱ ጽሑፎች ውስጥ የማይገኝ ፣ የመጨረሻው የቴዎድሮስን ሕይወት በመቅደላ ፣ በርሳቸውና በእንግሊዞች መካከል የተደረገውን ጦርነትና የንጉሡን ያማሙዋት ሁናቴ ስለሚዘረዝር ፣ በተቻለ መጠን የኝህን ስመ ጥር ንጉሠ ነገሥት ታሪክ ለማሟላት ጠቅሟል ። ስለዚህ ሦስቱም ጸሐፊዎች ከነርሱ ወዲህ ለተነሡት ለነጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ፣ ለዛሬ ዘመን ጸሐፊና አንባቢ ባለውለታ መሆናቸው አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ታሪካችን ውስጥ ፣ ከቀድሞ ዠምሮ አባቶቻችን በታሪካዊ ጽሑፋቸው ውስጥ ቀንና ዓመተ ምሕረት ለመጨመር እምብዛም አይቸገሩም ። በጣም የሚያስቸግረው ፣ ወሩን ጽፈው ዓመቱን ወደ ጐን በመተው ፣ ወይም በየፈረቃ የሚውለውን ካራት አንዱን የወንጌላዊውን (ማቴዎስ ፣ ማርቆስ ፣ ሉቃስ ፣ ዮሐንስ) ስም ጠቅሶ ማለፍ ልማዳቸው ነው ። በዚህም ምክንያት እላይ ስማቸው የጠቀስነው አባቶች ፣ ብዙ ነገር ሲጽፉ



ካሣ የተወለዱበትን ቀንና ዓመተ ምሕረት አልጠቀሱም ። የሚጽፉት አብዛኛውን ጊዜ ፣ ወደኋላ ተመልሰው የሴሉበትን ጭምር ያለፈ ታሪክ ስለሆነ ፣ ቀንና ዓመተ ምሕረት መጠየቁ መመራመሩ ያዳግታቸዋል ። የሚጠየቅ ቤተሰብ ቢገኝም ፣ ያመተ ምሕረትን ነገር ፣ እንኳን የዚያን ዘመን ቤተሰብ ፣ የሐያኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንኳን ቤተሰቦች ፣ አብዛኞቹ የልደትን ቀንና ዓመት በማወቅ አይጠነቀቁም ። አንድ አድራጐት ተፈጽሞ እንደሆነ በዚያ ስሌት ይደረጋል ፣ በመካከል የተወለደው ወይም የሞተው ትክክለኛ ጊዜው እንደ ተዳፈነ ይቀራል ማለት ነው ። በተለይ ደግሞ ፣ ቢበዛ የነገሥታት የጳጳሳት ይጻፍ እንደሆነ ነው እንጂ ፣ ወደፊት ይነግሣሉ ተብለው ያልተጠረጠሩትን የካሣን የልደት ቀንና ዓመት ለመጻፍ በቅድሚያ የሚያስበው የለም ።

ስለዚህ ፣ ያገራችንን ታሪክ ለመጻፍ ባገራችን ጽሑፍ ያጣነውን ለማግኘት ፣ ምዝገባ ወደ ለመዱት ወደ ፈረንጆች ጽሑፍ ሔዶ መፈለግ ልማዳችን ከሆነ ቆይቷል ። ያጼ ቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት ወይም የተጻፈውን ወደየቋንቋቸው የተረጐሙት ፣ አብዛኞቹ የካሣን ልደት (እ.ኤ.አ.) በ1818 — 1820 ዓ. ም. መካከል አድርገውታል ።(1) ሬቤራንድ (የተከበሩት) ሐንሪ ስቴርን ብቻ እስከ 1822 ዓ. ም. አራዝመውታል ። (2) መሠረት ማድረግ የሚሻለው የፊተኞቹን ይመስላል ። እነርሱ ከሰጡት 1818 — 1820 ዓ. ም. ላይ ወደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ያመጣነው እንደሆነ ካሣ የተወለዱት በ1811 ይሆናል ። ይኸውም እኔ ካሠፈርሁት ከ1811 ዓ. ም. (ጥር 6 ቀን) ጋር ይገጥማል ።(3)

የካሣ የአባታቸው አገር ቋራ ነው ። እናታቸው የጐንደር ተወላጅ ናቸው ። ቋራ የሚገኘው በጠቅላላው ከቤገምድርና ፣ በተለይም ከመናገሻ ከተማው ከጐንደር በስተምዕራብ በሚገኘው በደምቢያ ውስጥ ነው ። ይኸም የደምቢያ ወረዳ ፣ ከደቡብ በኩል አገው ምድር ፣ ከወደ ሰሜን ስሜንና የአርማጭሆ በረሃ

1 Chronique de Theodros II - Mondon Vidaillet, p, 12, J. B. Coulbeaux Hist. Pol. Vol. II - p. 409
2 The Captive Missionary.........Chap. 1, p, 2
3 የክርስትና ስማቸው ገብረ ኪዳን መሆኑ በፉዚላ መጽሐፍ ገጽ 1 ላይ ተጠቅሷል ።

በምዕራብ የሱዳን ግዛት ያዋስኑታል ። ከጐንደር ዘመነ መንግሥት ከነፋሲል ከነአድያም ሰገድ ዠምሮ ፣ ሱዳኖችንና ገዥዎቻቸውን ፣ ግብጾችንና ቱርኮችን ባንድ ወገን ፣ ኢትዮጵያውያንን በሌላ ወገን ሲያከራክር ፣ ሲያዋጋ የኖረው ፣ የስናር ወረዳ ፣ እንዲሁም ከተማዎቹ እነ ጋላባት ፣ እነ መተማ በምዕራብ በኩል ከደምቢያና ከቋራ ጋር በቅርብ ይዋሰናሉ ።

ቴዎድሮስ በተወለዱበት ዘመን (1811 — 1812) ፣ ደብረ ታቦር ተቀምጠው ደንበኛውን የመስፍንነቱን ሥልጣን የያዙት ታላቁ ራስ ጉግሣ ናቸው ። በዚሁ ጊዜ በትግራይ ራስ ወልደ ሥላሴ ፣ በስሜን ራስ ገብሬ ፣ በዳሞትና በአገው ምድር ደጃች ዘውዴ ፣ በጐጃም ደጃች ጓሉ ፣ በላስታ ዋግሹም ከንፉ ፣ በወሎ ደጃች ሊበን ፣ በሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የየክፍለ ሀገራቸውን ይዘው ያስተዳድራሉ ። በዚሁ ጊዜ ፣ መሳፍንቱ በትውልዳቸው ልዩነት የተነሣ ፣ ይኸውም ማለት ከሰሎሞናዊው ዘር ስለማይወለዱና ራሳቸው መንገሥ ስለማይችሉ ፣ አገሪቱም ‘ያለ ንጉሥ አትገዛም’ በሚል የባህል እምነት ፣ ከነገሥታቱ ልጆች እነ ዕጓለ ጽዮንን ፣ እነ ተክለ ጊዮርጊስን ፣ እነ ኢዮአስ ዳግማዊን ፣ እነ ሕዝቅያስን ፣ እነ ሣህለ ድንግልን እንደ ፈለጋቸው እያቀያየሩ ያነግሡና ፣ እነሱ ደግሞ ከነጋሢዎቹ የራስነትን ማዕረግ ተቀብለው ያስተዳደሩን ሥልጣን ይጨብጣሉ ። ይኸውም ፣ በጳጳስ ያልነገሠ ንጉሥ ዋጋ እንደሌለው ፣ በነጋሢ ያልተሠየመ ራስነትም አይረጋም በሚል ባህላዊ ስሜት ነው ።

እንግዲህ ከዚሁ ከራስ ጉግሣ ዘመን ዠምሮ ፣ በልጆቻቸው በነራስ ይማም ውስጥ ሆነው በትክለኛ ባላባትነት ደምቢያን ፣ ከዚያም ኃይል ሲመቻቸው ፣ አካባቢውን ወገራንና አቸፈርን ጨምረው የሚገዙ ደጃች ማሩ ናቸው ። ቋራ በደምቢያ ውስጥ ስለ ሆነ ፣ በደጃች ማሩ ሥር ሆነው ቋራን በባላባትነት የሚገዙት ደግሞ ፣ የካሣ አባት ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ ናቸው ። ከማሩ በፊት ፣ ደምቢያንና ቋራን የራስ ጉግሣ ልጅ ደጃች አሉላ ይገዙ ነበር ። አሉላ ከሞቱ በኋላ ለማሩ ተሰጠ ።

ግንቦት 16 ቀን 1817 ዓ. ም. ራስ ጉግሣ ሲሞቱ ፣ ልጃቸው ራስ ይማም ደንበኛው መስፍን ሆኑ ። ደጃች ማሩ ፣ የራስ ይማምን ልጅ ወይዘሮ ወርቅ ወሃን ያገባሉ ። እንደዚሁም በስሜን ራስ



ገብሬ ሞተው ፣ በሕይወታቸው ከራስ ጉግሣ ልጅ ከወይዘሮ ሂሩት የወለዷቸው ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ፣ አባታቸው ራስ ገብሬ ከሞቱ በኋላ ስሜንን ሲገዙ ቆይተው ፣ በግንቦት በ1818 ዓ. ም. እሳቸውም ሞቱና ልጃቸው ደጃች ውቤ ተተኩ ። በአገውም ደጃዝማች ዘውዴ ሞተው ልጃቸው ደጃች ጐሹ ፣ በጐጃምም ራስ መርድ ሞተው ደጃች ጓሉ ተሾመዋል ። በትግሬም የእንደርታው ራስ ወልደ ሥላሴ ሞተው ፣ የአጋሜው ደጃች ሰባጋዲስ ተተክተዋል ። በሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ግን ፣ ካገሩ ርቀት የተነሣ የግዛት ዘመናቸውም ረዘም ያለ ስለሆነ የሚጐንጣቸው ሳይኖር ፣ በሰላም ግዛታቸውን ያስፋፋሉ ። በልጅ ካሣ ልደትና ዕድገት አካባቢ ማሕል ፣ ኢትዮጵያንና ሰሜን ምዕራቡን ተከፋፍለው የሚገዙ መሳፍንት እነዚህ ናቸው ።

በዚህ መካከል ፣ ደጃች ማሩ የደምቢያና የቋራው ገዥ ፣ የራስ ይማምን ልጅ ወይዘሮ ወርቅ ወሃን አግብተው ሲኖሩ ፣ ሴትዮዋ ስለሞቱ ለሁለቱ ዝምድና እየቀዘቀዘ መሔድ ምክንያት ሆነ ። ቢሆንም ፣ ይማምና ማሩ የበላይና የበታች ሆነው በስምምነት እንዳሉ ፣ ይማም ውቤን ግባልኝ ቢሉዋቸው እምቢ አሉ ። ለጊዜውም ማሩና ውቤ በይማም ጀርባ ተስማምተው ሳለ ፣ ማሩ ሳይሰሙ ውቤ በምስጢር ተላልከው ለራስ ይማም ገብተው ተራረቁ ። በዚህ ጊዜ ፣ ደጃች ማሩ ተናደው የደጃዝማች ኃይለ ማርያምን ደግነትና የዋህነት ፣ የልጃቸውን የውቤን ተንኮለኛነት በማውሳት ፣ «በግ እባብ ይወልዳልን?» አሉ ይባላል ።[1]

ከዚህ በኋላ ፣ እንደራሴው ራስ ይማም ማሩን ለማሳዘን ፣ ውቤን ለማስደሰት ሲሉ ፣ ወገራን ከደጃዝማች ማሩ ወስደው ለውቤ ጨመሩላቸው ። ስለዚህ ፣ በደጃዝማች ማሩና በራስ ይማም መካከል ፣ በፊተኛ ጊዜ ከነራስ ጉግሣ ጊዜ ዠምሮ በነበረው ወዳጅነት ፈንታ ጠብ ተተካ ። ደጃዝማች ማሩም ለራስ ይማም አልታዘዝም ስላሉ ፣ ይማም ጦራቸውን ይዘው ወደ ደምቢያ ጉዞ ሲዠምሩ ፣ ውቤም ‘ታመሃል ቅር’ ቢባሉ ‘እምቢ’ ብለው በቃሬዛ እየተጓዙ ተከተሉ ። ደጃች ማሩም የአገው ምድሩን ገዥ ደጃች ጐሹን በማባበል ጭምር አስተባብረው ሊመክቱ ከተስማሙ በኋላ ፣ ትንሽ እንደ ተቀራቀቡ የራስ ይማምን ጦር አበዛዙን

1 ወሰሚዖ ደጃዝማች ማሩ ከመ ሖረ ደጃዝማች ውቤ በኀቡዕ ኀበ ራስ ይማም ፣ ይቤ በግዕ ይወልድኑ አርዌ La Crronaca Reale Abyssina Conti - Rossini pp. 63 - 65

ጐሹ አመዛዝነው ፣ ማሩን አጋልጠው ወደ አገራቸው ወደ ዳሞት ሸርተት ብለው ሔዱና ማሩ ብቻቸውን ቀሩ ።

ከጐሹ በቀር የራሳቸው ም መኳንንት ቢከዱዋቸውም ፣ «እኔ ማሩ በፈረሴ ጀርባ ላይ እንዳለሁ እየተዋጋሁ እሞታለሁ እንጂ ፣ ምንም ቢሆን ለጠላቴ እጄን አልሰጥም» ብለው ፣ ጦርነት በተዠመረበት ሰዓት ተመልካች እስኪደነቅ ድረስ በፈረሳቸው ላይ እንዳሉ ወዲያና ወዲህ እየተራወጡ ፣ በዠግንነት ሲያዋጉና ሲዋጉ ፣ የላስታው የዋግሹም ክንፉ ወታደር በጥይት መትቶ ከፈረሳቸው ገለበጣቸውና ፣ በጥቅምት 17 ቀን 1820 ዓ. ም. ሞተው በዋሸራ (ጐጃም) ተቀበሩ ። (1) በሙሟታቸው ዋና ባላጋራቸው ራስ ደግም ሳይቀሩ የቀድሞውን ወዳጅነት አስበው አለቀሱላቸው ።

በዚህ ጊዜ ፣ አባታቸው ከእናታቸው ተፋትተው ካሣ ከእናታቸው ጋር በጐንደር የሕፃንነታቸውን ጊዜ ካሳለፉ በኋላ ፣ ትንሽ ከፍ ሲሉ በቾንከር ተክለ ሃይማኖት ይማሩ ነበር ።(2) ዕድሜያቸው በዚህ ሰዓት (1822) 10 ዓመት በደረሰበት ወቅት ፣ አሸናፊውን ራስ ይማምን ተከትሎ የመጣው የዋጅራት ፣ የራያና የአዘቦ ዘማች በገዳሙ ገብቶ ያገኘውን እየዘረፈ ብዙ ሕፃናትና ተማሪዎች ፣ መምህራን ጭምር የፈጀ ጊዜ ፣ ካሣ በጫካ ተደብቀው ለጥቂት አመለጡ ።(3) በዚህም ጊዜ የካሣ አጐት ክንፉ በደጃች ማሩ ውስጥ ሆነው ሲዋጉ በላስቶች እጅ ተማርከው ሔዱ ።

ከዚህ በኋላ ፣ ካሣ ፣ እላይ እንዳልነው አባትና እናታቸው በሕፃንነታቸው ስለ ተለያዩ ፣ ከእናታቸው ጋር ወደ ጐንደር ሔደው ተቀመጡ ። ራስ ይማም ፣ ደጃች ማሩ ከሞቱ በኋላ ፣ የደምቢያን ግዛት ለቋራ ባላባቶች ለነ ክንፉ ይሰጡ ይሆን እየተባለ ሲጠበቅ ፣ ለታናሽ ወንድማቸው ለማርዬ ደረሰ ። አሁንም ራስ ማርዬ በመዠመሪያው ወቅት የደጃች ማሩን ግዛት ደምቢያን

1 ወተድኃሉ ደጃዝማች ጐሹ ምስለ ሠራዊት...... ወተርፈ ባሕቲቱ ደጃዝማች ማሩ ፣ ሐራሁኒ ወመኳንንቲሁኒ እለ አኩነኖሙ ሀገረ ኢተለውዎ ። ወአንከርዎ መኳንንት እንዘ ይትመያየጥ በፈረስ ማዕከለ ተትል ። ወይቤ ኢይገብእ ውስተ ዕደ ፀርየ አላ እመውት በዛባነ ፈረስየ ። ወቀተሎ አሐዱ ሐራዊ ዘዋግሹም ክንፉ በነፍጥ ፣ ወወድቀ እምላዕለ ፈረሱ ወሞተ ... La Chronaca Reale . . . p/65-68

2 ሲትማን ያሳተመው ያለቃ ዘነብ ጽሑፍ ገጽ 5 ሞንዶን ያሳተመው (ሞ /ማ) ገጽ 1-2

3 አለቃ ዘነብ ገጽ 5



ለወገኖቻቸው ለባቡ ባሪሆይ ፣ ቀጥሎም ለወሬኛ ወንዴ ከሰጡ በኋላ ፣ በመጨረሻ ለደምቢያው ትክለኛ ባላባት ፣ ለክንፉ የደጃዝማችነት ማዕረግ ጨምረው ሰጧቸውና የደምቢያና የቋራ ሕዝብ ደስ አለው ።

በመካከሉ ፣ ራስ ማርዬና የትግሬው ገዥ ደጃች ሰባጋዲስ በግዛት ተጣልተው ለውጊያ በሚፈላለጉበት ጊዜ ፣ የስሜኑ ደጃች ውቤ በመዠመሪያ ከሰባጋዲስ ጋር ተስማምተው ፣ የሰባጋዲስን ልጅ ወይዘሮ ድንቄን አግብተው ፣ ከቀድሞው ወዳጃቸው ከራስ ማርዬ ጠበኛ ሆነው ነበር ። ራስ ማርዬም ከሰባጋዲስ በፊት ውቤን ለመውጋት ሲዘጋጁ ፣ ውቤ ሰባጋዲስን «ናና እርዳኝ» ቢሏቸው ፣ «እዚሁ እኔ ዘንድ መጥተህ ከረምትን አብረን እናሳልፍና በኋላ ባንድነት ሆነን ማርዬን እንወጋለን» ብለው መለሱ ። ውቤ ግን ፣ «ይኸ እንዴት አድርጎ ይሆናል ፣ ወዳንተ ስመጣ አገሬ ይያዛል » እየተባባሉ ሁለቱ መልእክት ሲለዋወጡ ፣ ማርዬ ወደ ስሜን ዘምተው ውቤን አባረሩ ። በመጨረሻም ፣ እንደራሴውን ማርዬን መመከት አቅቷቸው ፣ ውቤ መልሰው ለማርዬ ታጥቀው ገቡና ፣ በጠላትነቱ ቦታ ማርዬና ሰባጋዲስ ብቻቸውን ስለቀሩ ፣ ተከዜ ወንዝ አጠገብ በ1822 ዓ. ም. መጋቢት ወር ሁለቱ ተጋጥመው ሲዋጉ ፣ ሐጐስ የሚባሉት የሰባጋዲስ ልጅ ራስ ማርዬን በጥይት ሲገድሉ ፣ የማርዬም ወገኖች እነ አዛዥ ውብሸት ሐጐስን ገደሉና የጌታቸውን ሞት ተበቀሉ ።

ደጃች ሰባጋዲስ ፣ ባንድ ወገን ተማርከው በማርዬ ሰዎች እጅ እንዳሉ ፣ የልጃቸውን የሐጐስን ሞት ሰምተው ሐዘናቸውን ሳይጨርሱ ፣ የጌታቸው ሞት ያናደዳቸው የራስ ማርዬ ሰዎች እርሳቸውንም ገደሏቸው ። በሰባጋዲስ ጊዜ የገነኑት የአጋሜ ባላባቶች በዚህ ጊዜ ትልቅ ውድቀት አገኛቸው ። በርሳቸው ፋንታ በዚህ ግርግር መካከል ፣ ብልጡ የስሜኑ የራስ ገብሬ የልጅ ልጅ ፣ እኚሁ ውቤ እየተስፋፉ ፣ እያደር እየተጠናከሩ ሔደው ትግራይንና ትግረን ጠቅልለው ለመያዝ ቻሉ ። በሟቹ በራስ ማርዬ ፈንታ ፣ አሁን ወንድማቸው ራስ ዶሪ ተተኩ ። ራስ ዶሪ በአባታቸው በራስ ጉግሣ ፈቃድ ውጫሌንና ወረሂመኑን ሲገዙ ቆይተው ፣ ወደ ዳሞት ተዛውረው በሚገዙበትና በርሳቸው እግር ደጃች ጐበና በተሾሙ ጊዜ ፣ የዶሪን ቸርነት የጐበናን ጨካኝነት በማውሳት በዘመኑ እንደዚህ ተብሎ ተገጠመ ።

«ባልቴቱ በምን ትጦሪ
ሳዱላይቱ (ልጃገረዲቱ) በምን ትዳሪ
ጎጃም ሔደና እንጀራው ዶሪ
ጎበና መጣ ቀንጃ (ቋንጃ) አስመታሪ ። » ([1])

የሆነ ሆኖ ፤ ራስ ዶሪ ከዳሞት (ጐጃም) መጥተው በወንድማቸው በራስ ማርዬ እግር እንደ ተተኩ ፤ ምንም ያህል ሳይቆዩ በሦስተኛው ወር በሰኔ በ1822 ዓ. ም. ሞተው የወንድማቸው የደጃች አሉላና የወይዘሮ መነን ልጅ ራስ ዐሊ የመስፍንነቱን ሥፍራ ያዙ ። ([2])

በዚህ ዐይነት ፤ ከታላቁ ራስ ጉግሣ ወዲህ በመስፍንነቱ ሥልጣን የተከታተሉት ራስ ይማም ፤ ራስ ማርዬ ፤ ራስ ዶሪ ልጆቻቸው ሲሆኑ ፤ አሁንም የመስፍንነቱ ሥልጣን ከርሳቸው ቤተሰብ አልወጣም ።ከዶሪ የቀጠሉት ራስ ዐሊ (ትንሹ) የወንድማቸው የደጃች አሉላ ልጅ ናቸው ። አሉላ የወሎውን ባላባት ፤ የደጃች ሊበንን ልጅ ፤ ወይዘሮ መነንን አግብተው ዐሊን ይወልዳሉ ። ስለዚህ ፤ ዐሊ የራስ ጉግሣ የወንድም ልጅ ፤ ዩልጅ ካሣ (ኋላ ቴዎድሮስ) ባለቤት ፤ የወይዘሮ ተዋበች አባት መሆናቸው ነው ።

ራስ ዐሊ የመስፍንነቱን ሥልጣን በያዙበት ጊዜ ፤ ደጃች ውቤም እላይ እንዳልነው ግዛታቸውን በወገራ ፤ በስሜን በትግራይና በትግሬ አስፋፍተው ይዘዋል ። የካሣ ኃይሉ አገር ፤ ቋራና ደምቢያም ላጭር ጊዜ ፤ ራስ ዶሪ ባላባቱን ደጃች ክንፉን ሽረው አስረዋቸው ሳለ ፤ አሁን ዐሊ ከእስራቱ ፈትተው የቀድሞ ግዛታቸውን ደምቢያን አደላድለው መለሱላቸው ።

ከደጃች ማሩ ወዲህ ፤ በደምቢያ የተሾመ እንደ ደጃች ክንፉ ስመ ጥር የሆነ መሪ አልተነሣም ። እርሳቸውም ፤ የደጃች ማሩ የእኅት ልጅ ፤ የወይዘሮ ወለተ ተክሌ ልጅ ናቸው ። ባስተዳደርና በተለይ በመተማና በጋላባት ደጃች ክንፉ የኢትዮጵያን ወሰን ለማስከበር ያደረጉት ተጋድሎ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል ።

1 La Chronaca Reale Abyssina - Conti Rossini, pp. 44 - 48;
2 Idem p. 76-78



እላይ ከጠቀስናቸው ፤ ሦስት ያፄ ቴዎድሮስን (ካሣን) ታሪክ ከጻፉት ውስጥ ፤ አንዱ አለቃ ወልደ ማርያም ፤ «በቋራ (ካሣ) የደጃች ክንፉ የወንድም ልጅ ሆነው አደጉ» ብለው ያል ፋሉ ። ወንድም የሚሉት የካሣን አባት ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስን ነው ።([1])

ስማቸውን ባለማወቃችን የምናዝነው ፤ የትግራይ ወይም የትግሬ ተወላጅ የጻፉትና ፤ ሉዊጂ ፉዜላ ያሳተሙት መጽሐፍ ፤ ባንድ ቦታ ላይ ክንፉን የካሣ ወንድም ያደርጉና መልሰው አጐት ያደርጓቸዋል ።«ያጤ ቴዎድሮስ ትውልዳቸው ፤ ያባታቸው አገር ቋራም ደምቢያም ነው ፤ ያባታቸው ስም ወልደ ጊዮርጊስ ኃይሉ ይባላሉ...... ወልደ ጊዮርጊስ ኃይሉ ከወንድማቸው ከደጃች ክንፉ ተጣልተው ጐንደር ከገዳም አስደውለው (ደውለው) ተቀምጠው ነበር ። ከዚያ ወዲያ ወይዘሮ አትጠገብን በጐንደር አገኙዋቸ ውና ዐፄ ቴዎድሮስን አረገዙ.....» በማለት ክንፉን የኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ ወንድም ያደርጉዋቸዋል ። በእኔ አስተያየት ጉዳዩ 150 ዓመት ያለፈው ታሪክ ስለሆነ ፤ የዛሬ ዘመን ሽማግሌዎች ከሚሰጡን ወሬ ይልቅ በዘመኑ ላይ የነበሩ እነዚህ ጸሐፊዎች ያሰፈሩትን ማመኑ ሳይሻል አይቀርም ። አለቃ ዘነብ በበኩላቸው አጐትም ፤ ወንድምም መሆናቸውን ሳይለዩልን ካሣ በደጃች ክንፉ ቤት ማደጋቸውን ብቻ ገልጠው ዐልፈውታል ።([2])

ከወንድምነት ይልቅ አጐትነታቸውን የሚያስረዳው ፤ በግዕዝ ተጽፎ ኮንቲ ሮሲኒ በ1917 ዓ. ም. ያሳተሙት ፤ «ደጃዝማች ክንፉ ከመሞቱ በፊት ፤ ወንድሞቹ፡ ደጃዝማች ገብሩና እንዳዋ ኃይሉ እናታቸው ወለተ ተክሌ ሞቱ.....» ይላል ።(*) ጽሑፉ «እንዳዋ ኃይሉ» ያለው የኃይሉ ልጅ ማለቱ ፤ ሌላ የካሣ አባት ያልሆነ ሞግሼ ሊሆን ይችላል ። ስለዚህ ክንፉ በትክክል የካሣ ወንድም ወይም አጐት መሆናቸው እስኪጣራ ድረስ እንደዘሁ ትተን ወደ ሌላው ታሪክ እንለፍ ። ነገር ግን በብዙው አኳኋን ክንፉ ለካሣ አጐት ይመስላሉ ።

1 ሞንዶን ቪዳዬ ያሳተሙት ገጽ 1
2 ኢኖ ሊትማን ያሳተመው ..... ገጽ 5
* ወእምቅድመ ይሙት ደጃዝማች ክንፉ ሞቱ እኅዊሁ ደጃዝማች ገብሩ ፤ ወእንዳዋ ኃይሉ ወእሞሙ ወይዘሮ ወለተ ተክሌ ።


የሆን ሆኖ ካሣ ኃይሉ ፣ ለደጃዝማች ክንፉ አሽከር ሆነው
ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ፤ ከርሳቸው ዘንድ ኮብልለው ለጐጃሙ
መስፍን ለደጃች ጐሹ ዘውዴ አድረዋል ። ከአጐታቸው ከክንፉ
ቤት ፣ ከትውልድ አገራቸው ከደምቢያና ከቋራ ኮብልለው ወደ
ጐጃም የሔዱበትን ምክንያት ጸሐፊዎቹ ለየት እያደረጉ ይተር
ኩልናል ። አለቃ ወልደ ማርያምና ስማቸው ያልታወቀው ጸሐፊ ፣
መነኮሳትና ባሕታውያን ፣ ‘ካንተ በኋላ ያንተን ገዥነት ልጆ
ችህእነ መኰንን ፣ እነ ይልማ አይወርሱም ፤ ወራሹ የኃይሉ ልጅ
ካሣ ነው’ ብለው ስለ ነገሩዋቸው ፣ በዚሁ ይወዱዋቸው በነ
በረው በካሣ ላይ ጥላቻ አደረባቸው ። ከዕለታት አንድ ቀንም
ግብር ገብቶ ሲበላ ፣ ካሣ ቆመው ሥጋ ሲያስቆርጡ ፣ ክንፉ
በጩቤ ሊወጉዋቸው ሲሉ ሳቷቸው ። ከዚያ ካሣ ከደምቢያ ወደ
ጐጃም ሔደው ለደጃች ጐሹ ማደራቸውን ሲገልጡልን ፣ አሁንም
የቴዎድሮስ አንድ ጊዜ ጸሐፊ ትእዛዝ ፣ ሌላ ጊዜ የመዝገብ ቤት
ሹም የነበሩት ፣ አለቃ ዘነብ የዚህን ጉዳይ ለየት አድርገው እንደ
ዚህ ሲሉ ይተርኩታል ። «......ከደጃች ክንፉ ቤት ነው ያደጉት ።
ደጃች ክንፉ በሞቱ ጊዜ ልጅ ካሣ ከልጃቸው ከልጅ መኰንን
ሆኑ ። የደጃች ክንፉ ልጆች መኰንንና ይልማ ይባሉ ነበር ።
ሁለቱ በተዋጉ ጊዜ ዘንዶ በሚባል አገር ልጅ መኰንን ድል
ሆኑ ፤ ልጅ ካሣም ተማርከው ሳሉ አብሮ አደግ ናቸውና ያ ማር
ኳቸው ያለ ፣ ፈረሳቸውን መልሶ ሰጣቸው» ካሉ በኋላ ፣ በዚሁ ፈረስ
እንደ ተቀመጡ ሁለት ዝሆን ገድለው ፣ አሽከርነት አድረውላ
ቸው የነበሩትን አቶ ቢተዋን እንዳስቀኑ ፣ እንደ ገና ከደጃች
ክንፉ ልጆች ከነልጅ መኰንን ጋር ተደባልቀው የጐጃሙን ገዥ
ብሩ ጐሹን መውጋታቸውን ፣ ከዚያ ተሸንፈው ዘርጊ በሚባል
አገር ባንድ ሰው ቤት ተደብቀው ስለዳኑ ፣ በኋላ የቋራ ገዥ
ሆነው ደጃዝማች በተባሉ ጊዜ ፣ ይኸንኑ ሰው በድምፁ ዐውቀው
እንደ ሸለሙት አስፋፍተው ይጽፋሉ ።([1])

የካሣን ዕድገት በዚህ ዐይነት ጸሐፊዎቹ ለያይተው ቢያቀር
ቡትም ፣ የሕፃንነት ጊዜያቸውን (1812 — 1817) በጐንደር
ከናታቸው ጋር ከዚያም ትንሽ ከፍ ሲሉ ፣ ምናልባት ከአምስት
እስከ ዐሥር ዓመት (1817 — 1822) ያለውን ጊዜያቸውን
በቸንከር ተክለ ሃይማኖት ገዳም (*) በአገራቸው ትምህርት

1 የቴዎድሮስ ታሪክ ፣ ኢኖ ሊትማን ያሳተሙት ገጽ 5 — 6
* ማኅበረ ሥላሴ ገዳም የሚለም አለ ።



እንዳሳለፉ ፣ ገዳሙ የደጃች ማሩን ሽፍትነት ለመደምሰስ በመ
ጣው በራስ ይማም ጦር የተወረረ ጊዜ ፣ ትምህርታቸውን ማቋረጥ
ግዴታ ሆኖባቸው ፣ ከዐሥር ዓመት እስከ ሠላሳ ዓመት ድረስ ያለ
ውን (1822 — 1840) ጊዜያቸውን በቅድሚያ ባጐታቸው በደ
ጃች ክንፉ ፣ ከዚያም በልጃቸው በልጅ መኰንን ቤት ፣ ቀጥሎ
ከአቶ ቢተዋ ዘንድ ፣ ከዚያ እንደ ገና ከልጅ መኰንን ጋር ተደ
ባልቀው ሳሉ፣ በመጨረሻ ለጐጃሙ ባላባት ለደጃች ጐሹ አሽከርነት
በማደር አሳልፈውታል ። በዚህም የዝውውር ወቅት ከየኅብረተሰቡ
በያይነቱ የሥነ ሥርዓት ፣ የንግግር ፣ የጦርነት ዕቅድ በልዩ
ልዩ መንገድ ለመጭው ዕድላቸው ጠቃሚም ሆነ ጐጂ ትምህርት
ቀስመዋል ማለት ነው ።



የጐንደር ከተማ
(ከወልደማዩር ቲዎፊል መጽሐፍ)

# ምዕራፍ ሦስት

## ከአሽከርነት ወደ ሸፍተነት

እንግዲህ ካሣ ኃይሉ ባለፈው እንደ ተመለከተው ፤ በቋራ ተወልደው ፤ በቸንከር ተክለ ሃይማኖት በትምህርት ካሳለፉና ለደጃች ክንፉ ፤ ቀጥሎ ለልጃቸው ለመኰንን የወንድም አሽከር ሆነው ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ፤ በመካከሉ ደጃች ክንፉ ሲሞቱ ቴዎድሮስ ከሙሉ ሰውነት ደርሰዋል ። የተወለዱት በ1811—12 ሲሆን ፤ ደጃች ክንፉ ታመው የሞቱት በ1841 ዓ. ም.[1] ስለ ሆነ ፤ ክንፉ በሞቱበት ሰዓት ካሣ የ29 ወይም የ30 ዓመት ጐልማሳ ናቸው ማለት ነው ። ያቶ እንግዳ ወርቅንም ልጅ አግብተው ባለትዳር ሆነው ፤ ከኝህ ስማቸውን ከማናውቀው ሴትዮ ልጅ ይውለዱ ፤ አይውለዱ እኚህ ሴት የነመሸሻ ወይም የነተሰማ የነአልጣሽ እናት መሆናቸውን ፤ አለመሆናቸውን አናውቅም ።

ቴዎድሮስ በዚህ ዕድሜያቸው አካባቢ ላይ ፤ ከደጃች ክንፉም ከልጅ መኰንንም ፤ ካቶ ቢተዋም ፤ ከደጃች ጐሹም አሽከርነት ነጻ ሆነው ፤ ሥልጣን ለመያዝ ወደሚያስችላቸው ወደ ሽፍትነት እንደ ተሠማሩ ጸሐፊዎቹ ተስማምተውበታል ።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሽፍትነት ሥራ በተለይ በዚያን ዘመን እንደ ወንድነት ሞያ እንጂ ፤ እንደ ወንጀል እምብዛም ስለማይቈጠር ፤ አንዱ መኰንን በደጅ ጥናትና በሕጋዊ መንገድ ያላገኘውን የጋብቻ ወይም የሹመት መብት ብዙ ጊዜ ከሽፍትነት በኋላ ያገኘዋል ። የመንግሥቱ አቅዋም ደግሞ ዐልፎ ፤ ዐልፎ እየደከመ ለሽፍታ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል ። 'ባንድ ንጉሥ ዘመን የመሶብ አቀማመጤ ከነእገሌ በታች ሆኖ ተዋረድሁ፤

1 La Chrenaca Reale..........pp. 82-83 የተወለዱበት ዘመን በዚሁ በ11 እና በ12 አካባቢ ሲሆን ከዚህ የሚያሳንሰው አለ ።

ለእገሌ እንደዚህ ያለው ማዕረግና ሹመት ሲሰጥ የኔ ግዛት የኔ ሹመት አነሰ ፥ እገሌ ራስ ደጃዝማች ሲባል እኔ ቀረብኝ ፣ እያለ በሸፍትነት የኖረው ፥ በሚቀጥለው ንጉሥ ዘመን በሸፍትነቱ በመቀጣት ፈንታ ፥ ታርቆ ገብቶ የተመኘውን አግኝቶ የንጉሥ ባለሟል ፥ የመንግሥት ባለሥልጣን ይሆናል ።

በዚህም ላይ ማዕከላዊው መንግሥት በተለይ በዘመነ መሳፍንት ፥ በማናቸውም ጊዜ በየአውራጃው ነዋሪ ወታደር እያስቀመጠ ፥ ላስቀመጠው ወታደር በየጊዜው ስንቅና ትጥቅ እያቀበለ ፥ የየአውራጃውን ጸጥታ በቁጥጥሩ ውስጥ አድርጎ ለረዥም ዘመን መቆየት ያቅተዋል ። ንጉሥ ሞቶ ንጉሥ በተተካ ቁጥር ይነስ ይብዛ ፥ በዙፋን ባላንጣዎችና በየደጋፊዎቻቸው መካከል ግርግር ሁካታ ፥ አንዳንድ ጊዜ የርስ በርስ ውጊያ ስለማይቀር ፥ ይኸው ወቅት ለሸፈተ ወይም ሊሸፍት ላቆበቆበ አመቺ ሁኔታ ይፈጥርለታል ። በፖለቲካ የሸፈተውን መስፍንና መኰንን ሰው ገድለው ወይም ሰርቀው ወንጀል የሠሩት ፥ በቅድሚያ በዘረፋ መሠማራት የሚወዱ ጉበዛዝት ወንበዴዎች ይከተሉታል ። በየወረዳው ያለው ያልቀናው በረሃና ጫካ ከመንግሥት ቁጥጥር ለመደበቅ ያግዛል ።

በዚህ ምክንያት ፥ ታላላቆቹ መሳፍንት ዋንዬው ራስ ዐሊ ዐልፎ ፥ ዐልፎ ከስሜኑና ከትግሬው ገዥ ከደጃች ውቤ ፥ በደቡብም ከነደጃች ጉሹ ሲጋጩ ሲዋጉ ፥ በመካከሉ በየጫካው ፥ በየበረሃው የሸፈተውን ለማሳመን የማደኑን ጉዳይ እንደ ሁለተኛ ተግባር ይቈጥሩታል ። እንግዴህ በዚህ ወቅት ነው ፥ አለቃ ዘነብ እንደሚዘረዝሩልን ፥ ካሣ ከደጃች ክንፉ ሞት ወዲህ የራስ ዐሊ እናት እቴጌ መነን የሣልሳይ ዮሐንስ ባለቤት ደምቢያን ከፍርቃ በመለስ የራሳቸው ግዛት (ማድቤት) አድርገው ፥ ስለ ርሳቸው (ምስለኔ) አቶ ሲባሉ የቆዩትን ደጃዝማች ቢተዋን የሾሙት ። ካሣ ለቢተዋ ጭፍራ ሆነው ሳለ እቴጌ ፥ ቢተዋን በኋላ ስላሰሩዋቸው ፥ ካሣ ወደ ቋራ ሸሽተው ሸፈቱ ።

በመጀመሪያ በሸፍትነት የተደባለቁት ከእቴጌ መነን ተጣልቶ ከሸፈተው ከይልማ ወሰን ጋር ነው ። ካሣ ወደርሱ ሔደው በተገናኙ ጊዜ ፥ «አይዞህ ያውራዬ ልጅ ፥ የዕንጨት ፍሬ በልተን እንኖራለን» ብሎ ይልማ ወሰን እንዳጽናናቸው አለቃ ዘነብ ያረጋግጣሉ ።[1] ከዚሁ አያይዘው ፥—

1ኛ. 12 ሰው ጭፍራ እንደያዙ 70 ከሚሆኑ ቀማኞች ጋር እኔም የቀማሁትን ፥ እናንተም የቀማችሁትን እኩል እንካፈላለን ብለው ከተዋዋሉ በኋላ ፥ እነዚያ «እርሱም ለራሱ ይቀማ ፤ እኛም ለራሳችን እንቀማለን» ብለው እንደ ከዱዋቸው በሰሙ ጊዜ ፥ 12ቱን ወታደሮቻቸውን እንደ ያዙ ወደ ሰባው ሽፍቶች ሔደው ፥ «እናንት ሐሰተኞች! ለምን ከዳችሁ» ብለው ጕራዴ መዘው ያዘው ባሉ ጊዜ የቀሩት ሲሸሹ ሰባቱ መማረካቸውን ፥ የተማረኩትን ሰባቱንም ተጉልበት ተጉልበታቸው ላይ እንደ ቆረጡዋቸው ፥ በዚህም ይልማ ወሰን ተቀይሞ እንደተለያቸው ፤

2ኛ. በማባበል ጭምር 30 ጭፍራ አግኝተው ፥ ወደ ቱምጎ (የቋራ ቆላ) ወርደው ፥ በድምሩ 45 ወታደር ይዘው ገንደዋ ቆላ ወርደው ፥ ሰባት ነጋድራስ ለንግድ የሚጓዝ ከሰፈረበት ደርሰው ፥ አደጋ ጥለው ፥ ብዙ ከብትና ብር በዘረፋ እንዳገኙ ፤ በዚህም ወታደራቸው ደስ እንዳለው ፤

3ኛ. ከዚያ እያደር የወታደራቸው ቁጥር ከ30 እስከ 300 ደርሶ ኢድሪስ ከሚባል የመተማ እስላም (ግንጃር) ጋር አምባላይ ወደሚባል አገር (ሱዳን ጠረፍ) ዘምተው ፥ በመንደሩ ላይ አደጋ ጥለው 600 የሚሆን ሻንቅላ ፥ ብዙ ፍየልና በግ ፥ ላም ማርከው ሲመለሱ አምስት ቤት አገው (*) አደጋ ጥሉባቸው ሰዋቸው መሸሽ ከጀመረ በኋላ ፥ እርሳቸው በርትተው በመዋጋት 360 የአገው ተወላጅ እንደ ማረኩ ፤ የተማረኩትንም ለምን

---

1 ኢኖ ሊትማን ያሳተመው ገጽ 7

* ሰባት ቤት አገው ከሚባለው አምስት ብቻ ማለት ነው ። ያሉበት አውራጃ ፥ አገው ምድር ፥ ከደምቢያና ከቋራ በስተደቡብ ፥ ከጐጃም በስተሰሜን ነው ።

ወጋችሁኝ የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡላቸው ፤ «እርስዎ እንዳሉ አላወቅንም ፤ እኛ የመጣነው ኢድሪስን ለመውጋት ነበር» ብለው እንደ መለሱ ፤ በዚህ ጊዜ ካሣ ፤ «ኢድሪስ የኔ አይደለም?» ብለው ኢድሪስን አስጠርተው በዐረብኛም ፤ በዐማርኛም በማነጋገር ፤ «እኔ ምርቱን አፈስሁ (ዋንኞቹን ገደልሁ) አንተ ግርዱን እፈስ» ብለው ፤ ሁለት መቶውን የአገው ተወላጅ መርጠው እንደ ሰጡትና ሁሉንም በሠይፍ እንዳስመታቸው ጸሐፊው አለቃ ዘነብ ያመለክታሉ ።[1]

በዚህ ዐይነት ፤ ካሣ በሽፍትነት ሳሉ በቀላል ጥፋትም በከባድ ሁኔታ መቅጣት ልማድ አድርገው ነበር ማለት ነው ። በመዠመሪያው በቋራ የሽፍትነት ጊዜያትው ፤ «ያውራዬ ልጅ አይዞህ! የዛፍ ፍሬም ቢሆን በልተን እንኖራለን» ብሎ ያጽናናቸውን ይልማ ወሰንን በዚሁ የጭካኔ አያያዝ አስቀይመውት እስከ መለያየት ደርሰዋል ። እርሱም ሲለያቸው ከትውልድ አገራቸው ከቋራ ወደ ቱምኃ ቆላ ወርደው ደረሰ አቡ ከሚባል ጋር በመተባበር ሽፍትነታቸውን አጸኑ ።

ብዙ ሰዎች ፤ ዐፄ ቴዎድሮስ ማንኛውንም ጥፋተኛ በከባድ መቅጣት የዠመሩት ከነገሡ በኋላ ፤ ሕዝቡን ወደ ሥልጣኔ ልምራህ ሲሉት ፤ አልመራም እያለ ስለ አስቸገራቸው ከዚሁ የተነሣ መሆኑን ያምናሉ ። በሦስቱም ደራሲያን ጽሑፍ ላይ ሠፍሮ የምናገኘውና ወደፊት እንደምናነበው አሁንም እንዳነበብነው ፤ የካሣ በተቃራኒዎቻቸው ላይ ከባድ እርምጃ የመውሰድ አቋም የዠመረው ፤ ከንግሣቸው በፊት መሆኑ በግልጽ ይታያል ።

የሆነ ሆኖ ፤ ካሣ በቋራና በአካባቢው እስከ መተማ ጠረፍ ድረስ ባለው አገር በሽፍትነቱ ወቅት ፤ ከዚያም ከዚህም የዘረፉትን ገንዘቡንም ፤ ከብቱንም ለጭፍሮቻቸው በማደል ወታደራዊ አቅዋማቸውን አጠናከረዋል ማለት ነው ። ኢድሪስ የሚባለው በመተማ ጠረፍ በሱዳን በኩል ፤ በኢትዮጵያም በቋራ ቆላ ባሉት

1 The Chronicle of King Theodore ... Eno Littmann ... pp. 5-10



ሸንቅሎች መካከል በሽፍትነት የታወቀው ለርሳቸው ታማኝ አገልጋይ ሆኖ በበኩሉ የዘረፈውን በግመል እየጫነ ግርም ፤ ቅቤም ፤ እህልም ከብትም እያመጣ በመገበር ዋና ታማኝና ታዛዥ ሆኖላቸዋል ። አንዳንድ ጊዜም ምንም ሽፍታ ቢሆኑ በሽፍትነት የያዙት ቋራና አካባቢው ያው የትውልድ አገራቸው ፤ ሕዝቡም ወገናቸው ስለሆነ ፤ ከዘረፉና ከውጊያ የሚያርፉበትን ጊዜ ለልማት እንደሚያደርጉት ይታያል ።

የቋራና የአካባቢው አገር ፤ በተለይ ከባላባቶቹ ከነደጃች ክንፉ ሞት ወዲህ ሽፍታ ስለ በዛበት ፤ መሬት የሚያርሰውና የሚቆፍረው አጥቶ እህል በመጥፋቱ ባገር ላይ ረኃብ ተነሥቶ ኖሮ ፤ በ200 ግመል እህል ጭኖ ኢድሪስ ስላመጣላቸው ፤ ካሣ ያንዱን ግመል ጭነት ለሁለት ለሁለት ሰው እንዳደሉ ፤ ወታደሩም ያገኘውን ጉድጓድ እየቆፈረ እንዲያስቀምጥ ፤ ባላገሩም ጫካውን እየመነጠረ እንዲያርስ ወይም እንዲቆፍር እየመከሩ ፤ ለዶማ መግዢያም ገንዘብ እየሰጡ ፤ ራሳቸው ምሳሌ ሆነው አብሮ በመሥራት ፤ በቋራ የልማት ሥራ ማከናወናቸውን ጠቅሰው ፤ በዚሁ ጊዜ ያቶ እንግዳ ወርቅን ልጅ አግብተው ፤ ወህኒን ወግተው ፤ በዚህ በወህኒ ያለውን የእቴጌ መነንን ጦር ቀድሞ የነበረውንም ፤ በኋላ ለእርዳታ የተላከውንም ጦር በታትነው በጣም ኃይላቸው ስለ ታወቀ ፤ እቴጌ መነን በኃይል የመደምሰሱን መንገድ ትተው በጋብቻ እንደዚህ ያለውን ጉበዝ ለመያዝ እንደ ፈለጉ ጸሐፊዎቹ ያረጋግጣሉ ።[1]

1 የቴዎድሮስ ታሪክ አለቃ ዘነብ ገጽ 5—10 ፉዜላ ያሳተሙት ያፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ገጽ 1—2

# ምዕራፍ አራት

## ከሽፍትነት ወደ ጋብቻና ከለማችነት ወደ ሹመት

በኢትዮጵያም ፡ በመላው ዓለምም ጋብቻ በተለይ በዚያ ዘመን ዋና የፖለቲካ ገበያ ፡ ያስተዳደር ሽቀጥ ነበር ። አንዱ ንጉሥ የጐረቤቱን አገር የመጠቅለል ምኞት ሲያድርበት ፡ የዚያን አገር ንጉሥ ሴት ልጅ ለወንድ ልጁ ዳርልኝ ወይም ያንተ ወንድ ልጅ ወይም ወንድምህ የኔን ልጅ ፡ የኔን እኅት ያግባ ብሎ ይጠይቃል ። ያኛውም በበኩሉ የግሉን ምኞት ደበቅበቅ አደርጎ ጋብቻውን በደስታ ይቀበላል ። ወደፊት ግን ፡ በዚህ ጋብቻ ተጠቅሞ ወደ ሥልጣን የመውጣቱ ወይም የጐረቤትን አገር ወደ ራሱ ጠቅልሎ ዝናን የማግኘቱ ፡ ወራሲን እስከ ልጅ ልጅ የመመሥረቱ ጉዳይ እንደ ሁለቱ የፖለቲካ ዘዴኛነትና ጠረኛነት ነው ። ከሁለቱም ችሎታ ጐን ያጋጣሚው ምክንያት ያንደኛውን ፍላጎት አቃውሶ ፡ የሁለተኛውን ሊያሣምርለት ይችላል ።

አንዳንዱ ደግሞ ፡ በቁርባን ያገባት ሚስቱ ምንም በደል ሳይገኝባት አልጋ የሚወርስ ፡ በዘር የሚተካ ልጅ እንዳጋጣሚ ሳትወልድ የቀረች እንደሆነ ወይም የርሷ ጋብቻ ግዛት ለማስፋፋት የማይጠቅም ሆኖ ሲገኝ ፡ እርሷ ከሞቀና ከደረጀ ቤቷ ተባርራ ሌላዋ ትገባለች ። ለዚህ የፈረንሣዊ ንጉሠ ነገሥት ናፖሊዎን (1769—1821 እ. አው. ቁ.) የወጣትነት ሚስቱን ራሱ በእጁ ዘውዷን ደፍቶላት ፡ በ1796 ዓ. ም. ከርሱ ጋር ያነገሣትን ዤዚፊን ቦሐርኔ የምትባለዋን ፡ በፈረንሣይ አገር ከጨዋ ቤተ ሰብ የምትወለደዋን ፡ በዚያ ሁሉ ፍቅራቸው መካከል ያለምንም ኃፍረት ፡ «ፈትቼሻለሁ» አላት ። ዤዚፊን ይኸን ቃል ከባሏ ስትሰማ ደንግጣ በመፍዘዝ ወደቀች ። የእልፍኝ አሽከሮች አንሥተው ፡ ደጋግፈው ፡ ወደ መኝታዋ ወሰዷትና በኋላም በርሱው አስገዳጅነት የፍቺው ውል በ1809 ዓ. ም. ተፈጸመ ።

ከዚያ ለግዛቱ ምኞት ምንም ወሰን የሌለው ፡ ከድል ወደ ድል በመራመድ ግሕል አውሮፓን በመዳፉ ውስጥ ያገባው ናፖሊዎን ፡ በምሥራቅም በመስኮብ አገር ላይ ለመስፋፋት ሲል ከጴጥሮስ ሦስተኛና ከታላቂቷ ካተሪን ልጆች ፡ ከጳውሎስና ከማሪያ ሼደሮቭና የምትወለደዋን ፡ የቀዳሚ እስክንድርን እኅት ፡ ካተሪንን ፡ ለማግባት ቢጠይቅ ፡ እርሱ አትወልጅም በሚል ሰበብ የገዜዜፊን ዘር ንቆ እንደ ፈታት ፡ የርሱንም ዘር እነርሱ ንቀው ውስጡን ፡ «ለዚህ ለኮርስ (ለኮርሲካ) ዕብድ አንድርም» ብለው ፡ ላዩን ግን በልዩ ልዩ ምክንያት አለባብሰው ሳይፈቅዱለት ቀሩ ። አሁንም እርሷ ካልሆነች ታናሽ እኅቷን ሐናን ፡ ላግባ ብሎ የዐርባ ዓመቱ ጕበዝ የዐሥራ አምስቷን ዓመት ወጣት ስጡኝ ቢል ፡ ሰውዬው በዚህ ጊዜ ምንም እንኳን የሚመከተው ጠፍቶ ብዙ የአውሮፓ ነገሥታት የተንበረከኩለት ፡ የድል አድራጊነቱ ኮከብ ያበራበት ጊዜ ስለ ነበረ ፡ እምቢታውም አስፈሪ ፡ እሺታውም የማይዋጥ ሆኖባቸው በነገሩ ተቸግረው በመጨረሻ ፡ «ሐና የ15 ዓመት ለጋ ወጣት ናት ፤ የፈረንሣይ ንጉሠ ነገሥት ባለቤት ለመሆን በትምህርትም ፡ በአካልም ብቁ አይደለችምና ትንሽ ከፍ ስትል ጉዳዩን ያን ጊዜ እናስብበት» የሚል ልመና ጭምር ያለበት ሰበብ ስለ አቀረቡ ፡ በዚህ በኩል ተስፋ ሲቆርጥ በሥልጣኑ ሥር የወደቀወን የአውስትሪያ ንጉሠ ነገሥት የፍራንሷ ገዜዜፊን ልጅ ፡ ማሪ ሉዊዝን አገባ ።[1] ከገዜዜፊን ይልቅ የማሪ ሉዊዝ ጋብቻ የፖለቲካ እንጂ የፍቅር ስሜት ስለ ሌለበት ፡ የተመኘውን አንድ ወንድ ልጅ ወልዳ በጨቅላነቱ የሮማ ንጉሥ ከተባለ ወዲህ ፡ ናፖሊዎን በምትወደው በገዜዜፊን ጊዜ የቀናውን ያህል ፡ በምትንቀው በማሪ ሉዊዝ ጊዜ የድል መሆንና የግዞት ዘመን ሲጎጥመው ፡ ሴትዮዋ ዘወር ብላም ሳታየው ከምትወደው ከሌላ ሰው ጋር ዘመኗን ፈጸመች ።

አንዳንድ ጊዜም ፡ ነገሥታቱ በውስጣቸው ያለ መኵንን ወይም ከውጭ ጊዜ ላነሣው መስፍን ለምነው አባብለው ፡ «ልጃችንን ወይም እኅታችንን ሰጥተንሃል» እያሉ እያጋቡ ፡ በዚህ ጋብቻ አልገዛም ብሎ የሸፈተውን ፡ ወይም ለመሸፈት ያፈነገጠውን ወይም በሁኔታው ፡ በዘሩ ወደፊት ሊነግሥ ይችላል ብለው ያመኑበትን ለመሳብ ይሞክራሉ ። በኢትዮጵያም

1 Alexandre Ier - H. Troyat - pp. 170 - 175



ወደፊት እንደምናነበው ፡ ካሣ ከነገሡ በኋላ ሴት ልጃቸውን ፡ አልጣሽን ፡ ከወጣቱ ከምኒልክ ጋር ያጋቡት ፡ ዐፄ ዮሐንስ የምኒልክን የስምንት ዓመቷን ልጅ ፡ ዘውዲቱን ፡ የ12 ዓመት ዕድሜ ላለው ልጃቸው ለራስ አርአያ ሥላሴ ያጋቡት ፡ በኋላም ምኒልክ ሸዋ ረጋን ልጃቸውን ለወሎው ባላባት ለራስ ሚካኤል የዳሩት ፡ እንደዚሁም ራስ መንገሻ ዮሐንስ በየጊዜው እየሸፈቱ ስለ አስቸገሩ ፡ በጋብቻ ገመድ አስሮ ለማስቀረት ሲሉ የእቴጌ ጣይቱን የወንድም ልጅ ፡ ወይዘሮ ከፈይ ወሌን ፡ ከደንበኛ ባላቸው ከራስ ናደው በግድ አፋተው የዳሩላቸው ከዚሁ ከፖለቲካ ጋር የተያያዘ መሆኑ ግልጥ ነው ። ዳሩ ግን የራስ መንገሻን ውስጣዊ ስሜትና የዙፋን ምኞት የቆንዦዋ የወይዘሮ ከፈይ ጋብቻ አላበረደውም ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ፡ አሁን ካሣ ለጋብቻው የቋራ ባላባትነታቸው የሚያኮራ መሆኑ ቢታወቅም ፡ በዚህ ላይ በቋራና በደምቢያ ጭፍራቸው እየበረከተ ፡ ስማቸው እየገነነ በሔደበት ዘመን ፡ እቴጌ መነን ፡ ለስሙ የነገሡት ዐፄ ዮሐንስ ፡ ዋናው እንደራሴ ራስ ዐሊ ፡ መክረው ዘክረው በመዠመሪያ የሸፈቱበትን የራሳቸውን የትውልድ አገር ቋራን ለግዛት መርቀው ፡ ተዋበችን የማግባቱ አሳብ ተወጠነ ። በዚህም ጊዜ ካሣ ወደ መተማ ዘምተው ከግብጽና ከቱርክ ወይም ካገር ተወላጁ ጋር በዚያው ባገኦታቸው በደጃች ክንፉ መሥመር ገብተው እየተዋጉ ፡ ከዚያ በምርኮም በዘረፋም ያገኙትን 200 ጥሬ ብር ፡ 12 የዝሆን ጥርስ ፡ 8 ባርያ ፡ 200 መቅሙስ[1] ገጸ በረከት ስለ ላኩላቸው ፡ ያለፈውን ሁሉ የሽፍትነት ሥራቸውን ሠርዘው ፡ «ያቶ እንግዳ ወርቅን ልጅ ትተህ የኔን ልጅ አግባ» ብለው እቴጌይቱ ትእዛዝ ለበስ መልእክት እንደ ላኩላቸው ዘነብ ያረጋግጣሉ ።[2]

የርሳቸውንም አባባል ፡ ሁለተኛው የዘመኑ ጸሐፊ እንደዚህ ሲሉ በማጽደቅ ያትታሉ «..........የቋራ ባላገር ሁሉ ከልጅ ካሣ ጋር ሸፍታ ሆነ ፤ እስከ ደምቢያ እስከ ጭልጋ ጕበዝ መጣላቸው ። ከትሁሪር[3] ሻንቅላም ወዳጅ አበጁና (*) በጣም በረቱ ፤ ሲበረቱ

1 የልብስ ዐይነት (ጣቃ) ይሆን?
2 አለቃ ዘነብ ..... ገጽ 10 — 12
3 በቅማንት አቅጣጫ በሱዳንና በኢትዮጵያ ድንበር ላይ የሚገኝ የሻንቅላ ሕዝብ ነው ። ስሙ ታክሩር ይባላል ። ጕርሹ ምንታንዶን ያዘጋጀውን ጂኦግራፊ በ294 ገጽ ተመልከት ።
* ሻንቅላ ወዳጅ አበጁ የሚለው ኢድሪስን መሆን አለበት ።

ጊዜ ፤ 'እንደዚህ ያለን ጐበዝ ሹመት ሰጥቶ ፤ ልጅ ድሮ ማኖር ነው የሚገባ' ብለው የራስ ዐሊ መኳንንት መከሩና የራስ ዐሊን እኅት(*) ወይዘሮ ተዋበችን እናታቸው እቴጌ መነን አጋቡዋቸው ። ቋራም ሹመት ሊቀበሉ አምለው ገቡ.......... ልጅ ካሣ ሲገቡ ወርቅም ፤ ባርያም ይዘው ለራስ ዐሊና ለእቴጌ መነን እጅ መንሻ ሰጡ ። ከዚያ ወዲያ ምሽታቸውን አግብተው ፤ አገርም ተቀብለው ወደቋራ ወረዱ ። ባገራቸው ብዙ ቀን ተቀምጠው ፤ የቋራ ግብር አውጥተው ተመልሰው ወደ ጉንደር መጡ ። ለእቴጌ መነን ግብር ሰጡ ። ለመኳንንቱም ብዙ ማቆላመጫ (ማባበያ ፤ ጉቦ) ሰጡ ። በሠፈሩ ሁሉ 'ልጅ ካሣ ፤ ልጅ ካሣ' እያለ ሁሉ ወደዳቸው ።»[1]

በዚህ መካከል ስለ መዠመሪያ ሚስታቸው ፤ ስላቶ እንግዳ ወርቅ ልጅ ሁኔታ ጸሐፊው ሁሉ ይዘለዋል ። ናፖሊዎን በዦዜፊን ላይ እንዳደረገው ፤ «ምን ይደረግ ለሹመት ፤ ለዕድገት የራስ ዐሊ ልጅ ታስፈልገኛለችና ደኅና ሁኝ» ብለው ፤ ደሞዝና ርስት ሰጥተው ያሰናብቷት ወይም በተዋበች ላይ ደርበው እንደ ዕቁባት አድርገው ያስቀምጧት በትክክል አናውቅም ።

የሆነ ሆኖ ፤ የዚህን ጋብቻ ጉዳይ ሦስተኛው ጸሐፊ ወልደ ማርያም ለየት አድርገው እንደዚህ ሲሉ ይተርካሉ ። «ከትምህርት ቤት ገብተው ፤ ዳዊት ደግመው ፤ ወታደርነት ከደጃች ጐሹ ሔዱ ። ከዚያም ኑረው ተመልሰው ፤ ከራስ ዐሊ ቤት ገቡ ። ሰዎችም 'ከዚህ ኑር ፤ ምሽት አግብተህ' ቢሏቸው 'የራስ ዐሊን ልጅ አግባ እንደሆነ' አሉ.......... 'የራስ ዐሊን ልጅ ላንድ ወታደር ስጡ ብሎ ማን ይደፍራል?' ሲሉ ሁለት ሰዎች ወዳጆች የሆኑ ለራስ ዐሊ ገብተው ቢነግሩ ፤ 'የኔን ልጅ አንድ ወታደር እንዴት ደፈረ' ብለው ተቆጡ ። እናታቸው ወይዘሮ መነን ግን ፤ 'ክርስቶስ ባለው ይሁን ፤ እንስጠው ፤ በሀብቱ ያሳድራት' ብለው ሰጡዋቸው ።»[2]

---

* ተዋበች የራስ ዐሊ ልጅ እንጂ እኅት አይደሉም ። ለእቴጌ መነንም የልጅ ልጅ ናቸው ።

1 ያጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ፋዚላ ያሳተመው ገጽ 3

2 ያጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ም. ቪዳዬ ያሳተመው ገጽ 1—2



ሦስቱም ጸሐፊዎች የአተራረካቸው መንገድ ይለያይ እንጂ ፤ ልጅ ካሣ በቋራና በአካባቢው እስከ መተማ ድረስ እየዘመቱ የኢትዮጵያን ጠረፍ በመቈጣጠር ጐን ፤ ከዘመቻው በዘረፉ ያገኙትን ለእቴጌ መነንም ፤ ለየመኳንንቱም እያደሉ ፤ በራሳቸው ሽፍትነት ከደንበኛው ሹመት በፊት በተግባር የቋራ ገዥ ሆነው ሳለ ፤ የማዕከላዊው መንግሥት መሪዎች ራስ ዐሊና እናታቸው ተማክረው ፤ 'እንደዚህ ያለውን ጉልማሳ መኰንን የቋራን ሹመት ሰጥተን ልጃችንን ድረን ወደኛ ብንስበው ይሻላል' ብለው ልጃቸውን ተዋበችን እንደ ዳሩላቸው ሦስቱም ጸሐፊዎች ይስማማሉ ። በመዠመሪያ የተጋቡበት ዘመን 1838 ዓ. ም. መሆን አለበት ።[1] በኋላ ደግሞ በ1847 ዓ. ም. ሲነግሡ ሁለቱ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሥነ ሥርዓትና በቁርባን አጽድቀዋል ።

ነገር ግን ፤ የካሣ ምኞት እንደ ናፖሊዮን ረዥም ስለሆነ ፤ ምንም እንኳን ነገሩን በየደረጃው ፤ በየወቅቱ ለመፈጸም ጊዜውን በመጠበቅ ፤ አሁን ግን የመስፍኑን ልጅ ተዋበችን ማግባታቸው ደስ ብሏቸው ሳለ ፤ እቴጌይቱና ራስ ዐሊ ግን ፤ የካሣን ሁኔታና ሰፊ ምኞት ለማወቅ ሲሉ ፤ በቋራ ሹመት በበላያቸው ሆኖ የሚቈጣጠራቸው ደጃች በለውን ስለ ሾሙባቸው በካሣ ዘንድ ቅርታ ገባ ። የጋብቻውም ወጥመድ ብቻውን ለማገልገል ምንም ዐይነት ዐቅም አላገኘም ። በጋብቻውም ከነራስ ዐሊ ይልቅ ተዋበችን በፍቅር ስበው ፤ የራሳቸው ታማኝና አገልጋይ በማድረግ ራሳቸው ከመጠቀም በቀር ልጃቸውን አገባሁ ብለው በመኩራራት ከራስ ዐሊም ፤ ከእቴጌ መነንም ተዋግተው የመሪነት ዓላማቸውን ለመተው አላመኑቱም ። ስለዚህ የጋብቻ እግር ብረት አብዛኛውን ጊዜ የማንንም ዕድል ያሰራል ለማለት ያስቸግራል ።

ደግሞም ፤ መስፍኑ ራስ ዐሊ ልጃቸውን ላንድ ተራ ሺፍታ ሰጡ ያሰኘው የጊዜውን ሁኔታ በመመልከት ነው እንጂ ፤ ከላይ የዘር አመጣጥ የተመለከትን እንደሆነ ፤ በቋራ የደጃች ክንፉ ባላባትነት ከላይ ከነእቴጌ ምንትዋብ (ያፄ በካፋ ባለቤት) የወረደ ስለሆነ ፤ የባላባትነታቸው ደረጃ ከነራስ ዐሊ ፤ ከየጁና ከወሎ ባላባትነት አያንስም ። በዚህም ላይ ከነጋሚዎቹ ከነዐፄ ፋሲል ትውልድ እንዳላቸው የሚያረጋግጡ አሉ ።

---

1 A Chronology of Menilek II.........Ch. P. Rosenfeld p. . 3

# ምዕራፍ አምስት

*ክሶና ታላቁ የብልት ሥጋ — የልጅ ካሣ ቀያሚና የመጨረሻው ሽፍትነት*

የኢትዮጵያ ሰው፣እርጥብ ሥጋ መብላት ካዘወተረ ዘመኑ ራቅ ያለ ነው ። በቃል እንደሚተረተው፣እርጥብ ሥጋ መብላት የተዠመረው በግራኝ አህመድ ወረራ ጊዜ (16ኛው መቶ ዓመት) ሕዝቡ በዕንጨት ሥጋ እያበሰለ ለመብላት ሲሞክር፣የጠላት ጦር እሳቱንና ጭሱን በሩቅ እያየ ማጥቃት ስለ ዠመረ ፣ ከዚህ ለመዳን ሕዝቡ እርጥቡን መብላት ለመደ ይባላል ። ነገር ግን ከዚያ በፊት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት ዐፄ ዳዊት (1375—1404) የበግ ጨጓራ እርጥቡን ሲበሉ ታይተዋል ።([1])

የሆነ ሆኖ ፣ ከሌላው መብል ከዶሮና ከበጉ ወጥ፣ ከአልጫው፣ ከዝግኑ ፣ ከምንቸት አብሹ ጾዋትወ መብል በኋላ በመጨረሻ መደምደሚያው እርጥብ ሥጋ ነው ። እርሱም ከታረደው ሠንጋ ብልት አወጣጡ ወግ አለው ፤ ከዚያም ለየመሳፍንቱ ፣ ለየመኳንንቱ መሶብ በግብር ቀን የሚቀርበው የብልቱ ሥጋ ደረጃ ደረጃ አለው ። በጣም ከበር ላለው ሽንጥ ፣ ከዚያም ታናሽ ፣ ጉድን ተዳቢት ፣ ቤተ ሳልገኝ እያለ በተዋረድ ይቀርብና ይበላል ።

ይኸው እርጥብ ሥጋ ከተበላ ዘንድ በሆድ ውስጥ ሲቆይና ሲያጋጥም ትል መፍጠሩ የተለመደ ስለሆነ ፣ ይኸም ትል በሆድ ውስጥ ሲቆይ ለጤንነት አደጋ ማምጣቱ ስለ ታወቀ ፣ ሰዉ ላፄ ቴዎድሮስ እናት መሰደቢያ ምክንያት የሆነውን የኮሶን ዛፍ ፍሬ መድኃኒትነቱን አምኖበት፣ ሁሉም ይኸው ትል በታየ ጊዜ ፍሬው ተለቅሞ ሲደርቅ ተፈጭቶ ፣ ተልሞ ፣ በውሃ ተበጥብጦ በዋንጫ ወይም በብርጭቆ ተለክቶ በባዶ ሆድ ይጠጣል ። ባለ ቤት ሲጠጣ ሚስቱን ፣ ሚስት ባሏን ፣ ልጆች አባትና እናቶቻቸውን

---

1 የግራኝ አህመድ ወረራ ተ.ጸ.መ — ገጽ 88

ይሰናበታሉ ። እንደዚሁም መኳንንቱ ከግዛታቸው ለደጅ ጥናት መጥተው በከተማ ፣ በቤተመንግሥት አካባቢ በሚገኙበት ሰዓት ትል የተጣባቸው እንደሆን እንደ ደረጃቸው ንጉሡን ፣ ንግሥቲቱን ፣ ጭፍራም እንደሆነ አለቃውን ይሰናበታል ። ይሰናበታል ማለት 'ደህና ሁኑ' ብሎ ይሔዳል ማለት ሳይሆን ፣ዛሬ ኮሶ ስለ ጠጣሁ በሻርሁ ጊዜ ምግቤን ከናንተ ወይም ከአንተ እጠብቃለሁ ማለት ነው ።

የቆሎ ተማሪ እንኳን ከአገሩ ተሰዶ ለትምህርት ጉጃም ፣ ጐንደር ፣ ዋድላ ፣ ትግሬ ፣ ሸዋ (አንኮበር) በመጣበት ሰዓት ኮሶ ተጣባኝ (ታየኝ) ብሎ ለመምህሩ የነገረእንደሆነ ፣ መምህሩ ወደ አንድ ቤተሰብ እንዲጋበዝ አደራ ብለው ይልኩታል ። ቤተሰቦችም ኮሶ የጠጣ ሰውን ሲያሽረው መጋበዝ ያገር ባህል ስለሆነ ፣ ያለቅርታ የተቻላቸውን ያህል አብልተውና አጠጥተው ለዚያ ቀን ያስተናግዱታል ። ኮሶው ለመጠጣት መራራ ስለሆነ ልጆች ጨክነው እንዲጠጡ ፣«ዶሮ ማታ! ዶሮ ማታ!» እያሉ አባትና እናት ያደፋፍሯቸዋል ። ይኸውም ማለት ፣ 'ደፍረህ ብትጠጣውና ቢያሽርህ ፣ ማታ የዶሮ ወጥ ተሠርቶ ትበላለህ' ማለት ነው ። መካከለኛ የሀብት ደረጃ ያለው ሁሉ ኮሶ የጠጣለት ወደ ማታ ሲያሽረው የዶሮ ወጥ በእንጀራ ይጋበዛል ።

እንደዚሁ አንዱ መኰንን ወይም መስፍን ፣ ኮሶ ተጣብቶኝ መድኃኒት ጠጥቻለሁ ብሎ በቃል ወይም በመልእክት የተሰናበተ እንደሆነ ፣ ከቤተ መንግሥት የሚላክለት መስተንግዶ እንደ ሰውዬው የክብር ደረጃ ነው ። ሙሉ ሠንጋ ወይም መሲና ላም ፣ አለዚያም ዝቅ ሲል የበግ ሙክት ፣ ከዚያ ደግሞ በጣም ሲዋረድ አንድ የብልት ሥጋ ይላክለታል ። ካሣ ለሽፍትነት ያበቃቸው ከዚህ ወራዳ መስተንግዶ ላይ ነው ።

ካሣ ተዋበችን ከአገቡና አማች ከሆኑ በኋላ ፣ በተለመደው መንገድ ደጃዝማች ተብለው ቋራን ብቻ ሳይሆን ዋናውን ደምቢያን ሊሾሙ በተገባ ነበር ። ነገር ግን ፣ ከተጋቡ ወዲያ በነራስ ዐሊ በኩል የታየው ቸልታ ዱሮውን ካሣን ከሽፍትነታቸው ሥራ ለማስጣልና አደገኛ መስሎ የታየውን እንሣሣቸውን ለማጨንገፍ እንጂ ፣ ልባዊ እንዳልነበረ ሁኔታው ያመለክታል ። በዚህ



መካከል በቋረኞችና በወሎዎች መካከል ካዬ ኢዮአስ ዘመነ መንግሥት ዠምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ፣ በርሳቸው ዘመን የራስ ይማም ጦር በደምቢያና በቋራ ላይ ዘምቶ በማኀበረ ሥላሴ ገዳም የፈጸመው እልቂት ከካሣ ልብ እንዳልጠፋ በማስረዳት ፣ በወሎ ተወላጆች በመሳፍንቱ በነራስ ዐሊ ላይ የበቀል ነገር ይመኛል የሚል ወሬ ነጋሪ አሳብቆ የበለጠ እንዲጠሉ አድርጎ ይሆናል ። ካሣም ራስ ዐሊንና እናታቸውን በንቀት መዝለፋቸውና እነመነንም ካሣን ፣ «ቆለኛ ፣ የፍየል እረኛ» እያሉ መሰዳደባቸው በሁለቱም ወገን ዘንድ የተሠወረ አይመስልም ።

በዚህ ምክንያት ፣ልጃቸውን ድረው የቋራን ግዛት ከሰጡዋቸው ወዲህ የደንቡን ግብርና ገጸ በረከት ይዘው መጥተው ለእቴጌይቱ በማቅረብ ፣ ለየመኳንንቱም የገንዘብ ስጦታ በመስጠት አስደስተው ዝናን ስላተረፉ ፣ በንጉሣዊው ቤተሰብ ውስጥ ጥርጣሬን ፣ ፍራቻንና ጥላቻን ጭምር አሳድሮ ይሆናል ። አሁንም ያው ወይም ሌላው ወሬ ነጋሪ ፣ 'ብቻውን ወደ ሹመት አገሩ ብትመልሱት ይሸፍታል ። ስለዚህ ሌላ ሰው በላዩ ላይ ሆኖ እየተመለከተ የሚቈጣጠረው አድርጎ መልሶ መላክ ይሻላል' የሚል አሳብ አቅርቦ ፣ ጉዳዩ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ በደጅ ጥናት በጐንደር ከተማ ስንቃቸውን ፈጅተው የተከተላቸውም ሰው በረኃብ ተቸግሮ ይሆናል ።

በዚህ ምክንያት ፣ የደጃች ካሣን ያሁኑን አሽፋፈታቸውን ጸሐፊዎች በዚሁ ኮሶ አጠጣጥ ምክንያት አድርገው ይተርኩታል ። አለቃ ወልደ ማርያም በጻፉት ፣— «ወይዘሮ ተዋበችን አግብተው አማች ሆነው ሲኖሩ መድኃኒት ቀምሰው (ኮሶ ጠጥተው) 'እራቴን' ብለው ቢልኩ ወርች ሥጋ እንደ መጣላቸው 1 ልጅ ካሣም 'ወርች ሥጋ አልበላም' ብለው እንደ ተቀየሙና ሚስታቸው ተዋበች ተናደው ፣ 'አገር የለህምን? ታጠቅ ፣ እንሒድ' ቢሉ 'ምነው የለኝ?' ብለው ቋራ ተመልሰው እንደ ሸፈቱ ያመለክታሉ ።»(1) የርሳቸው አኳያ አለቃ ዘነብ የወርቹን ሥጋ ወደ ጐን አድርገው ፣ ባጭሩ «በዚያው ወራት የራስ ዐሊን ልጅ እቴጌ ተዋበችን 'ምሽት ትሁንህ' ብለው ሰጧቸው ። በሁለተኛው ዓመት ልጅ ካሣም እጅግ ተቸገሩ 1 ሰዋቸውም ተራበ ። እጅግ

1 ኢ.ና ሊትማን (ዘንባ) ገጽ 3—6 ።

በደልና መዋረድ ፣ ንቀት በመጣባቸው ጊዜ በጥቅምት በ5ኛው ቀን ሽፍትነት ወጡ» ብለው ሲያልፉ ፣ ሦስተኛው ስማቸው ያልታወቀው ጸሐፊ ያለቃ ወልደማርያምን አጭር አባባል በማጽደቅ ፣ «ከጥቂት ቀን በኋላ ልጅ ካሣ 'ኮሶ ልጠጣ ነኝ' ብለው አስፈቅደው ወደ ቤታቸው ሔደው ኮሶ ጠጡ ። ወደ ዐፄ ዮሐንስ (ሣልሳዊ)፣ የእቴጌ መነን ባል 'ኮሶ ጠጥቻለሁ' ብለው አሽከር ላኩ ። ከዚያ በኋላ ዐፄ ዮሐንስ አንድ ፍሪዳ ፣ ብዙ እንጀራና ጠጅ ሰደዱ ። እቴጌ መነን ግን ፣ ታላቅ ሥጋና አንድ ገምቦ ጠጅ ፣ 30 እንጀራ ሰደዱ » ካሉ በኋላ ፣ ይኸ ለካሣ በተደረገበት ጊዜ አንድ የእቴጌይቱ መኰንን 'ምነው፣ አንድ ፍሪዳ (ቁምከብት) ፣ አለዚያም በግ መላክ በተገባ' ቢል ፣ እቴጌይቱ 'ለቆለኛ ይህ መች አነሰው፣' ብለው በንቀት መመለሳቸውንና ይኸንኑ ካሣ ካንድ ወዳጃቸው መስማታቸውን ያረጋግጣሉ ።

በዚህ ምክንያት ከንጉሡ ካፄ ዮሐንስ የተላከላቸውን መሲናላም አርደው ከነሰዎቻቸው በልተው ፣ ከእቴጌይቱ የተላከውን ታላቅ ሥጋ በአገልግል አስይዘው ፣ በሁለተኛው ቀን ከሰዎቻቸው በምስጢር ተነጋግረው ወደ ደምቢያ ሔደው ሸፈቱ ። ደምቢያ እንደ ደረሱ ፣ «ያን የእቴጌን ሥጋ አምጣ» ብለው አገልግሉ ሲከፈት ፣ «የኔ አሽከሮች ፣ እስቲ ይኸን ሥጋ እንብላውን፣» የሚል ጥያቄ አቅርበው ሥጋውም ሸቶ ስለ ነበረ ፣ «እኔ አንድ የናቱ (እኔ የመይሳ ልጅ)........... » ብለው በቁጣ ፈከረው ፣ ሽጉጥ ተኲሰው ፣ ጐራዴ የመዘዙ ጊዜ የርሳቸው ወታደሮችም እየፈከሩ ፣ በጐራዴም በስለትም ያችን ሥጋ እየቆረጡ ወደ በረሃ እየጣሉ ፣ «እንግዲህ ሥጋይቱን እንደ ቆረጥናት እኛም ልባችን ይቁረጥ» ማለታቸውን ጸሐፊው በደንብ ዘርዝረውታል ።(1)

ባንድ ወገን ደግሞ ካሣ ፣ «ወደ አገሬ ልሒድ» ብለው እቴጌን ቢሰናበቱ ፣ እቴጌ «ቋራ የደጃዝማች አገር ነውና በላይህ የሚሾም አንድ ባለ ነጋሪት ይዘህ ሒድ» ብለው ደጃች በለውን እንደ ሰጡዋቸው ፣ ካሣም በለው በበላያቸው በመሾሙ የተሰማቸውን ንዴት በልባቸው እንደያዙ ቋራ ደርሰው ሕዝቡን በመቀስቀስ በበለው ላይ እያሸፈቱ እንዳስቸገሩ ፣ በለው በቋራ መኖር

---

1 ምንዶን ሺዳዬ (ወ/ማ) ገጽ 2 ቀዚሉ ገጽ 6



አቅቶት እንደ ተመለሰ ፣ ካሣ ግን በቋራ ቀርተው እንደ ሸፈቱ ከላይኛው አባባል ለየት አድርገው ያቀርቡታል ። ምናልባት የኮሶውም አጠጣጥ ፣ የደጃች በለውም በካሣ በላይ መሾም ባንድ ወቅት ተጋጥሞ ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ፣ የልጅ ካሣ የመጨረሻውና ወደ ዘውድ የመራቸው ሽፍትነት ከዚህ ጊዜ ላይ ይዠምራል ። እርሳቸውም «ከእንግዲህ ወዲያ ለእነ ዐሊ አልታጠቅም» ብለው ለዘለቄታ የቆረጡት ተከታዮቻቸውም ፣ «ሥጋይቱን እንደ ቆረጥናት ልባችን ይቁረጥ» ብለው በቃል ኪዳን የተባበሩዋቸው ከዚህ ጊዜ ዠምሮ ነው ። የርሳቸውን ከዚህ ጊዜ ዠምሮ ከድል ወደ ድል እየተራመዱ ፣ የተመኙትን ዘውድ ከመድፋታቸው በፊት በመካከሉ በሚስታቸው አባት በዋናው እንደራሴ በራስ ዐሊና በስሜን ፣ በትግራይና በትግረ እየተጠናከሩ በሔዱት በደጃች ውቤ መካከል የተደረገውን የግዛት ፍልሚያ ፣ ሁለቱንም ቀብተው ሊያነግሡ በሚችሉት በጳጳሱ በአቡነ ሰላማ የተነሣ ያደረጉትን ውጊያ በቅድሚያ በሚቀጥሉት ተከታታይ ምዕራፎች ውስጥ እንመለከታለን ።

# ምዕራፍ ስድስት

## በመሳፍንቱ መካከል የውጭ አገር የወዳጅነተ ሽሚያ

ከዐፄ ይኩኖ አምላክ ዠምሮ (1262—1277) እስከ ዐፄ ኢዮአስ ድረስ (1748—1762) በሕጋዊ መልክ ከአባት ወደ ልጅ ፣ ልጅ የሌለ እንደሆነ ወደ ወንድም ወይም ብዙ ልጆች ፣ ብዙ ወንድሞች ባንድ ጊዜ በሚገኙበት ጊዜ ፣ የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ሥልጣን የያዙት ወገኖች ለፈቀዱት እየተላለፈ ከሰሎሞንና ከንግሥተ ሳባ እንወለዳለን የሚሉት ነጋሢዎች ኢትዮጵያን በሙሉ በፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን አስተዳድረዋል ።

በዙፋን የነበረው ንጉሥ ሞቶ ሌላው ሲተካ ዐዋጅ ነጋሪው ወደ አደባባይ ወጥቶ ፣ «ያለንም እኛ ፣ የሞትንም እኛ ፣ ወዳጃችን ይደሰት ፣ ጠላታችን ይዘን» የሚል ዐዋጅ ማስነገር የተለመደ ነው ።([1]) ትርጓሜውም የሞተውም ነጋሢ ፣ ወደ ዙፋን የወጣውም መስፍን ካንድ ሰሎሞናዊ ቤተሰብ መሆናቸውን ለማስረዳትና የነገሠውን የደገፉ እንዲደሰቱ ፣ ሌላ ይሁን ያሉት እንዲያዝኑ ለማለት ነው ።

በ1762 ዓ. ም. የተምቤኑ ተወላጅ ራስ ስሑል ሚካኤል ንጉሥ ኢዮአስን በሻሽ አሳንቀው ካስገደሉ ወዲህ ፣ የንጉሥ የገዥነት ሥልጣን ተዳከመና ከራስ ስሑል ሚካኤልና በኋላም ከታላቁ ራስ ዐሊ ወዲህ ሥልጣን በእንደራሴዎች እጅ ስለገባ ፣ ከራስ ስሑል ሚካኤል እስከ ታናሽ ራስ ዐሊ ድረስ ያለው ጊዜ (1762—1845) ዘመነ መሳፍንት ተባለ ። መሳፍንቱም በጦርነት ፣ በትግል እንደ ምንም ብለው የእንደራሴነቱን ሥልጣን ሲጨብጡ የነጋሢነት ዘር እንደሌላቸው ራሳቸው በማመን ፣ 'ብንነግሥም ሕዝቡ አይቀበለንም' በሚል ሥጋት ልባቸው

---

1 Annales Iyasu - 1 - guidi p. 31

የፈቀደውን አንዳንድ የነጋሚ ዘር እያነገሡ እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ
መነሣት ድረስ ቆዩ ።

ነገር ግን ፣ እንደ ምንም ተጣጥሮ አንዱ መስፍን በጐንደር
እንደራሴነት ሲይዝ ፣ ለስሙ እንደ መንግሥት እንደራሴ ይቈጠ
ራል እንጂ ፣ በመላው ኢትዮጵያ ቀርቶ ባማራውና በትግሬው
አውራጃ ሁሉ ሥልጣኑን ማረጋገጥ እያቃተው ፣ ሁሉም የየክ
ፍለ ሀገሩ ባላባት ‘ለእንደራሴው አልታዘዝም ፣ ማን ከማን ያን
ሳል?’ እያለ የሚዋጋበት ከማዕከላዊው ከጐንደር መንግሥት
እየተነጠለ ለብቻው የሆነበት ጊዜ ብዙ ነው ።

ለምሳሌ ፣ በታላቁ ራስ ዐሊና በፈጻሚ መንግሥት ተክለ
ጊዮርጊስ ጊዜ ፣ የሸዋ መሳፍንት ከጐንደሩ ንጉሥ ተለይተው ለብ
ቻቸው ሆነው ፣ በራሳቸው መስፍንነት ሲተዳደሩ ቆይተዋል ።
በዐፄ ቴዎድሮስ አነሣሥ ዋዜማ የቴዎድሮስ ሚስት የምንትዋብ
አባት ፣ ትንሹ ራስ ዐሊ ፣ የጐንደርን መንግሥት በእንደራሴነት
ሲያስተዳድሩ በዚሁ ጊዜ ደጃች ውቤ ስሜንን ፣ ትግራይንና
ትግረን ሲገዙ ሁለቱ መሳፍንት የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ
እርስ በርሳቸው ይዋጉ ነበር ።

ሁለቱንም በዚያን ዘመን ሥልጣን ሊያስጨብጥ የሚያስ
ችለው የዘር ባላባትነት መሆኑ ቀርቶ በኃይል ፣ ኃይሉም የሚገ
ኘው ከጦር መሣሪያ ፣ የጦር መሣሪያውም የሚገኘው ከአውሮፓ
ኃያላን መሆኑ ስለ ገባቸው ፣ መሳፍንቱ ሁሉ በየበኩላቸው
የጦር መሣሪያ የመሻት ምኞት አደረባቸው ። «እገሌ ኃያል
ነው ። የእገሌ መንግሥት ከእገሌ ይበልጣል ። ለርሱ ብትጽፉ
መሣሪያ ይልክላችኋል ፤ ምኞታችሁን ይፈጽማል» እያሉ አን
ዳንድ ባጠገባቸው የሚገኙ የወንጌል መልእክተኞች ወይም ነጋ
ዴዎች የሆኑ የውጭ አገር ሰዎች በጠቆሟቸው መሠረት ለእ
ንግሊዝና ለፈረንሣይ ፣ ለሌሎቹም መሪዎች በደብዳቤ ወዳጅ
ነትን ይሻሙ እንደ ነበረ ሠነዱ ሁሉ ያመለክታል ። አንዳንድ
ጊዜ ሁሉም ባንድ ወቅት ፣ ባንድ ሰሞን በተመሳሳይ ቃል ለአ
ውሮፓ መሪ ወይም ንጉሥ የጻፉት ሲነበብ ፣ ደብዳቤውን ለሁ
ሉቱም ያዘጋጀው አንድ ሰው ይመስላል ።



ለምሳሌ ፣ ራስ ዐሊ (ትንሹ) ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ
«እምኃበ ርዕሰ መኳንንት ፣ ዐሊ ገብረ ንጉሠ ነገሥት ፣ እግዚ
አብሔር ዘይትወሐድ በመለኮት ፣ ወይሜለስ በገጻት ። ትብጻሕ
ኃበ ንግሥተ እንግሊዝ ፤ እንዴት ነሽ? በጎ ነሽ? የሰማይ የም
ድሩን ያህል ፣ እኔ ባንቺ ወዳጅነት ጠንቻለሁ ፤ አንቺም በኔ
ወዳጅነት ጥኚ............የምትወጅውን ነገር ላኪብኝ ፣ እሰድልሻለሁ»
ብለው ሲጽፉ ፣ ደጃች ውቤም ለኝሁ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት
ቃሉም ፣ ብዕሩም አንድ ዐይነት ባንድ ጸሐፊ እጅ የተጻፈ ይመ
ስላል ። ([1])

በሌላ ደብዳቤ ደግሞ ፣ ራስ ዐሊ «ዛቲ. ጦማር. ዘተፈነወት
እምኃበ ራስ ዐሊ ፣ ንጉሠ ሐበሻ ፣ (*) ትብጻሕ ኃበ ፊቅጦርያ (ቪክ
ቶሪያ) ንግሥተ እንግሊዝ» ብለው የውጭ መሪዎችን በማጭ
በርበር ራሳቸውን ንጉሥ አድርገዋል ። እንደውነቱ ግን ፣ በርሳ
ቸው የእንደራሴነት ዘመን ሥልጣን ባይኖራቸውም ፣ ንጉሡ
የእናታቸው የወይዘሮ መነን ባል ዐፄ ዮሐንስ ሣስተኛ ናቸው ።
የሆነ ሆኖ ፣ ዐሊ በዚሁ ደብዳቤ ላይ በቆንሲል ፕሎውዴን እጅ
የመጣላቸውን ዕቃ ደስ ብሏቸው ከተቀበሉ በኋላ ፣ የተላከላቸውን
ዕቃ የሚመስል ዕቃ ለመላክ ደሃ መሆናቸውን ገልጸው በበኩ
ላቸው ሁለት ጋሻ ፣ ሁለት ሾተል ፣ ሁለት ቢተዋ (አምባር)......
መላካቸውን አመልክተው ፣ መደምደሚያውን «.........እኔ ድሀ
ነት ጦር እየሆነብኝ ፣ ወታደር እየበዛብኝ ነው ። ደመወዝ የም
ሰጠው ብር ቢሰዱልኝ የወዳጅነት ምልክት ነው..........ደግሞ
ፍልፍል ፈረንጅ ነፍጥ (ጠብመንጃ) ፣ በከምሱል (ባሩድ ባለ
በት ጥይት) የሚተኮስ ፣ ዘለግ ያለ ቢገኝ እወዳለሁ ። እንግሊዝ
ሁሉ ቢመጣ በምገዛው አገር ፣ በምችለው ሁሉ በፍቅር እቀበ
ላለሁ» ሲሉ ጽፈዋል ።

---

1 Copyright of the Public Record Office, London, Tef. Fol/7

* ራስ ዐሊ የአበሻ ንጉሥ ብለው የጻፉት በውጭ አገር መንግሥታት
ዘንድ ለመከበር በማን አለብኝነት የጨመሩት ነው እንጂ ፣ የንጉሥ
እንደራሴ እንጂ ንጉሥነት የላቸውም ። ንጉሡ በዚህ ጊዜ የእናታ
ቸው የእቴጌ መነን ባል ዐፄ ዮሐንስ ማልሳይ ከርሳቸውም በፊት
ዐፄ ሣህለ ድንግል ናቸው ።

በመካከል አገር በቤጌምድር ያሉት ራስ ዐሊ የራሳቸውን ጉዳይና ችግር በዚህ ዐይነት ሲገልጹ ፣ የሥልጣን ባላጋራቸው ትግሬንና ትግራይን እስከ ምጥዋ ድረስ የሚገዙት ደጃች ውቤ ደግሞ የሕሊና ዕረፍት የሚነሣቸው የባሕር ጠረፉና የወደቡ ጉዳይ ስለሆነ ፣ ለኝሁ ንግሥት በራሳቸው አባባል በጻፉት ደብዳቤ ላይ «............ቀድሞ ዘመን አባቶቻችን ምጥዋ እስከ ባሕር ድረስ በጃቸው ነበር ። ኋላ እኛ በኛ (እርስ በርሳችን) ብንጣላ ትርኮች (ቱርኮች) በኃይል በግድ መተው ወሰዱት ። ተከትለው ከሁለት ዓመት ወዲህ ጦር ሰደው ምንኩሉን ደሆኖን (አርኪቆ) በር ያዙት ። በዚህም ወትሮ (በሌላ ጊዜ) የሚሰዱልኝን ግብር ቢያስቀሩብኝ ፣ ናይብ ዘንድሮ ጦር ሰድጄ ትርኮችን አባርሬ ምጥዋ ከተትኋቸው ። አንቱም የክርስቲያን ንጉሥ (ንግሥት) ክርስቲያን ሁሉ የምትወዱ ነሁ ። ጉልበተኛ ነዎና እንዲረዱን ወዳጅነትዎን እፈልግአለሁ ............ ከሁሉ እምንፈልገው እንግሊዝን (የእንግሊዝን) ወዳጅነት ነውና አበሻን መውደዳችሁን በዝህ (በዚህ) ነው እምናውቀው»[1] ብለዋል ። ሁለቱም ሲጽፉ በደብዳቤያቸው ላይ ቀንና ዓመተ ምሕረት አላደረጉበትም ።

ነገር ግን ፣ ራስ ዐሊ በሥልጣን ላይ የነበሩት ከ1823 እስከ 1847 ዓ. ም. ድረስ ደጃች ውቤ ከ1824/1825/ እስከ 1847 ዓ. ም. መካከል ስለሆነ ፣ ደብዳቤውም ቆንሲል ፕሎውዴን እንዳመለከተው ፣ ሎንዶን የደረሰው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1849 ዓ. ም. ስለሆነ ፣ የደብዳቤዎቹ ቀኖች በ1841 ወይም በ1842 ዓ. ም. ላይ መሆኑ ይገመታል ።

በዚያን ዘመን በነበረው በየብስና በባሕር ጉዞ ርቀት እንዲሁም በቱርኮች ባሕር ጠረፍ አካባቢ መገኘት ምክንያት ከኢትዮጵያ መሳፍንት የሚላከው ደብዳቤ ወደ ሎንዶን ደርሶ ፣ በውጭ ጉዳይና በባሕር ማዶ ግዛት ቢሮ ባለሥልጣኖች ፊት ቀርቦ የመጠናት ዕድል የሚያገኘው ከብዙ ጊዜ በኋላ ነው ። ምናልባትም እገናናይቱ የእንግሊዝ ፣ የአየርላንድና የሕንድ ንግሥት ፊት ላይቀርብ ይችላል ። ንግሥቲቱ ከሕንድ ሌላ የዚያ ሁሉ የአፍሪካ ፣ የእስያና የአሜሪካ አገሮች የበላይ ገዥ ስለሆነች ፣ ያንዱ ወይም የሁለቱ የኢትዮጵያ መሳፍንት ደብዳቤዎች

---

1 Public Record Office , London Fol (5/1/6



ወደርሷ ለመድረስና መልስ ለማግኘት ያላቸው ዕድል የመነመነ ነው ። አንዳንድ ጊዜ ከራስ ዐሊ ወዲህ በዙፋን ለተከታተሉት ነገሥታት በርሷ ስም ደብዳቤ ቢመጣም ፣ ደብዳቤው እንደ አስፈላጊነቱ ለእንግሊዝ መግቢያና መስፋፊያ እንደሚጠቅም ሆኖ በቅኝ አገርና በውጭ ጉዳይ ቢሮ እየተጠናና እየተዘጋጀ የሚመጣ ደብዳቤ ነው ።

ስለዚህ ፣ ማናቸውም አውሮፓዊ መሪ ለመንግሥቱ ኃያልነት የሚጠቅመውን ብቻ እያሰበ ይወስናል እንጂ ፣ በተለይ ከአፍሪካና ከእስያ መሳፍንት ዘንድ የሚሰነዘረውን ወዳጅነት ለመግቢያ መሣሪያ ከማድረግ በቀር ከምንም አይቆጥረውም ። «በኔ ወዳጅነት ጽኚ ፣ እኔም ባንቺ ወዳጅነት ጸንቻለሁ» የሚለው የራስ ዐሊም ፣ የደጃች ውቤም አባባል ለንግሥት ቪክቶሪያ ጆሮ አይጥምም ።

የሆነ ሆኖ ፣ የጐንደሩ እንደራሴ ራስ ዐሊ በሁሉም ላይ የበላይነት ሲሰማቸው በስሜንና በትግሬ ፣ በትግራይ ደጃዝማች ውቤ የራስ ዐሊን የበላይነት ከምንም ሳይቆጥሩ ከውጭ መንግሥት መሪዎች በቀጥታ እየተጻጻፉ የግል ነጻነታቸውን ሲያረጋግጡ ፣ የጐጃም መሳፍንት እነ ደጃች ተድላ ጓሉ ከዳሞት መሳፍንት ከነደጃች ዘውዴ ጋር ሲዋጉ ፣ ቀጥለው ደጃች ጐሹ ዘውዴና ልጃቸው ብሩ ጐሹ በኅብረት ከራስ ዐሊ መኳንንት ከነደጃች ሥዩም በቃሽኝ ፣ ከነደጃች መሸሻ ባቡ ጋር ተዋግተው የጐጃምንና የዳሞትን ነጻነት ከተከላከሉ ወዲህ አባትና ልጅ እርስ በርሳቸው ተዋጉ ። በኋላም ልጅየውም ፣ አባትየውም የራስ ዐሊን የበላይ መስፍንነት ዐውቀው ገቡላቸውና የራስ ዐሊ ግዛት በጐጃም ላይ ተመሠረተ ።

ስሜን ፣ ትግረና ትግራይ ፣ ቤጌምድርና ጎጃም በዚህ ዐይነት ሁኔታ ሲገኙ ፣ ሸዋ ደግሞ ከጐንደሩ መንግሥት ቀደም ብሎ በማፈንገጥ በራስ ዐሊ (ትንሹ) ጊዜ በሸዋው መስፍን በታወቁት በሣህለ ሥላሴ ይገዛ ነበር ። መስፍኑ በግዛታቸው ፣ «ራስ ሣህለ ሥላሴ ንጉሠ ሸዋ» ወይም ባጭሩ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ እየተባሉ በሚጠሩበትና ራስ ዐሊና ደጃች ውቤ እርስ በርሳቸው እየተዋጉም ፣ እየታረቁም ሲኖሩ ሁለቱም በየበኩላቸው የእንግሊዝንና የፈረንሣይን ወዳጅነት አጥብቀው በሚፈልጉበት ጊዜ እርሳቸውም በበኩላቸው ሥራ አልፈቱም ።

መሳፍንቱ የውጭ አገር ትምህርቱንም ፥ ሥልጣኔውንም ታሪኩንም በቀጥታ ራሳቸው ተምረው ስለማያውቁት ፥ እላይ የጠቀስናቸው «ላገር ጉብኝት ፥ ለንግድ ወይም ለወንጌል መልክተኝነት መጥተናል» የሚሉት የውጭ አገር ሰዎች ብዙ ጊዜ እንዳመቻቸው ምክር እያቀረቡ ፥ የማይሆነውን እንደሚሆን እያስመሰሉ በመንገር መሳፍንቱን ያሳስቷቸው ነበር ። ለምሳሌ ፥ አንቷን ዳባዲና አርኖ ዳባዲ የሚባሉ ሁለት ፈረንሣዮች በቤጌምድር ፥ በጐጃምና በትግሬ እየተዘዋወሩ ከየመሳፍንቱ በመወዳጀት የፈረንሣይን ጥቅም በሚጠብቁበት ጊዜ ፥ የእንግሊዝ መንግሥት የፈረንሣይ የቅኝ አገር ኃይለኛ ባላንጣ ስለሆነ ወደ ሸዋ መጥቶ ማናቸውንም ግንኙነት እንዳያደርግ ለማደናቀፍ ፥ ሣህለ ሥላሴ እንግሊዞቹን እንዳይቀበሉና የነርሱም ገናናው ንጉሥ ሉዊ ፊሊፕ ሊያግዱላቸው እንደሚችል እያስመሰሉ ስለ ነገሩዋቸው ፥ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ አጽፈዋቸዋል ።

«ዛቲ ጦማር ዘራስ ሣህለ ሥላሴ ንጉሠ ሸዋ ......ትብጻሕ ኃበ ሉዊ ፊሊፕ ፥ ሃይማኖቱ እቀና ፥ ክርስትናው እጠና ፥ ጋሻው እበረደደ(*)...... ሃይማኖትህ ሃይማኖቴ ነው ፥ አገርህ አገሬ ነው ።......እንግሊዞች ወዳገሬ መምጣት አስበዋል አሉና አንተ ዐርፋችሁ ተቀመጡ ታላልኻቸው ቀረ አይደሉም ። ተቆጥተህ አስቀርልኝ......»([1])

ራስ ዐሊና ደጃች ውቤ ለንግሥት ቪክቶሪያ ፥ «እኔ ባንቺ ወዳጅነት ጸንቻለሁ ፤ አንቺም በኔ ወዳጅነት ጽኚ» እያሉ ሲጽፉ ፥ አሁን ደግሞ ሣህለ ሥላሴ ይኸን የመሰለ የየዋህነት ደብዳቤ እስከ መጻፍ መድረስ ፥ የዚያን ዘመን መሳፍንት ስለ ውጭ አገር ሁኔታ ፥ ስለ ፖለቲካውም ሆነ ስለ አስተዳደሩ ያላቸው አስተያየት በጣም ዝቅ ያለ ደረጃ ላይ መሆኑን እንገምታለን ። ብዙ ጊዜም መሳፍንቱ ባገር ውስጥ የሌላቸውን ሥልጣን ፥ ያልጨበጡትን ግዛት ፥ ያልተሰጣቸውን የሥያሜ ደረጃ በራሳቸው ፈቃድ እየወሰዱ ውቤም ፥ ዐሊም 'የአበሻ ንጉሥ' እያሉ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት ታሪካዊ መዝገብ በሎንዶን ይገኛል ።

---

* ኃይሉ የሚያስበረግግ ለማለት ነው ።

1 Bibleothéque Nationale - Paris Department Manuscripts 40 Dosiers d'Abbadie



የሆነ ሆኖ ፥ በሣህለ ሥላሴ የዋህነት በመጠቀም ፈረንሣዮቹ እነ አንቷን ዳባዲ ያገራቸውን ጥቅም ለመጠበቅና ፈረንሣይ ብቻዋን በሸዋ እንድትስፋፋ ይህን የመሰለውን የየዋህነት ደብዳቤ ያጽፏቸው እንጂ ፥ በመጨረሻ ግን ሙካር ገብቶ እንግሊዝን ለመከልከል ፈረንሣይ ምንም ሥልጣን እንደሌለው ታውቆ ፥ እንግሊዝን አትምጣብኝ ማለቱም የማያዋጣ አሳብ ሆኖ ስለተገኘ ፥ ትክክለኛው መንገድ ከሁለቱም ጋር መወዳጀቱ ብቻ ስለሆነ ፥ የፈረንሣይ መንግሥት በ1836 ዓ. ም. ሮሼ ዴሪኩርን ፥ የእንግሊዝ መንግሥት በ1834 ዓ. ም. ካፒቴን ሐሪስን ልከው ከሁለቱም ጋር የሸዋው ንጉሥ ስለ ንግድ ፥ ስለ ወዳጅነት ተዋውለው ጉዳዩ በዚህ ቆመ ።

እንግዲህ የሰሜኑ ክፍለ ሀገርና ቤጌምድር ፥ ጐጃምና ሸዋ በዚህ ዐይነት የመከፋፈል ሁኔታ ሲገኙ ወሎ ፥ ይነስ ይብዛ ፥ ራስ ዐሊ ተወላጅነት ስላላቸው ከጐንደር እንደራሴ ሥልጣን ሥር ሊወጣ አልቻለም ። ላስታም አንድ ፩ ጊዜ መሸፈቱ ባይቀርም ፥ እንደዚሁ ከራስ ዐሊ ሥልጣን አልወጣም ። የደቡቡ ክፍል ከ16ኛው መቶ ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አካል ሆኖ ሲኖር ፥ በጐንደር ግን የመንግሥቱ አቅዋም ከ17ኛው መቶ ዓመት መጨረሻ ገደማ ነገሥታቱም ፥ መሳፍንቱም እርስ በርስ ጐራ እየለዩ በመዋጋት ስለ ተዳከሙ ከአክሱም ጀምሮ ፥ ሲያንስም ሲበዛም ፥ የኢትዮጵያ አካል የነበሩት ሐረርጌና ባሌ ፥ አሩሲና ሲዳሞ ፥ ከፋና ሊሙ ፥ ወለጋና ኢሉባቦር በየራሳቸው ባላባት ይተዳደሩ ጀመር ። እነዚህ ሁሉ አውራጃዎች በዘርና በሃይማኖት ልዩነት ወይም ባንዱ የማፈንገጥ ፍላጐት ባለው ቀንደኛ ባላባት አነሣሥ ዐልፎ ፥ ዐልፎ ጦርነትና ግጭት ባይጠፋም ፥ ሁሉም ከግራኝ አህመድ አነሣሥ በፊት ለነበሩት ለእነ ዐፄ ዐምደ ጽዮን ፥ ለእነ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ይገብሩ እንደ ነበረ በነዚሁ አውራጃዎች ዐልፎው ፥ ዐልፎው የሚገኙ የታሪክ ቅርሶች በደንብ ያስረዳሉ ።([1])

ስለዚህ ፥ በጐንደር መንግሥት ከ18ኛው መቶ ዓመት መጨረሻና በ19ነኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ ነገሥታቱ ሥልጣናቸውን በመሳፍንት ተነጥቀው ለስሙ ብቻ በቤተ መንግሥት

---

1 Chronique du Régne de Menelik II Tome II — G. Sellassie — M. Decoppet p. 464.

እንደ ሴት ወይዘሮ ዐርፈው እንዲቀመጡ ሲደረግ፣ የነርሱን ሥልጣን የወረሱት መሳፍንት ደግሞ የገዥነት ሥልጣናቸውን በሌላው ላይ ለማረጋገጥ አቅም ሲያንሣቸው እንኳን የደቡቡ የሰሜኑና የመካከሉ ክፍለ ሀገርም ባለፈው እንደ ተመለከት ነው ተከፋፍሎ ለየብቻ ሆነ ። በዚህ አሳዛኝ የመከፋፈል ሁኔታ ላይ ነው — የቴዎድሮስ ፣ የዮሐንስና ፣ የምኒልክም አነሣሥ ያተኮረው ።



## ምዕራፍ ሰባት

### የማርቆስ መንበርና ዘረኛዋ የፍትሐ ነገሥት አንቀጽ
### የአቡነ ሰላማ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመዝግቦ እንደሚገኘው ፣ የዓለም ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ባሕርይ የተነሣ ፣ የእርስ በርስ መከፋፈል ሲደርስባት ፣ ሁለቱ ታላላቅ የክርስትናን እምነት የሚያስፋፉት ድርጅቶች የሮማ ቫቲካን ሁለት ባሕርይን ፣ የእስክንድርያ ፓትሪያርክ አንድ ባሕርይን በመደገፍ ፣ እርስ በርሳቸው በጠብ ተለያዩ ።

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአራተኛው ክፍለ ዘመን ከእስክንድርያ ከማርቆስ ወንበር በመሆኑ ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ሐያኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ግብጻዊ ጳጳስ እየተላከ ይኸው የተዋሕዶ እምነት እየተስፋፋ መጣ ። ከግብጽ ከማምጣት ይልቅ ከኢትዮጵያውያን ጳጳስ መሾም እንዳይቻል ከግብጻውያኑ በዐረብኛ ተጽፎ ወደ ግዕዝ የተተረጐመው ፣ በቤተ መንግሥቱም በቤተ ክህነቱም ተከብሮ የኖረው የፍትሐ ነገሥት መጽሐፍ ይከለክላል ።

በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ በአራተኛው አንቀጽ ፣ «ኢትዮጵያውያን በራሳቸው ፈቃድ ከዐዋቂዎቻቸው ውስጥ ሊቀ ጳጳሳት አይሹሙ ። የነርሱ ጳጳስ ሊሆን የሚገባው ከእስክንድርያው ባለ ቤት (ሊቀ ጳጳስ) ሥር ያለው ነው ። ሊቀ ጳጳስ ለነርሱ የሚሆነውን ፣ ለርሱ የሚታዘዘውን አንድ ሊቅ መርጦ ይሾምላቸዋል.........» ይላል (1) ግብጾቹ እንደዚህ ያለውን ቃል ሲያሰፍሩ

1 ወሰብእ ኢትዮጵያ ኢይሚሙ ላዕሌሆሙ ሊቀ ጳጳሳት እማዕምራኒሆሙ ወኢ በሥምረተ ርዕሶሙ እስመ ጳጳሶሙ ይከውን እምታሕተ ዕዴሁ ለበዓለ እስክንድርያ ። ወውእቱ ዘይደልዎ ከመ ይሚም ላዕሌሆሙ ሊቀ እምኀቤሁ ዘውእቱ መትሕተ ሊቀ ጳጳሳት ። ፍትሐ ነገሥት ጉዳዩ ያሳተመው አንቀጽ 42.

በኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ለራሱ መንፈሳዊ አስተዳዳሪ የሚሆነውን ጳጳስ ከራሱ ለመሾም መብትም ፡ ብቃትም እንደሌለው በማድረግ ነው ። የበለጠ ደግሞ የሚያስገርመው እንደዚህ ያለውን ዘረኛ አንቀጽ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነቱም ፡ ቤተ መንግሥቱም አሜን ብለው ለረዥም ዘመናት መቀበላቸው ነው ። (*)

ስለዚህ ፡ ጳጳስ ሲሞት አዲስ ጳጳስ ለማስመጣት ነገሥታቱ ለእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ የሚሰጠውን ገጸ በረከት አሲዘው ወደ ግብጽ መላክተኛ በላኩ ቁጥር መላክተኞቹ ከምጥዋ ጀምሮ የቱርክና የግብጽ ግዛት የሆነውን አገር በሚያቋርጡበት ጊዜ ፡ መርከብ ለማግኘት ደጅ በሚጠኑበት ሰዓት የነበረባቸው የመጉላላትና ዐልፎ ፡ ዐልፎ የመታሰር ችግር ከልክ ያለፈ ነበር ። በየኬላው አዛዡና ባላባቱ ለኔም ቀረጥ ወይም መታያ ካላቀረባችሁ አታልፉም ወይም ከአገሬ አትወጡም እያለ ሲያስር ፡ ሲፈታ የነበረበት የታሪክ ጊዜ ረዥም ነው ። ግብጽም ከደረሱ በኋላ መታያውን ባንድ ወገን ለግብጽ ገዥ ፡ በሌላ ወገን ለሊቀ ጳጳሱ አቅርበው ወደ ኢትዮጵያ የሚላከው ጳጳስ ተመርጦ ፡ ተቀብቶ እስኪሰጣቸው ድረስ በመካከሉ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ከግብጹ ከሊፋ ወይም ከሡልጣኑ ፈቃድ ለማግኘት ሌላ ችግር አለ ። ከሃይማኖት ልጆችህ ብዙ ወርቅ ታገኛለህና ለኔ በብዙ ገብር ወይም ከኔ ሳታስፈቅድ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ አትላክ በማለት በሊቀ ጳጳሱ በራሳቸው መጉላላትና መታሰር ዐልፎ ፡ ዐልፎ ሲደርስባቸው ኖሮአል ።

ከዚህም በቀር ፡ የግብጽ ሡልጣን ጳጳሱን በማሰር ወይም የተመረጠውን ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ አልክም በማለት ባስፈራራ ቁጥር የኢትዮጵያ ነገሥታት እነ ዐፄ ሠይፈ አርዕድ (1337—1365) «እኛም አባታችንን ካልፈታህ ፡ ጳጳሳችንን ካለቀቅህ የአባይን ወንዝ እንዘጋብሃለን» እያሉ ሲያስፈራሩ የኖሩበት ታሪክ ብዙ ነው ። ጳጳሱ በማናቸውም ምክንያት ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት በአቋረጠ ቁጥር ፡ ኢትዮጵያውያኑም ከመካከላቸው እንዳይሾሙ በፍትሐ ነገሥት ስለ ተከለከሉ ክህነት ፡ ዲቁናና ቅስና ሰጭ ጠፍቶ ፡ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ትዘጋለች ፡

* አንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመት ።



እስላምና ካቶሊክ ይውጠናል በሚል ሥጋት የጳጳሱን መቅረት እግዚአብሔር እንደ ተቆጣ በመቁጠር ነገሥታቱና መኳንንቱ ፡ ካህናቱና መነኰሳቱ በጸሎት ፡ በምሕላ የጳጳሱን መምጣት በናፍቆት ሲጠባበቁ ይኖሩ ነበር ።

ቅዱስ ሐርቤ (ገብረ ማርያም) የሚባለው ከዛጉዌ ወገን የሆነው ንጉሠ ነገሥቱ ይኸን የቆየ ልማድ በዘመኑ ለመሻርና ከጳጳሱ በታች በየአውራጃው ተበታትነው የሚያስተምሩ ኤጲስ ቆጶሳት ይሾሙ ብሎ በዘመኑ ለነበሩት ለእስክንድርያው ከኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ለአባ ገብርኤል መልእክተኛ ልኮ ፡ ሊቀ ጳጳሱ ፈቃዱን ሳይፈጽሙለት ቀርተው በዚሁ ከፓትርያርኩ ስለ ተጣላ ፡ ከዚያ ወዲህ የተጻፈው በሚያዝያ 10 ቀን የሚነበበው ስንክሳር «ሊቀጳጳሱን አባ ገብርኤልን ብፁዕ ወቅዱስ እያለ ሲያመሰግን ፡ የኢትዮጵያ ንጉሥ ኤጲስ ቆጶሳት ካልተሾሙ ብሎ ከሊቀ ጳጳሳቱ ስለ ተጣላ ፡ እግዚአብሔር ተቆጥቶ በአገሩ በኢትዮጵያ ላይ መቅሠፍት አወረደበት እያለ ይተርካል ።» ([1]) ስለዚህ አስቀድሞ በነበረው ልማድ መሠረት ፡ በየጊዜው ጳጳስ ከግብጽ የማስመጣቱ ጉዳይ እንደ ቀጠለ ኖረ ።

በዚሁ መሠረት ፡ በሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ፡ ባማራና በቤጌምድር ዋናው እንደራሴ ራስ ዐሊ ፡ በስሜን በትግራይና በትግሬ ደጃች ውቤ በሚገዙበት ጊዜ ልጅ ካሣ ኃይሉ ለየመሳፍንቱ እንደ አሽከር ሲያገለግሉ ኖረው ፡ በኋላም የራስ ዐሊን ልጅ ተዋበችን አግብተው ከእነራስ ዐሊ ጋር በደጅ ጥናትና በሽፍትነትም ባሉበት ሰዓት የስሜኑና የትግራዩ ገዥ ደጃች ውቤ በምጥዋም አካባቢ ካሉት ከግብጾቹ አስተዳዳሪዎች ፡ ከውጭ ቆንሲሎችም በመስማማት ከእስክንድርያ ጳጳስ ለማስመጣትና ለመንገሥ ዐቀዱ ። መቼም ጳጳስ ለማስመጣት ከሸዋውም ፡ ከቤጌምድሩም ገዥ የሚቀናው በወደቡ በምጥዋ አካባቢ ያለውን ክፍለ ሀገር የሚያስተዳድረው ነው ።

በዚህ ምክንያት ፡ ደጃች ውቤ ለመንገድ መሪነት ከካቶሊኮቹ መሪዎች ከነአባ ያዕቆብ ጋር ከተስማሙ በኋላ ፡ አለቃ ሀብተ ሥላሴ የሚባሉትን የሸዋ ተወላጅ በአጠገባቸው አስቀምጠው ፡

1 ዋዜማ ፡— ብላቴን ጌታ ኅሩይ ገጽ 69 — 70

ዋና አማካሪ አድርገዋቸው ነበርና አለቃ ሀብተ ሥላሴን ለግብጹ ሡልጣንና ለፓትርያርኩ ለአቡነ ጴጥሮስ የሚቀርበውን መታያ አሲዘው ወደ እስክንድርያ ልከው ስለነበረ ፣ ወደ ኢትዮጵያ ስለሚላኩት ጳጳስ በ1833 ዓ. ም. ስብሰባ ተደርጎ ፣ እንድርያስ የሚባሉት የ25 ዓመት ወጣት ተመረጡ ። ወዲያው እንደ መጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ (ፍሬምናጦስ) አባ ሰላማ ተብለው በመሠየም ከአለቃ ሀብተሥላሴ ጋር በ1834 ዓ. ም. በኅዳር 3 ቀን መጥተው ከደጃች ውቤ ጋር ተገናኙ ።

በኢትዮጵያ አጠገቡ ጳጳስ ያስቀመጠና በመጠኑም ቢሆን የነጋሢነት ዘር ያለው ሥልጣን ላይ ላሉ ገዥዎች አደገኛ ነው ። ደጃች ውቤ በምጥዋ በኩል በብላታ ኮከቤ አማካይነት በግዥም ፣ በስጦታም ብዙ የጦር መሣሪያ እንደሚሰበስቡ ፣ የሚነግሡበትንም የደረስጌ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አገር ውስጥ ባሉ የውጭ አገር ሰዎች በነሺምብር ዊልሄም አሠማምረው እንደሚሠሩ በዋናው የመንግሥቱ እንደራሴ በራስ ዐሊ ዘንድ የተሰወረ አይደለም ። አሁንም ከድርጅቱና የሚነግሡበትን ቤተክርስቲያን ከማሠራት ጋር አንጋሹን ጳጳስ ማስመጣታቸው ሲሰማ ፣ ራስ ዐሊ ሊታገሡአቸው አልቻሉምና ሁለቱም ለጦርነት ይዘጋጁ ጀመር ።



አቡነ ሰላማ
(ከጉስታቭ አሬን መጽሐፍ)



የአቡነ ሰላማ ዘውድ
(ከሮገር አክቶን መጽሐፍ)